የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሰላሳኛ ዓመት ቁጥር ፷፮
አዲስ አበባ ጳጉሜ ፬ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

30th Year No.66
ADDIS ABABA 9th, September, 2024

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፴፫/፪ሺ፲፮

የፌደራል የመንግሥት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ……………………………………………………………………………………..ገጽ ፲፯ሺ፶

**Content**

Proclamation No.1333/2024

The Federal Public Procurement and Property Administration Proclamation …………………………………….Page 17050

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፴፫/፪ሺ፲፮

## የፌደራል የመንግሥት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ

በሥራ ላይ የነበረው የኢትዮጵያ ፌደራል መንግሥት የግዥ እና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፮፻፵፱/፪ሺ፩ በይዘት እና አፈፃፀም ክፍተቶች ያሉበት በመሆኑ፤

የመንግሥት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅን የተፈፃሚነት ወሰን በማስፋት በመንግሥት የልማት ድርጅቶች ላይ ተፈጻሚ እንዲሆን ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

የመንግሥት ግዥ አፈፃፀምና ንብረት አስተዳደር ሥርዓቱን ግልፀኝነት በማሻሻል እና ተደራሽነቱን በማስፋት በመንግሥት ግዥ አፈፃፀምና ንብረት አስተዳደር ዙሪያ የሚከሰት የሕግ ጥሰት የሚያስከትለውን አስተዳደራዊ ተጠያቂነት ግልፅ ማድረግ በማስፈለጉ፤

## PROCLAMATION No. 1333 /2024

## THE FEDERAL PUBLIC PROCUREMENT AND PROPERTY ADMINISTRATION PROCLAMATION

**WHEREAS;** the Ethiopian Federal Public Procurement and Property Administration Proclamation No. 649/2009 had gaps in regard to its content and implementation;

**WHEREAS;** it has become necessary to redefine the scope of application of the Federal Public Procurement and Property Administration Proclamation to encompass Public Enterprises;

**WHEREAS;** it is found necessary to clarify the administrative accountability resulting from violation of the law in the execution of Public Procurement and Property Administration by improving the transparency and accessibility of the public procurement and property administration System;

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ-አንቀጽ ፩ መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ምዕራፍ አንድ
## ጠቅላላ

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የፌደራል የመንግሥት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፴፫/፪ሺ፲፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/ "**ግዥ**" ማለት ዕቃዎችን፣ የምክር አገልግሎቶችን፣ ከምክር ውጭ የሆኑ አገልግሎቶችን እና የግንባታ ዘርፍ ሥራዎችን በመግዛት፣ በኪራይ፣ በሊዝ ስምምነት ወይም በማናቸውም ሌላ ተመሳሳይ ውል ማግኘት ነው፤

፪/ "**ዕቃ**" ማለት በጠጣር፣ በፈሳሽ ወይም በጋዝ መልክ የሚገኝ ጥሬ ዕቃ፣ ምርት፣ መሳሪያ፣ ሸቀጥ፣ ለገበያ የተዘጋጀ ሶፍትዌር እና እንስሳ ነው፤

፫/ "**የዕቃ ዋጋ**" ማለት አንድን ዕቃ ለማግኘት የሚከፈል አጠቃላይ ወጪ ሲሆን ከዕቃው ጋር ግንኙነት ያለውን እና ከዕቃው ዋጋ ያነሰ ዋጋ ያለው የተከላ፣ የትራንስፖርት፣የጥገና እና ሌላ ተመሳሳይ ከምክር ውጪ የሆነ አገልግሎት ዋጋን ይጨምራል፤

፬/ "**ከምክር ውጭ የሆነ አገልግሎት**" ማለት ከግንባታ ዘርፍ ሥራ እና ከምክር አገልግሎት ውጪ የሆነ ማንኛውም አገልግሎት ሲሆን፣ የኪራይ፣ የትራንስፖርት፣ የህትመት፣ የጥገና፣ የጥበቃ፣ የጽዳት፣ የኃይል አቅርቦት፣ የቴሌኮሙኒኬሽን፣ የውሃ አቅርቦት እና የመሳሰሉት አገልግሎቶችን

**NOW,THEREFORE**, in accordance with Article 55 Sub-Article(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

## CHAPTER ONE
## GENERAL

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as "The Federal Public Procurement and Property Administration Proclamation No. 1333/2024".

**2. Definition**

Unless the context otherwise requires, in this Proclamation:

1/ "**Procurement**" means obtaining goods, consultancy services, non-cosultancyservices, and works by purchase, hire or lease or any similar contractual means;

2/ "**Good**" means raw material, products, equipment or commodities whether in a state of solid, liquid or gas, or marketable software and live animals;

3/ "**Price of Good**" means the total cost incurred to acquire a good and includes the price of the installation, transport, maintenance or similar services related to the supply of that good, provided that the value of such services is less than that of the good itself;

4/ "**Non-Consultancy Service**" means any service other than works and consultancy services and includes hiring, transport, printing, maintainance, security, janitorial, power supply, telecommunication, water supply and other

ይጨምራል፤

፭/ "**የአገልግሎት ዋጋ**" ማለት አንድን ከምክር ውጭ የሆነ አገልግሎት ለማግኘት የሚከፈል አጠቃላይ ወጪ ሲሆን ከአገልግሎቱ ጋር የሚቀርብ ከአገልግሎቱ ዋጋ ያነሰ ዋጋ ያለውን ዕቃ ወይም የግንባታ ዘርፍ ሥራ ዋጋን ይጨምራል፤

፮/ "**የምክር አገልግሎት**" ማለት አማካሪዎች ያላቸውን ሙያዊ ክህሎት በመጠቀም የሚሰጡት የጥናት፣ የዲዛይን እና ቁጥጥር፣ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን የማደራጀት፣ ለደንበኞች ምክር የመስጠት፣ ስልጠና የመስጠት እና እውቀትን የማስተላለፍ የመሳሰሉት የአማካሪነት ባህሪ ያለው የአዕምሮ አገልግሎት ነው፤

፯/ ‹‹**የግንባታ ሥራ**›› ማለት ከሕንጻ፣ ከመንገድ፣ ከድልድይ፣ ከግድብ፣ ከወደብ፣ ከአውሮፕላን ማረፊያ፣ ከውሃ ሥራዎች፣ ወይም ከሌሎች መሰረተ ልማት ሥራዎች ጋር በተያያዘ የሚከናወን አዲስ ግንባታ፣ የመልሶ ግንባታ፣ ደረጃ የማሳደግ፣ የማፍረስ፣ የጥገና ወይም የማደስ ሥራ ሲሆን የዲዛይን እና ግንባታ፣ የኮንስትራክሽን ማኔጅመንት፣ የተርንኪ እና የመሳሳሉ ውሎችን ይጨምራል፤

፰/ ‹‹**የግንባታ ሥራ ዋጋ**›› ማለት አንድን የግንባታ ሥራ ለማከናወን የሚከፈል አጠቃላይ ወጪ ሲሆን ከግንባታ ሥራው ጋር ተጓዳኝ የሆነ እና ከዋናው ሥራ ያነሰ ዋጋ ያለውን የአገልግሎት ዋጋን ይጨምራል፤

፱/ ‹‹**የመንግሥት መሥሪያ ቤት**›› ማለት በሙሉ ወይም በከፊል በፌደራል መንግሥት በጀት የሚተዳደር ወይም በተቋቋመበት ሕግ የፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም ተቋም ተብሎ የተሰየመ የፌደራል መንግሥት አካል ሲሆን በፌደራል መንግሥት ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶችን ይጨምራል፤

related services;

5/ "**Price of Service**" means the total cost incurred to acquire a service and includes the price of the goods or works related to the supply of that service provided that the value of such goods or works is less than that of the service itself;

6/ "**Consultancy Service**" means a service of an intellectual and advisory nature provided by consultants using their professional skills to study, design or supervise, organize specific projects, advise clients, conduct training and transfer knowledge;

7/ "**Works**" means all works associated with construction, reconstruction, upgrading, demolition, repair or renovation of a building, road, bridge, dam, port, air port, water works or other infrastructure works, and includes design and build, construction management, turnkey and other similar contracts;

8/ "**Price of Works**" means the total cost incurred to acquire works and includes the price of the services ancillary to the works, provided that the value of those services is less than that of the works themselves;

9/ "**Public Body**" means any organ or institution of the Federal Government which is financed wholly or partly by budget allocated by the Federal Government, or which is designated as a Federal Public Body or institution by the law establishing it and includes Federal Government Public owned enterprises;

፲/ ‹‹**በፌደራል መንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት**›› ማለት በፌደራል መንግሥት ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፲፬/፪ሺ፲፮ ወይም በሌላ ማቋቋሚያ ሕግ መሰረት የተቋቋመ ሆኖ ሙሉ በሙሉ በፌደራል መንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት ነው፤

፲፩/ ‹‹**የመንግሥት ገንዘብ**›› ማለት እንደአግባብነቱ ከፌደራል መንግሥት ግምጃ ቤት ወይም የፌደራል መንግሥት ካገኘው የውጭ እርዳታ እና ብድር ለመንግሥት መሥሪያ ቤት የተመደበ ገንዘብ ወይም የመሥሪያ ቤቱ የውስጥ ገቢ ሲሆን በፌደራል መንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት ገንዘብን ይጨምራል፤

፲፪/ ‹‹**የመንግሥት ግዥ**›› ማለት የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የመንግሥት ገንዘብን በመጠቀም የሚያከናውኑት ግዥ ነው፤

፲፫/ ‹‹**ጨረታ**›› ማለት የግዥ ወይም የንብረት ሽያጭ ማስታወቂያ ይፋ ከሆነበት ወይም ጥሪ ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ አሸናፊው ተለይቶ ውል እስኪፈረም ድረስ ያለው የግዥ አፈፃጸም ወይም የንብረት ሽያጭ ሂደት ነው፤

፲፬/ ‹‹**ተወዳዳሪ**›› ማለት በመንግሥት ግዥ ወይም በንብረት ሽያጭ ላይ እንዲሳተፍ የተጋበዘ ወይም በጨረታ ለመሳተፍ ፍላጎት ያሳየ ሰው ነው፤

፲፭/ ‹‹**ተጫራች**›› ማለት የመጫረቻ ሰነድ ያቀረበ ሰው ነው፤

፲፮/ ‹‹**አቅራቢ**›› ማለት ለመንግሥት መሥሪያ ቤት ዕቃ ለማቅረብ፣ ከምክር ውጭ የሆነ አገልግሎት ወይም የምክር አገልግሎት ለመስጠት ወይም የግንባታ ዘርፍ ሥራን ለማከናወን ውል የገባ ሰው ነው፤

10/ “**Federal Governement-Owned Enterprise**” means a wholly Government owned enterprise established pursuant to the Federal Government-Owned Enterprises Proclamation No.1314/2024 or other establishing law;

11/ “**Public Fund**” means any monetary resource appropriated to a Public Body from the Federal Government treasury or aid grants or credits obtained from foreign or domestic sources and put at the disposal of the Public Body through the Federal Government or internal revenue of the Public Body, and includes any monetary resource of a Public Enterprise;

12/ “**Public Procurement**” means procurement executed by public bodies by using public fund;

13/ “**Bid**” means the process that extends from advertisement of or invitation to bid up to awarding and signing of contract for procurement or disposal of property;

14/ “**Candidate**” means a person invited to take part in public procurement or sale of disposable property or showing interest to participate in a bid for such procurement or sale;

15/ “**Bidder**” means a person submitting a bid document;

16/ “**Supplier**” means a person under contract with a Public Body to supply good, to render non-consultancy service or consultancy service or to perform works;

፲፯/ ‹‹**የግዥ ወይም የንብረት አስተዳደር ሙያተኛ**›› ማለት በዚህ አዋጅ እና ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጡ ሕጎች መሰረት በግዥና ንብረት አስተዳደር ሙያተኞች ዝርዝር ውስጥ የተመዘገበ ወይም የብቃት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው ነው፤

፲፰/ ‹‹**የጨረታ ሰነድ**›› ማለት በመደበኛ የጨረታ ሰነድ ላይ በመመስረት በመንግሥት መሥሪያ ቤት የሚዘጋጅ ዝርዝር የግዥ ፍላጎት መግለጫን ወይም በጨረታ የሚሸጡ ንብረቶችን ዓይነት እና ያሉበትን ሁኔታ እንዲሁም የመወዳደሪያ መስፈርቶችን የያዘ ሰነድ ነው፤

፲፱/ ‹‹**መደበኛ የጨረታ ሰነድ**›› ማለት የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች አጠቃላይ ይዘቱ አንድ ወጥ የሆነ ወይም ተመሳሳይ የሆነ የጨረታ ሰነድ በቀላሉ ማዘጋጀት እንዲችሉ የሚረዳ በባለስልጣኑ የሚዘጋጅ ሰነድ ሲሆን፣ ለዲዛይን እና ግንባታ፣ ለኮንስትራክሽን ማኔጅመንት፣ ለተርንኪ እና ለመሳሳሉ ውሎች የሚያገለግሉ ሰነዶችን ያካትታል፤

፳/ ‹‹**የመጫረቻ ሰነድ**›› ማለት የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ያዘጋጀውን የጨረታ ሰነድ መሰረት በማድረግ ተጫራች በግዥው ወይም በሽያጩ ለመሳተፍ የሚያቀርበው የመወዳደሪያ ሀሳብ የያዘ ሰነድ ነው፤

፳፩/ ‹‹**ስትራቴጂያዊ ግዥ**›› ማለት በሚኒስቴሩ ሀገራዊ ጠቀሜታ ያላቸው በመሆኑ ምክንያት በውሳኔ በጥቅል የሚፈጸሙ ግዥዎች ናቸው፤

፳፪/ ‹‹**የማዕከል ግዥ**›› ማለት የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ያሏቸውን ተመሳሳይ የግዥ ፍላጎቶች በማጠቃለል ከሌሎች መካከል ለዚህ ዓላማ በተቋቋመ አካል በማዕከል የሚፈፀም ግዥ ነው፤

17/ "**Procurement or Property Administration Professional**" means a person registered in the procurement and property administration professional list or certified by the Authority in accordance with this Proclamation and subsidiary laws enacted to implement this Proclamation.

18/ "**Bid Document**" means a document prepared by a Public Body in accordance with the standard bid document containing detailed specification of the desired object of procurement or the type and condition of the property disposable by sale and the evaluation criteria;

19/ "**Standard Bid Document**" means a document prepared by the Authority to facilitate the preparation of consistent or uniform bid document by public bodies, and includes documents that apply to design and build, construction management, turnkey and other similar contracts;

20/ "**Bid Proposal**" means a document submitted by a bidder to participate in a bid on the basis of a bid document prepared by a Public Body in respect of a procurement or sale of disposable property;

21/ "**Strategic Procurement**" means a procurement carried out in bulk by a decision of the Ministry on account of the national significance of that procurement;

22/ "**Central Procurement**" means a collective procurement of similar items of common use to public bodies, carried out by a Public Body established, inter alia, for this purpose;

፳፫/ ‹‹**የማዕቀፍ ስምምነት**›› ማለት የረጅም ጊዜ አቅርቦትን ወይም ንብረት ማስወገድን ታሳቢ በማድረግ ወደፊት በሚፈጸም ዝርዝር ውል ለሚከናወን አቅርቦት ወይም ንብረት ለማስወገድ መሠረት በመሆን የሚያገለግል፣ በነጠላ ዋጋ እና ሌሎች የውል ሁኔታዎች ላይ በመመስረት የሚፈፀም አጠቃላይ የሆነ ስምምነት ነው፤

፳፬/ ‹‹**የማዕቀፍ ስምምነት አቅራቢ**›› ማለት በማዕቀፍ ስምምነት ዕቃ ወይም ከምክር ውጭ የሆነ አገልግሎት ለማቅረብ ውል የገባ አቅራቢ ነው፤

፳፭/ ‹‹**የመንግሥት ንብረት**›› ማለት ከመንግሥት ገንዘብ እና መሬት በስተቀር የፌደራል መንግሥት ሀብት የሆነ ማንኛውም ንብረት ነው፤

፳፮/ ‹‹**ቋሚ ንብረት**›› ማለት ግዙፋዊ ህልዎት ያለው፣ የተናጠል ዋጋው በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው መመሪያ የሚወሰን ሆኖ ገቢ ከተደረገበት ጊዜ አንስቶ ከአንድ ዓመት በላይ ለሆነ ጊዜ አገልግሎት የሚሰጥ ንብረት ነው፤

፳፯/ ‹‹**ልዩ ቋሚ ንብረት**›› ማለት ዋጋው ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ለቋሚ ዕቃ ከተወሰነው ዋጋ ያነሰ ሆኖ ገቢ ከተደረገበት ጊዜ አንስቶ ከአንድ ዓመት በላይ አገልግሎት የሚሰጥ ማንኛውም ዕቃ ነው፤

፳፰/ ‹‹**አላቂ ንብረት**›› ማለት ከቋሚ ንብረት እና ከልዩ ቋሚ ንብረት ውጪ የሆነ ማናቸውም ንብረት ነው፤

23/ "**Framework Agreement**" means an umbrella agreement for long term supply or disposal of property establishing unit price and other terms and conditions of contract, which serves as basis for supplies to be delivered or property to be disposed off under future specific contract;

24/ "**Framework Contract Supplier**" means a supplier who has entered into a contractual obligation to supply goods or services under a framework contract;

25/ "**Public Property**" means any property of the Federal Government other than public money and land;

26/ "**Fixed Asset**" means tangible asset the value of which is determined by a Directive to be issued hereunder, that has a useful economic life of more than one year from the date of its receipt ;

27/ "**Special Fixed Asset**" means any tangible asset the value of which is below the minimum threshold determined for fixed asset by the Directive to be issued hereunder, that has a useful economic life of more than one year from the date of its receipt;

28/ **Supplies**" means any tangible asset other than fixed asset but does not include special fixed asset;

፳፱/ ‹‹**የህይወት ዘመን ሥርዓት**›› ማለት ከመንግሥት ንብረት ጋር የተያያዙ ተግባሮች እና ወጪዎችን የማቀድ፣ የመያዝ፣ የመረከብ፣ የመጠቀም፣ የጥገና፣ የፍጆታ ወይም የማስወገድ ወይም ከመዝገብ የመሰረዝ ተግባራትን ያካተተና የመንግሥት ንብረት አስተዳደር እና ቁጥጥር ብቃት ባለው መንገድ እንዲመራ ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓት ነው፤

፴/ ‹‹**የህይወት ዘመን ወጪ ትንተና**›› ማለት የግዥውን መነሻ ዋጋ እና ንብረቱ አገልግሎት ላይ በሚውልበት፣ እንዲሁም እንደሁኔታው በሚወገድበት ጊዜ የሚያስከትለውን ኢኮኖሚያዊ፣ ከባቢያዊ እና ማህበራዊ ወጪ የሚያካትት ትንተና ነው፤

፴፩/ ‹‹**ማስወገድ**›› ማለት የመንግሥትን ንብረት በሽያጭ፣ ለሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት በማዛወር፣ በስጦታ ለሌላ አካል በማስተላለፍ፣ በማምከን፣ በማፌን፣ በመቀየጥ፣ በመቅበር ወይም በማቃጠል ከንብረት መዝገብ የመሰረዝ ተግባር ነው፤

፴፪/ ‹‹**የውል አስተዳደር**›› ማለት የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ከአቅራቢው ወይም ከሚወገድ ንብረት ገዥው ጋር ባሰረው ውል ላይ የተቀመጡ ግዴታዎች በአግባቡ መፈጸማቸውን ለማረጋገጥ የሚከናወኑ የክፍያን፣ በወቅቱ የማስረከብን፣ የውል ማሻሻል፣ የዋጋ ማስተካከያ፣ የጥራትና መጠን ፍተሻን፣ የውል አለመግባባቶችን መፍታትን፣ ውል የማጠናቀቅ እና ሌሎች የውል አፈፃፀም ክትትልና ቁጥጥር ተግባራትን ይጨምራል፤

29/ “**Life-Time Approach**” means a system of effective management and control of public property which involves all associated activities and costs, namely, planning, acquisition, receipt, use, maintenance, consumption or disposal or write off of public property;

30/ “**Life Cycle Cost Analysis**” means the analysis involving the economic, environmental and social cost arising from the acquisition, use and where applicable, the disposal of a property during its life time;

31/ “**Disposal**” means the act of writing off public property by sale or by transferring to another Public Body or by donating to another entity or byneutralizing, suppressing, diluting, burying or burning;

32/ “**Contract Administration**” means the act of ensuring that the obligations under a contract between a Public Body and a supplier or a buyer of disposable Property are duly performed which involves tasks of payment, timely delivery, contract amendment, price adjustment, quality and quantity inspection , resolution of contractual disputes, contract completion and other activities of monitoring and evaluation of contract performance;

፴፫/ ‹‹**የኤሌክትሮኒክ ሥርዓት**›› ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፯ ንዑስ አንቀጽ(፩) መሰረት የተዘረጋውን የኤሌክትሮኒክ ዘዴን በመጠቀም የመንግሥት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር ተግባራት የሚከናወንበት ሥርዓት ነው፤

፴፬/ ‹‹**የጥፋተኝነት ሪፖርት**›› ማለት በግዥ ወይም የሚወገድ ንብረት ሽያጭ ጨረታ ሂደት ወይም በውል አፈፃፀም ሕጉን ያልጠበቀ ወይም የመሥሪያ ቤቱን ጥቅም የሚጎዳ ድርጊት ወይም መታቀብ በፈፀመ ተጫራች ወይም አቅራቢ ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ እንዲወሰድ የመንግሥት መስሪያ ቤት ለባለሥልጣኑ የሚያቀርበው ሪፖርት ነው፤

፴፭/ ‹‹**ሚኒስቴር**›› ወይም ‹‹**ሚኒስትር**›› ማለት እንደቅደምተከተሉ የገንዘብ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

፴፮/ ‹‹**ባለስልጣን**›› ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፱ መሰረት እንደገና የተቋቋመው የፌደራል መንግሥት የግዥና ንብረት ባለስልጣን ነው፤

፴፯/ ‹‹**ቦርድ**›› ማለት በመንግሥት መስሪያ ቤቶች የግዥ አፈጻጸም እና የንብረት አወጋገድ ሂደት ላይ በተወዳዳሪዎች ወይም በተጫራቾች የሚቀርብለትን ይግባኝ መርምሮ ውሳኔ እንዲሰጥ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፯ መሰረት እንደገና የተቋቋመ አካል ነው፤

፴፰/ ‹‹**አቤቱታ**›› ማለት ጨረታውን ያወጣው የመንግሥት መሥሪያ ቤት በዚህ አዋጅ ወይም በመንግሥትና የግል አጋርነት አዋጅ ወይም በአፈጻጸም መመሪያዎች የተመለከተውን ባለመፈጸሙ ምክንያት ጉዳት ወይም በደል ደርሶብኛል ወይም ሊያደርስብኝ ይችላል የሚል ተወዳዳሪ ወይም ተጫራች ለመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ የሚያቀርበው ቅሬታ ነው፤

33/ "**Electronic System**" means a system by which activities pertaining to public procurement and property administration are carried out by means of electronic system established pursuant to Sub-Article (1) of Article 27 of this Proclamation;

34/ **“Report of Default”** means report filed with the Authority by a Public Body for administrative measure against a bidder or a supplier who has committed or omitted an act in a bid process or in the performance of a contract for procurement or sale of disposable property, which is unlawful or prejudicial to the interest of the Public Body

35/ “**Ministry**” or “**Minister**” means the Ministry or the Minister of Finance respectively;

36/ “**Authority**” means the Federal Public Procurement and Property Authority re-established under Article 9 of this Proclamation;

37/ “**Board**” means an entity re-established under Article 67 of this Proclamation to review and decide on appeal from candidates or bidders in regard to the conduct of public procurement or sale of disposable property of public bodies;

38/ **“Complaint”** means petition submitted at first instance to the head of a Public Body by a bidder or candidate who claims to have sustained or that he is likely to sustain damage or who is aggrieved because of an action or inaction of the Public Body that is inconsistent with this Proclamation, the Public Private Partnership Proclamation or

፴፱/ ‹‹**ይግባኝ**›› ማለት ግዥውን በሚፈፅመው ወይም ንብረቱን በሽያጭ በሚያስወግደው የመንግሥት መስሪያ ቤት ሳይከናወን የቀረው የሕግ ጥሰት አለበት ብሎ የሚያምን ተወዳዳሪ ወይም ተጫራች ጉዳዩ ተመርምሮ ውሳኔ እንዲሰጥበት ለቦርዱ የሚያቀርበው ቅሬታ ወይም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፹፩ እና አንቀጽ ፹፭ መሰረት ለመደበኛ ፍርድ ቤት የሚቀርብ ቅሬታ ነው፤

፵/ ‹‹**የተርንኪ ግዥ**›› ማለት የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በተናጠል ሊፈፀሙ የሚችሉ የአንድ ፕሮጀክት አካል የሆኑ ግዥዎችን በማቀናጀት በአንድ ጨረታ የሚፈፅሙበት የግዥ ሥልት ነው፤

፵፩/ ‹‹**ልዩ አስተያየት**›› ማለት በመንግሥት የግዥ ሂደት ለሀገር ውስጥ ምርቶች፣ ለኢትዮጵያውያን ከምክር ውጭ የሆነ አገልግሎት ሰጪዎች፣ አማካሪዎች፣ ሥራ ተቋራጮች፣ እና ልዩ ትኩረት ለሚሹ የሥራ ዕድል ፈጠራ ተቋማት በውድድር ወቅት የሚሰጥ የተለየ ድጋፍ ነው፡፡

፵፪/ ‹‹**የተጨማሪ እሴት**›› ማለት አንድ የሀገር ውስጥ ምርት ለገበያ ከመቅረቡ በፊት በምርቱ ላይ በሀገር ውስጥ የታከለው ተጨማሪ ኢኮኖሚያዊ እሴት ነው፡፡

፵፫/ ‹‹**ሰው**›› ማለት የተፈጥሮ ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

፵፬/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

the Directives issued thereunder, as the case may be, in connection with the execution of procurement or sale of disposable property for which the Public Body has invited bids, for correction of the proceeding ;

39/ **“Appeal”** means a petition submitted to the Board or to a court of law pursuant to Article 81 and Article 85 of this Proclamation for a review by a candidate or a bidder against an act or an omission of the Public Body in regard to the conduct of public procurement or sale of disposable property where he believes that such an act or an omission violates this Proclamation;

40/ **“Turnkey Procurement”** means a procurement approach where by Public Bodies carryout procurements of components in a project under a single tender, which would otherwise be procured separately;

41/ **“Preference Margin”** means a preference given to local goods, non- consultancy service providers, consultants, contractors of Ethiopian nationals and job creation institutions in the evaluation of bid;

42/ **“Value Addition”** means a local content economic addition on a locally produced good before the good is supplied to the market;

43/ **“Person”** means any natural or juridical person;

44/ Any expression in the masculine gender includes the feminine.

**፫. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>**

፩/ ይህ አዋጅ በማናቸውም የፌደራል የመንግሥት መሥሪያ ቤት የግዥ እና የንብረት አስተዳደር ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው ቢኖርም የፌደራል መንግሥት ከአንድ ወይም ከአንድ በላይ ከሆኑ የሌሎች ሀገር መንግሥታት ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር ካደረገው ወይም ከሚያደርገው ስምምነት ወይም ከስምምነቱ ከመነጨ ግዴታ ጋር የማይጣጣም ከሆነ በስምምነቱ የተመለከተው ግዴታ ተፈፃሚ ይሆናል።

**፬. <u>መርሆች</u>**

የመንግሥት ግዥ አፈፃጸም እና የንብረት አስተዳደር የሚከተሉትን መርሆች መሰረት ማድረግ ይኖርበታል፡-

፩/ የመንግሥት ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም ማስገኘት፤

፪/ በዚህ አዋጅ በተፈቀደው ልዩ አስተያየት ካልሆነ በስተቀር በተወዳዳሪዎች እና ተጫራቾች መካከል አድሎዎ አለማድረግ፤

፫/ ማናቸውም የግዥ አፈጻጸምና የንብረት አወጋገድ ውሳኔ የሚሰጥበት መስፈርት እና እያንዳንዱ የግዥና የንብረት አወጋገድ ሂደት ላይ የሚሰጠው ውሳኔ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ሁሉ ግልጽ እና ፍትሐዊ እንዲሆን ማድረግ፤

፬/ ማንኛውም የመንግሥት ግዥ በሚፈጸምበት እና ንብረት በሚወገድበት ወቅት በአካባቢ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የማያስከትል፣ እንዲሁም የህይወት ዘመን ወጪ ትንተናን ከግምት ያስገባ እና መልሶ መጠቀምን የሚያበረታታ መሆኑን ማረጋገጥ፤

**3. <u>Scope of Application</u>**

1/ This Proclamation shall apply to procurement and property administration of any Federal Public Body.

2/ Notwithstanding the provision of Sub-Article (1) of this Article, to the extent that this Proclamation conflicts with an obligation of the Federal Government under or arising out of an agreement with one or more other states or with an international organization, the provisions of that agreement shall prevail.

**4. <u>Principles</u>**

The conduct of public procurement and property administration shall comply with the following principles:

1/ Value for money in the use of public fund;

2/ Non-discrimination among candidates and bidders except in cases of preference specifically provided for in this Proclamation;

3/ Transparency and fairness of the criteria on the basis of which decisions are given in public procurement and property disposal as a whole, as well as of decisions in the conduct of each specific case of procurement and property disposal to all concerned;

4/ Ensuring that any process of public procurement or property disposal has not any harmful impact on the environment, takes into consideration life cycle cost analysis and promotes recycling;

፭/ የግዥ አፈጻጸምና ንብረት አወጋገድ ሂደቶች ቀልጣፋ፣ ውጤታማ እና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ የተፈጸሙ መሆኑን ማረጋገጥ፤

፮/ የግዥ አፈጻጸምና የንብረት አስተዳደር ተግባራትን በታማኝነት መፈጸም፤

፯/ በመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ላይ የተሰጡ ውሣኔዎች እና የተወሰዱ እርምጃዎች ተጠያቂነት የሚያስከትሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤

፰/ የቴክኖሎጂ ፈጠራን ማበረታታት፡፡

## ምዕራፍ ሁለት
## ተግባርና ኃላፊነት

### ፭. የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ ተግባር እና ኃላፊነት

የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነቶች በዚህ አዋጅ መሰረት በሚወጡ መመሪያዎች የሚወሰን ሆኖ የሚከተሉት አጠቃላይ ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

፩/ በመሥሪያ ቤቱ የሚፈጸሙ ግዥዎች እና የንብረት አስተዳደር ተግባራት የኤሌክትሮኒክ ሥርዓት ተከትሎ በዕቅድ የተመሰረቱ እና በዚህ አዋጅ የተመለከቱ የግዥ እና የንብረት አስተዳደር መርሆችን በጠበቀ መንገድ መተግበራቸውን የማረጋገጥ፤

፪/ በአዋጁ አንቀጽ ፲፪ ንዑስ አንቀጽ (፲፰) የተደነገገውን የግዥና ንብረት ሙያተኞች ምዝገባና የምስክር ወረቀት አሰጣጥ ትግበራን መሰረት አድርጎ በተገቢው የግዥና ንብረት አስተዳደር ሙያተኞች የተሟሉ እና የግዥና ንብረት አስተዳደር የሥራ ተግባራትን የሚያከናውኑ የሥራ ክፍሎችን የማደራጀት፤

5/ Ensuring that the processes of procurement and property disposal are executed in an efficient, effective and economic manner;

6/ Carryout functions of procurement and property administration with integrity;

7/ Accountability for decision made and measures taken in regard to public procurement and property administration;

8/ Promoting technological innovations.

## CHAPTER TWO
## DUTIES AND RESPONSIBILITIES

### 5. Duties and Responsibilities of Heads of Public Bodies

With the details to be specified in the Directives to be issued hereunder, the head of a Public Body shall have the following general duties and responsibilities:

1/ Ensure that the procurements and property administration activities of the Public Body are plan based using the electronic system and carried out in conformity with the principles laid down in this Proclamation;

2/ Establish unit in charge of procurement and property disposal activities of the Public Body which is adequately staffed with procurement and property administration professionals, in compliance with the implementation of Procurement and Property Professionals Registration and Certification pursuant to Sub-Article (18) of Article 12 of this Proclamation;

፫/ ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቁ የመሥሪያ ቤቱ የፕሮጀክት ግዥዎች ከመፈጸማቸው አስቀድሞ የግዥ ፕሮጀክት ስትራቴጂ የተዘጋጀላቸው መሆኑን የማረጋገጥ፤

፬/ መሥሪያ ቤቱ የሚኖረውን የግዥና ንብረት አስተዳደር ተግባራት ባህርይ ከግምት በማስገባት እንደ አስፈላጊነቱ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የግዥ እና የሚወገዱ ንብረቶች ሽያጭ አጽዳቂ ኮሚቴ የማቋቋም፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ውስብስብ ለሆኑ ግዥዎች ጊዜያዊ የግዥ ገምጋሚ ኮሚቴ፣ እንዲሁም የንብረት ዋጋ ገማች ኮሚቴ የማቋቋም፤

፭/ በግዥ እና በንብረት አስተዳደር ሥራ ላይ የሚመደቡ ወይም የተመደቡ የግዥ እና የንብረት አስተዳደር ሙያተኞች፣ ሰራተኞች እና ኃላፊዎች እንዲሁም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፬ መሰረት የሚቋቋሙ ኮሚቴዎች አባላት ይህንን አዋጅ፣ የአፈፃጸም መመሪያዎችን፣ የግዥ እና የንብረት አስተዳደር ማንዋሎችን፣ መደበኛ የጨረታ ሰነዶችን፣ የኤሌክትሮኒክ ሥርዓት አጠቃቀም እንዲያውቁ ማድረግ የሚያስችል ስልጠና ማግኘታቸው እና የመንግሥት ግዥ እና ንብረት አስተዳደርን ለመፈጸም በቂ እውቀት እና ክህሎት ያላቸው መሆኑን የማረጋገጥ፤

3/ Ensure that a strategy for large procurements pertaining to projects implemented by the Public Body is in place before such procurements are carried out;

4/ Setup one, or where the nature of the procurement and property administration activities of the Public Body so require, more than one procurement and property disposal endorsing committee, and in respect of complex procurements ad-hoc bid evaluation committee and disposable property valuation committee as may be necessary;

5/ Ensure that procurement and Property professionals, staff and officials assigned in the procurement and property administration units and members of the committees established pursuant to Sub Article 4 of this Article receive training to enable them acquire knowledge of the content and application of this Proclamation, the Directives to be issued hereunder, the procurement and property administration manuals, the standard bid documents, the application of the electronic system and other relevant forms and have adequate knowledge and skill to perform the functions of procurement and property administration;

፮/ በመሥሪያ ቤቱ በተከናወነ የግዥ እና የንብረት አስተዳደር ኦዲት የተለዩ የአሰራር ግድፈቶች የእርምት እርምጃ እንዲወሰድባቸው የማድረግ እና የአፈጻጸም ሂደቱን አስመልክቶ ለሚመለከታቸው አካላት ሪፖርት መላኩን የማረጋገጥ፤

፯/ መሥሪያ ቤቱ ባለው አደረጃጀት ምክንያት የተለያዩ ማዕከላት ያለው ሲሆንና ስራዎችን በአግባቡ ለመወጣት ያመቻል ብሎ ሲያምን ማዕከላቱን በበላይነት ለሚመሩ ኃላፊዎች ከግዥ ዕቅድ ዝግጅት ውጭ ያሉ የግዥ እና የንብረት አስተዳደር ስራዎችን እንዲመሩ፣ እንዲያስፈጽሙ ውክልና የመስጠት፤

፰/ በአጽዳቂ ኮሚቴ መጽደቅ የማያስፈልጋቸውን ግ ዥ እ ና የሚወገዱ ንብረቶች ሽያጭ እንዲያጸድቅ ለግዥ እና ንብረት አስተዳደር ተግባራትን ለሚያከናውነው የሥራ ክፍል ውክልና የመስጠት፤

፱/ የቀጥታ ግዥ ዘዴን ለመጠቀም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፬ ላይ የተቀመጡ ሁኔታዎች ሲሟሉና ግዥውን በቀጥታ መፈፀም ለመሥሪያ ቤቱ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ የሚያስገኝ መሆኑን ሲያምን ግዥው በቀጥታ እንዲፈፀም የመወሰን፤

፲/ በዚህ አዋጅ እና ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጡ ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያዎች መሠረት የግዥ ዕቅድ፣ የግዥ አፈፃፀም፣ የተሽከርካሪና ነዳጅ አጠቃቀም እንዲሁም ሌሎች ለባለሥልጣኑ መቅረብ ያለባቸው ሪፖርቶች በኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ መሰረት ወቅቱን ጠብቀው መቅረባቸውን የማረጋገጥ፤

6/ Cause corrective measures to be taken on audit findings of irregularities in the conduct of procurement and property administration and ensure that reports on such measures are submitted to the appropriate bodies;

7/ Where a Public Body is organized in such a way that it has cost centers under it, and the head of that Public Body considers it to be conducive to efficiency, delegate to the heads of such cost centers the duty to carry out the whole range of procurement and property administration activities except procurement plan;

8/ Delegate to the procurement and property disposal unit the responsibility of endorsing procurements that do not need endorsement by the procurement endorsing committee;

9/ Where the conditions for using direct procurement method listed under Article 34 of this Proclamation are satisfied and the head of the Public Body is convinced that using this method in respect of the procurement is economically beneficial to the Public Body, authorize direct procurement;

10/ Ensure the timely submission of procurement plan and reports on the execution of procurement, utilization of vehicles and fuel, and on other matters that have to be reported to the Authority using the electronic system;

፲፩/ በመሥሪያ ቤቱ የሚገኝ የመንግሥት ንብረት ተገቢው ጥበቃ እና እንክብካቤ የሚደረግለት እንዲሁም የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት የተዘረጋለት መሆኑን የማረጋገጥ፤

፲፪/ የግዥና የንብረት አስተዳደር የሥራ ክፍሎች፣ የግዥና የሚወገዱ ንብረቶች አፀዳቂ ኮሚቴ እና ሌሎች ግዥን የመፈፀም እና ንብረትን የማስወገድ ኃላፊነት የተሰጣቸው አካላት ተግባራቸውን በተገቢው ሁኔታ መወጣታቸውን የማረጋገጥ፤

፲፫/ እንደአስፈላጊነቱ የመሥሪያ ቤቱን የግዥ አፈፃፀም እና የንብረት አስተዳደር ተግባራት በሙሉ ወይም በከፊል በሦስተኛ ወገን የማሰራት፤

፲፬/ መሥሪያ ቤቱ በሚፈፅመው ግዥ እና በንብረት ማስወገድ ሂደት ላይ ለሚቀርብ አቤቱታ አጣርቶ ምላሽ መስጠት፣ እንዲሁም በቦርድ የሚተላለፍ ውሳኔን ተፈፃሚ የማድረግና ስለአፈፃፀሙ ለቦርዱ ሪፖርት የማቅረብ፤

፲፭/በግዥ እና የሚወገድ ንብረት ሽያጭ ሂደት ይፋ መደረግ ያለባቸው መረጃዎች ወቅቱን ጠብቀው በኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ እና በሌሎች አግባብነት ባላቸው ዘዴዎች ለሕዝብ ይፋ መደረጋቸውን የማረጋገጥ፡፡

**፮. <u>የግዥ እና የንብረት አስተዳደር የሥራ ክፍሎች ተግባርና ኃላፊነት</u>**

በመንግሥት መሥሪያ ቤት ውስጥ የሚቋቋሙት የግዥ እና የንብረት አስተዳደር የሥራ ክፍሎች የሚኖሯቸው ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነት በዚህ አዋጅ መሰረት በሚወጡ መመሪያዎች የሚወሰኑ ሆነው የሚከተሉት አጠቃላይ ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሯቸዋል፡-

11/ Ensure that property at the disposal of the Public Body is properly handled and taken care of, and that a track and trace system is in place in respect of such property;

12/ Ensure that the procurement and property administration unit, the procurement and property disposal endorsing committee and other sections of the Public Body involved in procurement and property disposal discharge their duties properly;

13/ Where necessary, outsource in whole or in part, the procurement and property administration activities of the Public Body;

14/ Investigate and give decisions on complaints brought against the Public Body in the conduct of procurement and property disposal, execute any decision of the Board and submit report on the execution of such decision to the Secretariat of the Board;

15/ Ensure the timely dissemination of information that shall be disclosed to the public in the process of execution of procurement and sale of disposable property using the electronic system or by means of any other appropriate method of communication.

**6. <u>Duties and Responsibilities of Procurement and Property Administration Units</u>**

With the details to be specified in the procurement and property administration Directives issued hereunder, the procurement and property administration units in a Public Body shall have the following general duties and responsibilities:

፩/ የመሥሪያ ቤቱ ተግባራት ከፋይናንስ ዕቅዱ ጋር እንዲጣጣም፣ እንዲሁም ውጤታማ የሆነ የበጀት ዝግጅት ለማድረግ እንዲያመች የግዥ ዕቅድ በወቅቱና በአግባቡ ማዘጋጀትና በዕቅዱ መሰረት ግዥውን መፈጸም፤

፪/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ (፫) ላይ በተደነገገው መሰረት ከሚመለከታቸው የመሥሪያ ቤቱ የሥራ ክፍሎች ጋር በጋራ በመሆን ከፍተኛ ወጪ ለሚጠይቁ የመሥሪያ ቤቱ ግዥዎች ፕሮጀክት ስትራቴጂ ማዘጋጀት እና አፈፃፀሙን መከታተል፣

፫/ ይህንን አዋጅ፣ የአፈፃፀም መመሪያዎችን፣ መደበኛ የጨረታ ሰነዶችን እና ሌሎች የአሰራር ሰነዶችና ቅጾችን እንዲሁም የግዥና የሚወገድ ንብረት ሽያጭ ውሎችን መሠረት በማድረግ የመንግሥት ግዥን እና ንብረት አስተዳደርን በተሟላ የሙያ ሥነ-ምግባር እና ክህሎት የመፈፀም፤

፬/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፱ ንዑስ አንቀፅ (፩) መሠረት በሚቋቋመው የመንግሥት መሥሪያ ቤት ከሚወገዱ ንብረቶች ውጪ ያሉትን መወገድ ያለባቸውን የመሥሪያ ቤቱን ንብረቶች ይህንን አዋጅ፣ የንብረት አስተዳደር መመሪያውን፣ ሌሎች የአሰራር ሰነዶች እና ቅጾችን መሠረት በማድረግ አግባብነት ባለው የንብረት ማስወገጃ ዘዴ የማስወገድ፤

፭/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፱ በተደነገገው መሠረት የተሟላ የግዥ እና የንብረት አስተዳደር መረጃ በኤሌክትሮኒክ ሥርዓት የመያዝ፤

1/ Prepare the annual procurement plan of the Bublic Body properly and in due time with a view to aligning the activities of the Bublic Body with its financial plan and facilitating the task of effective budget preparation and execute the procurement in accordance with the plan;

2/ Pursuant to Sub-Article 3 of Article 5 of this Proclamation, prepare strategy for project related costly procurements of the Public Body in collaboration with other appropriate units of the Public Body and follow up its application;

3/ Carry out public procurement and property administration in an ethical and skillful manner in accordance with this Proclamation, the Directives issued hereunder, the standard bid documents, and other working documents and the forms as well ascontracts of procurement and sale of disposable property;

4/ Other than those to be disposed of by the Public Body referred to in Sub-Article (1) of Article 59 of this Proclamation, get rid of disposable property of the Public Body using the appropriate method of disposal in accordance with this Proclamation, the Directive to be issued hereunder, the property administration manual and other relevant forms;

5/ Maintain complete record of procurement and property administration of the Public Body using the electronic system in accordance with Article 19 of this Proclamation;

፮/ በመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ውስጥ ራሱን የቻለ የውል አስተዳደር የሥራ ክፍል ከሌለ የውል አስተዳደር ሥራዎችን የማከናወን፤

፯/ የአቅራቢዎችንና የሚወገድ ንብረት ገዥዎችን የውል አፈፃፀም ብቃት የሚያሳዩ መረጃዎችን በኤሌክትሮኒክ ሥርዓት መሰረት የመያዝ።

**፯. <u>የግዥ እና የሚወገዱ ንብረቶች አፅዳቂ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት</u>**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ (፬) የሚቋቋመው የግዥ እና የሚወገዱ ንብረቶች አጽዳቂ ኮሚቴ የሚኖረው ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነት ሚኒስቴሩ በሚያወጣቸው መመሪያዎች የሚወሰን ሆኖ የሚከተሉት ዋና ዋና ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖረዋል፡-

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፬ መሠረት ከሚፈፀሙ ቀጥታ ግዥዎች ውጪ፣እንዲሁም በግዥ አፈፃፀም መመሪያው ለዋጋ ማቅረቢያ ከተቀመጠው የገንዘብ መጠን በላይ የሆኑ ግዥዎች አፈፃፀምን በተመለከተ ከግዥ ሥራ ክፍል የሚቀርብለትን የውሳኔ ሀሳብ ሌሎች ይህንን አዋጅ፣ የግዥ መመሪያን፣ መደበኛ የጨረታ ሰነዶችን እንዲሁም የአሰራር ሰነዶችና ቅጾችን መሠረት በማድረግ መርምሮ ማጽደቅ፣ የአሰራር ስህተት ያለበት ከሆነ እንደሁኔታው ተገቢው ማስተካከያ እንዲደረግበት ጉዳዩን ለግዥ ክፍሉ መልሶ መላክ ወይም ሂደቱ እንዲሠረዝ መወሰን፤

6/ Discharge the functions of contract administration, where there is no distinct unit for administration of contracts in the Public Body;

7/ Maintain track records of performance of suppliers and buyers of disposable property by using the electronic system.

**7. <u>Duties and Responsibilities of Procurement and Property disposal Endorsing Committee</u>**

With the specific details to be set forth in the Directives to be issued by the Ministry, the procurement and property disposal endorsing committee to be established pursuant to Sub-Article (4) of Article 5 of this Proclamation shall have the following duties and responsibilities:

1/ Other than direct procurements executed in accordance with Article 34 of this Proclamation and procurements of small value falling within the threshold to be fixed in the Directive issued hereunder and executed by means of request for quotation, review and endorse procurements on the basis of the result of the evaluation of bids conducted by procurement unit and in accordance with this Proclamation, the Directive issued hereunder, the standard bid documents and other working documents and forms, or where the committee finds flaw in the conduct of the procurement, send the case back to the procurement unit for the appropriate correction or decide to cancel the proceeding;

፪/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፱ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት በሚቋቋመው የመንግሥት መሥሪያ ቤት ከሚወገዱ ንብረቶች በስተቀር ከንብረት አስተዳደር የሥራ ክፍል በሚቀርብለት የውሳኔ ሀሳብ መሰረት የመንግሥት መሥሪያ ቤቱን የሚወገዱ ንብረቶች ሽያጭ ይህንን አዋጅ፣ የንብረት አስተዳደር መመሪያን፣ እንዲሁም ሌሎች የአሠራር ሰነዶችና ቅጾችን መሠረት በማድረግ መርምሮ ማጽደቅ፣ የአሰራር ስህተት ያለበት ከሆነ እንደሁኔታው ተገቢው ማስተካከያ እንዲደረግበት ጉዳዩን ለንብረት አስተዳደር ክፍሉ መልሶ መላክ ወይም ሂደቱ እንዲሰረዝ መወሰን፤

፫/ የመንግሥት ግዥን እና ንብረት አወጋገድን ውጤታማ ለማድረግ በሚያስችሉ ዘዴዎች ላይ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱን የበላይ ኃላፊ ማማከር፤

፬/ በመሥሪያ ቤቱ የሥራ ክፍል የሚዘጋጀውን ዓመታዊ የግዥ እና የንብረት ማስወገድ ዕቅድ በመመርመር ለመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ አስተያየት ማቅረብ፤

፭/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም በሥራ ባህሪያቸው ምክንያት በሥራ አመራር ቦርድ ለሚተዳደሩ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ግዥው በመሥሪያ ቤቶቹ የስራ አመራር ቦርድ እንዲጸድቅ ሚኒስትሩ በልዩ ሁኔታ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

2/ Other than property to be disposed of by the Public Body referred to in Sub Article (1) of Article 59 of this Proclamation, review and endorse sale of disposable property of the Public Body on the basis of the result of the evaluation of bids conducted by property administration unit and in accordance with this Proclamation, the Directive issued hereunder, the standard bid documents and other working documents and forms, or where the committee finds flaw in the conduct of the sale, send the case back to the property administration unit for the appropriate correction or cancel the proceeding;

3/ Advise the head of the Public Body on ways of achieving efficient procurement and property administration;

4/ Review the annual procurement and property disposal plan prepared by the Public Body's unit and deliver its opinion thereon to the head of the Public Body;

5/ Notwithstanding the provision of Sub-Article (1) of this Article, the Minister may, under special circumstance, authorize the large procurement of certain Public Bodies to be endorsed by their management Board.

**፰. ተጠያቂነት**

የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ፣ የመንግሥት የግዥ እና የንብረት አስተዳደር የሥራ ክፍሎችን የሚመሩ ኃላፊዎች፣ ለግዥ እና ንብረት አስተዳደር ሥራ የተመደቡ ሠራተኞች፣ ባለሙያዎች፣ እንዲሁም የግዥ አጽዳቂ እና የንብረት አስወጋጅ እና ሌሎች ኮሚቴዎች አባላት ስለሚወስዷቸው ይህንን አዋጅ እና በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጡ መመሪያዎችን ያልጠበቁ እርምጃዎች ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡

**8. Accountability**

Heads of Public Bodies, heads of procurement and property administration units and staff thereof as well as members of the procurement endorsing and property disposing and other committees in Public Bodies shall be accountable for their action that is inconsistent with this Proclamation and the Directives issued hereunder.

## ምዕራፍ ሦስት
## የመንግሥት የግዥ እና ንብረት ባለሥልጣን

**፱. መቋቋም**

፩/ የመንግሥት የግዥ እና ንብረት ባለሥልጣን (ከዚህ በኋላ “ባለሥልጣኑ” እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለና የሕግ ሰውነት ያለው የፌደራል የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ እንደገና ተቋቁሟል፡፡

፪/ ባለሥልጣኑ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል፡፡

**፲. ዋና መሥሪያ ቤት**

የባለሥልጣኑ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች ሊኖሩት ይችላል፡፡

**፲፩. የባለሥልጣኑ ዓላማ**

የባለሥልጣኑ ዓላማ አስፈላጊውን አቅም በመገንባት፣ የመንግሥት ግዥ አፈፃፀም እና ንብረት አስተዳደር የዚህን አዋጅና በአዋጁ መሠረት የወጡትን መመሪያዎች የጠበቀ መሆኑን ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ማረጋገጥ እንዲሁም የግዥና ንብረት አስተዳደር ሥርዓቱን ለማሻሻል ለሚቀርብ ሀሳብ መሠረት የሚሆኑ የጥናት ሥራዎችን በማከናወን ዘላቂ የሆነ፣ ውጤታማና ቀልጣፋ የመንግሥት ግዥና ንብረት

## CHAPTER THREE
## THE PUBLIC PROCUREMENT AND PROPERTY REGULATORY AUTHORITY

**9. Establishment**

1/ The Public Procurement and Property Authority (hereinafter referred to as the "Authority") is hereby re-established as an autonomous Federal Government Public Body having its own legal personality.

2/ The Authority shall be accountable to the Minister.

**10. Head Office**

The head office of the Authority shall be in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere as may be necessary.

**11. Objective of the Authority**

The objective of the Authority is to achieve sustainably effective and efficient procurement and property administration by creating the requisite capability, ensuring adherence of the conduct of procurement and property disposal to the provisions of this Proclamation and the Directives issued hereunder through regular supervision and follow up and by conducting study that

አስተዳደርን ማሳካት ነው፡፡

provides the basis for proposal on improving the procurement and property administration system.

**፲፪. <u>የባለሥልጣኑ ሥልጣን እና ተግባር</u>**

ባለስልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ በመንግሥት የግዥና የንብረት አስተዳደር ፖሊሲዎች፣ መርሆችና አፈፃፀም ላይ የፌደራል መንግሥትን ማማከር፣ ለክልሎች እና ለከተማ መስተዳደሮች የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት፣

፪/ በመንግሥት ግዥ አፈፃፀምና ንብረት አስተዳደር ሥርዓትና አተገባበር ላይ ጥናት ማከናወን እንዲሁም በጥናቱ ላይ ተመስርቶ ሥርዓቱን ለማሻሻል የሚረዱ የማሻሻያ ሀሳቦችን ለሚኒስቴሩ ማቅረብ፣

፫/ ከመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሚቀርብለትን መረጃ መሰረት በማድረግ የመንግሥት የግዥና የንብረት አስተዳደር ሥርዓት አፈፃፀምን በሚመለከት የተጠቃለለ አመታዊ ሪፖርት ለሚኒስቴሩ ማቅረብ፣ ሚኒስቴሩ በሚጠይቀው ዝርዝር መሠረት በእያንዳንዱ መንግሥት መሥሪያ ቤት ስለተከናወነው ግዥ ዓይነት እና መጠን እንዲሁም ንብረት አስተዳደር ጉዳዮች መረጃዎችን መስጠት፣

፬/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፹፮ ንዑስ አንቀጽ (፩) ሥር የተዘረዘሩትን ኃላፊነትን ባለመወጣት የሚያስጠይቁ ጥፋቶች የፈፀመ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ተሿሚ ወይም የተመደበ ሰው ላይ አስተዳደራዊ ቅጣት እንዲወሰን ለሚኒስቴሩ ሪፖርት ማቅረብ፣

**12. <u>Powers and Duties of the Authority</u>**

The Authority shall have the powers and duties to:

1/ Advise the Federal Government on public procurement and property administration policies, principles and execution and provide technical assistance to the Regional Governments and City Administrations,

2/ Conduct research on the system of Public Procurement and Property Administration and the implementation thereof , and propose recommendations to the Ministry on the improvement of the system based on the research,

3/ Submit compiled annual report to the Ministry regarding the overall performance of the public procurement and property administration system based on information obtained from Public Bodies and provide data in such detail as the Ministry may request regarding the nature and volume of public procurement executed by each Public Body, as well as on matters of property administration,

4/ Submit to the Ministry report of default constituting failure to discharge duty under Sub-Article (1) of Article 86 of this Proclamation, against a person appointed to or employed by a Public Body for any appropriate measure of administrative penalty,

፭/ ከሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ጋር በመተባበር በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ለሚፈለጉ ተመሳሳይ ንብረቶች ደረጃ ማውጣትና የወጡት ደረጃዎች ወጥነት ባለው መንገድ ሥራ ላይ እንዲውል ማድረግ፣

፮/ የግዥና ንብረት አስተዳደር የሕግ ማዕቀፍን ሥራ ላይ ለማዋል አስፈላጊ የሆኑ መደበኛ የጨረታ ሰነዶችን ማዘጋጀት፣ ማፅደቅ፣ የግዥ ዝርዝርና ካታሎግ ልዩ ልዩ ቅፆችን፣ ማኑዋሎች እንዲሁም የግዥና ንብረት ሙያተኞች እና ኃላፊዎች ሊከተሏቸው የሚገባ የሥነ ምግባር መርሆዎችን ማዘጋጀት እና ሥራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ፣

፯/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፮ መሠረት የተዘጋጁ መረጃዎች፣ እንዲሁም በግዥ አፈፃፀም እና በንብረት አወጋገድ ሂደት ጥፋት በመፈፀማቸው ለባለሥልጣኑ በቀረቡ የጥፋተኝነት ሪፖርቶች ላይ የተሰጡ ውሣኔዎች፣ የኦዲት ውጤቶች እና ሌሎች ሕዝብ ሊያውቃቸው የሚገባ ዋና ዋና ጉዳዮችን በኤሌክትሮኒክ ሥርዓት መሠረት እና እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎች የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ለሕዝብ ይፋ ማድረግ፣

፰/ ከሚኒስቴሩ እና ሌሎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን መሥሪያ ቤቶች ካላቸው የሥራ ባህሪ በመነሳት ሊኖራቸው የሚገባውን የግዥና ንብረት አስተዳደር እና ተያያዥ ስራዎች አደረጃጀት አጥንቶ ማቅረብ፣ ተፈፃሚነቱን መከታተል፤

5/ Set standards for common user items to Public Bodies in collaboration with the appropriate Government Agencies, and ensure uniform compliance with such standards,

6/ Prepare, approve as the case may be, and issue standard bid documents, forms, manuals and procurement lists and catalog which are necessary for the implementation of the procurement and property administration legal framework, as well as the code of conduct that the procurement and property professionals and officials are required to observe,

7/ Publish the documents prepared as per Sub-Article 6 of this Article, decisions given by the Authority on reports of default submitted to it by Public Bodies against non- compliant suppliers, buyers of disposable property, bidders or candidates in the process of procurement or property disposal, audit findings and other matters that should be disclosed to the public using the electronic system or by other appropriate means of communication,

8/ In collaboration with the Ministry and other pertinent public entities, conduct studies on the organization of public procurement and property administration units and other departments in a Public Body performing related functions, taking into account the particular nature of their duties,

፱/ በመንግሥት ግዥ ወይም በሚወገድ ንብረት ሽያጭ ጨረታ ለመሳተፍ ፍላጐት ያላቸው ተወዳዳሪዎች የሚመዘገቡበትን ዘመናዊ ሥርዓት መዘርጋትና ማስተዳደር፣

፲/ የተቋም እና የሰው ኃይል አቅም ለማጎልበት የሚያስችል የአቅም ግንባታ እስትራቴጂክ ዕቅድ ማዘጋጀት እና የአቅም ግንባታ ሥልጠና መስጠት፣

፲፩/ ለመንግሥት ግዥ አፈፃፀም እና ንብረት አስተዳደር የሚያገለግል የመረጃ ቋት ማቋቋም፣ ማጐልበት፣ መጠበቅ እና ወቅታዊነቱ የተጠበቀ እንዲሁም ማድረግ፣

፲፪/ በፌዴራል እና በክልል መንግሥታት መካከል የተጣጣመ የመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ሥርዓት እንዲኖር ዕገዛ ማድረግ፣

፲፫/ የመንግሥት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር እንዲሁም የመንግሥት እና የግል አጋርነት ዘርፍ ግዥዎችን አፈፃፀም በራሱ ዕቅድ፣ እንዲሁም ጥፋት ስለመፈፀሙ ጥቆማ ሲቀርብለት ሂደቱን በማስቆም የሥርዓት መጠበቅ ወይም የክዋኔ ኦዲትና ክትትል የማካሄድ እና በግኝቱ መሠረት ተገቢውን እርምጃ እንደአግባብነቱ በራሱ መውሰድ ወይም ሥልጣን ባላቸው ሌሎች አካላት እንዲወሰድ ማድረግ፣

፲፬/ የሚቀርቡ የጥፋተኝነት ሪፖርቶችን በማጣራት ጥፋት የተፈፀመ መሆኑን ሲያረጋግጥ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፹፬ መሠረት እንደጥፋቱ ክብደት ማስጠንቀቂያ የመስጠት፣ ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ በመንግሥት ግዥ ወይም የመንግሥትን ንብረት በሽያጭ ለማስወገድ በሚወጣ ጨረታ እንዳይሳተፉ ማገድ፣

9/ Introduce and administer an efficient system of registration for candidates who are interested in participating in public procurement or sale of disposable property,

10/ Draw up strategic plan for institutional and staff capacity building in public procurement and property administration and give training accordingly,

11/ Set up, develop, maintain and update a data base that covers the entire spectrum of public procurement and property administration,

12/ Strive to maintain harmonized system of procurement and property administration between the Federal and Regional Governments,

13/ Conduct compliance or performance audit and follow up on the execution of public procurement and property administration, as well as on procurements of public-private partnership in accordance with its own plan, or on receipt of allegation of misconduct, by suspending the process in case of the latter , and take or cause to be taken, as the case may be, any appropriate measure on the basis of the findings,

14/ In accordance with Article 84 of this Proclamation, give warning to or suspend for a definite or indefinite period of time from participating in public procurement or sale of disposable property on the basis of reports of default brought to it where it establishes that such default has in fact been committed,

፲፭/ የመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ተግባራት ይህን አዋጅና በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጡ መመሪያዎችን ተከትሎ መፈፀማቸውን መከታተልና መቆጣጠር፣ እንዲሁም ከመሥሪያ ቤቶች፣ ከአቅራቢዎች ወይም ከሕዝብ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን መሠረት በማድረግ ምርመራ ማድረግና እርምት እንዲወሰድ ማድረግ፣ እንደሁኔታው አስተዳደራዊ እርምጃ የመውሰድ ሥልጣን ላለው አካል ማሳወቅ፣

፲፮/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፲፭) ዓላማ፣ እንዲሁም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፹፫ ንፁስ አንቀጽ (፫) መሠረት ሰነዶች፣ መዛግብት፣ ሪፖርቶች እና ማናቸውም ሌሎች ማስረጃዎች ከመንግሥት መሥሪያ ቤቶች፣ ከተወዳዳሪዎች፣ ከተጫራቾች ወይም ከአቅራቢዎች እና ከሌላ ማንኛውም ሰው እንዲቀርቡለት የማዘዝ፣ እንዲሁም ምስክሮችን በመጥራት፣ ምስክሮችና ግዥው ወይም የሚወገደው ንብረት ሽያጭ የሚመለከታቸው ወገኖች ቃላቸውን በመሐላ እንዲሰጡ ማድረግ፣

፲፯/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፲፭) መሠረት በሚያደርገው ቁጥጥርና ምርመራ ጉዳዩ በፍትሐብሔር ወይም ወንጀል እንዲታይ ማድረግ አስፈላጊ ነው ብሎ ሲያምን ለሚመለከተው የሕግ አካል ማሳወቅ፣

፲፰/ እንደአስፈላጊነቱ አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ሙያተኞች ሊኖራቸው የሚገባውን ዕውቀትና ክህሎት መወሰን፣ የሙያ ብቃት የማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መስጠት፣ ሙያተኞችን መመዝገብና መቆጣጠር፣ የግዥና ንብረት አስተዳደር ሙያተኞች ማህበር እንዲቋቋም ድጋፍ ማድረግ እንዲሁም የሚቋቋመው የሙያተኞች ማህበር በሕግ

15/ Follow up and Monitor whether the activities of public procurement and property administration are carried out in conformity with this Proclamation and the Directive issued hereunder, as well as conduct investigation based on complaints from Public Bodies, suppliers or the public, and cause corrective action to be taken, and report to the Public Body competent to take administrative measure as the case may be,

16/ For the purpose of Sub Article (15) of this Article and pursuant to Sub-Article (3) of Article 83 of this Proclamation, require documents, records, reports and any other evidence from Public Bodies, candidates, bidders, suppliers or from any other person; summon and examine witnesses and the parties concerned with the procurement or sale of the disposable property, and require them to give oral testimony under oath,

17/ Report the matter to the competent body, where it determines that the monitoring and investigation carried out in accordance with Sub Article 15 of this Article necessitates civil or criminal action,

18/ As necessary, in collaboration with appropriate entities, determine the knowledge and skill that professionals are required to possess, certify, register and monitor such professionals, render the necessary support for the establishment of procurement and property administration professionals association, and delegate, as

የሚሰጠውን ኃላፊነት መውጣት በሚችልበት አቋም ላይ ሲደርስ እንደሁኔታው ከላይ የተዘረዘሩትን ተግባራት እንዲያከናውን ውክልና መስጠት፣

፲፱/አግባብነት ባለው የክልል መንግሥት አካል በክልሉ የመንግሥት ግዥ እና የሚወገድ ንብረት ሽያጭ ላይ እንዳይሳተፍ የታገደ ተጫራች ወይም አቅራቢ በፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች ግዥ እና የሚወገድ ንብረት ሽያጭ ላይ እንዳይሳተፍ ማገድ፣

፳/ለመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ሙያ ዕድገት ከሚሰሩ እና በዘርፉ ለመሳተፍ ፍላጎት ካላቸው አካላት ጋር ተቋማዊ ግንኙነት በመፍጠር ተባብሮ መሥራት፣

፳፩/በፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሥር ያልሆነን የፌደራል መንግሥት ንብረት ወይም በሕግ ወይም ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት በተሰጠ ውሳኔ የፌደራል መንግሥት ንብረት እንዲሆን የተደረገን ማናቸውንም ንብረት በመንግሥት ንብረትነት የመያዝ፣ የማስተዳደር፣ በሚኒስትሩ ውሳኔ መሠረት እንዲወገድ የማድረግ፣

appropriate, the aforementioned duties when the association attains the standing that enables it to discharge the responsibilities to be vested in it by law,

19/ Cause any bidder or supplier suspended by a decision of a competent authority of a Regional Government from participating in public procurement and sale of disposable property of such region, not to participate in public procurement and sale of disposable property of the Federal Public Bodies where it is satisfied that the suspension appropriate,

20/ Establish institutional linkage and engage cooperatively with entities working for professional development in public procurement and property administration and have interest to participate in the area,

21/ Take possession of and administer , cause the disposal of the property in accordance with the decision of the Minister, any property of the Federal Government that is not owned by any Public Body, or that is transferred to the Federal Government by virtue of the law or by decision of a competent court,

፳፪/ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን በጤና ወይም በአካባቢ ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ ጊዜያቸው ያለፈባቸው አደገኛ ኬሚካሎች ወይም የኬሚካል ውጤቶች፣ ከአገልግሎት ውጭ የሆኑ የኤሌክትሮኒክ ዕቃዎች፣ መድኃኒቶች፣ ጨረራ አመንጪ ዕቃዎች፣ የኢንዱስትሪ ዝቃጮችና የግብርና ተረፈ ምርቶች አያያዝና አጠባበቅ፣ እንዲሁም አወጋገድ ላይ ጥናት በማከናወን የአሰራር ሥርዓት እንዲዘረጋ ማድረግ፣

፳፫/ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚኒስቴሩ የሚዘረጋውን ዘመናዊ የግዥ እና ንብረት አስተዳደር የኤሌክትሮኒክ አሠራር ሥርዓት መቆጣጠር፣ ማስተዳደር፣

፳፬/ በዚህ አዋጅ ሌሎች አንቀፆችና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች ለባለሥልጣኑ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት መወጣት፡፡

**፲፫. <u>የባለሥልጣኑ አቋም</u>**

ባለሥልጣኑ፡-

፩/ በመንግሥት የሚሾም ዋና ዳይሬክተር፣

፪/ እንደ አስፈላጊነቱ በመንግሥት የሚሾሙ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፣ እና

፫/ አስፈላጊ ሠራተኞች

ይኖሩታል፡፡

**፲፬. <u>የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር</u>**

፩/ የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር የባለሥልጣኑ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ሆኖ የባለሥልጣኑን ሥራዎች በበላይነት ይመራል፣ ያስተዳድራል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሰው ጠቅላላ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር፡-

22/ In collaboration with other entities, conduct a study to establish a system for the handling, preservation and disposal of properties that are harmful to health or the environment such as expired and dangerous chemical substances or products, discarded electronic equipment, drugs, radiation emitting items, industrial wastes, and agricultural bi-products,

23/ Regulate and administer the electronic system of public procurement and property administration to be established by the Ministry pursuant to this Proclamation.

24/ Discharge the powers and duties vested in it by other provisions of this Proclamation and other relevant laws.

**13. <u>Organization of the Authority</u>**

The Authority shall have:

1/ A Director General appointed by the Government,

2/ Deputy Director Generals, as required to be appointed by the Government, and

3/ The necessary staffs.

**14. <u>Powers and Duties of the Director General</u>**

1/ The Director General of the Authority shall be the chief executive officer of the Authority and shall direct and administer the activities of the Authority.

2/ Without limiting the generality of Sub-Article (1) of this Article, the Director General of the Authority shall:

ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፪ የተመለከቱትን የባለሥልጣኑን ሥልጣንና ተግባራት ሥራ ላይ ያውላል፣

ለ) የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሠረታዊ መርሆዎች ተከትሎ የባለሥልጣኑን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣

ሐ) የባለሥልጣኑን የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣ በመንግሥት ሲፈቀድም ሥራ ላይ ያውላል፣

መ) የባለሥልጣኑን የሥራ ክንውንና የሂሳብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣

ሠ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ባለሥልጣኑን ይወክላል፡፡

፫/ የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ለባለሥልጣኑ የሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ኃላፊነቱን በከፊል ለባለሥልጣኑ ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

a) exercise the powers and duties of the Authority specified under Article 12 of this Proclamation,

b) Employ and administer the employees of the Authority in accordance with the basic principles of the Federal Civil Service Laws,

c) Prepare and submit to the Ministry the work program and budget of the Authority and implement same upon approval by the Government,

d) Prepare and submit to the Ministry operational and financial report of the Authority,

e) Represent the Authority in all its dealings with third parties.

3/ The Director General of the Authority may delegate part of his powers and duties to employees of the Authority to the extent necessary for the effective management of the functions of the Authority.

**፲፭. <u>የምክትል ዋና ዳይሬክተር ሥልጣንና ተግባር</u>**

የባለሥልጣኑ ምክትል ዋና ዳይሬክተር፡-

፩/ ተጠሪነቱ ለዋና ዳይሬክተሩ ሆኖ ተለይቶ የሚሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ያከናውናል፤

፪/ የባለሥልጣኑን ተግባራት በማቀድ፣ በማደራጀት፣ በመምራት እና በማስተባበር ዋና ዳይሬክተሩን ያግዛል፤

፫/ የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር በማይኖርበት ጊዜ ዋና ዳይሬክተሩ ለይቶ ካልወከለ በስተቀር በሹሙት ቅድሚያ ያለው ምክትል ዋና ዳይሬክተር ዋና ዳይሬክተሩን ወክሎ ይሠራል፡፡

**15. <u>Powers and Duties of the Deputy Director General</u>**

The Deputy Director General shall:

1/ Being accountable to the Director General of the Authority, discharge the duties and responsibilities assigned to him;

2/ Assist the Director General in planning, organizing, directing and coordinating the activities of the Authority;

3/ In the absence of the Director General and upon delegation shall act in place of the Director General; failing such delegation a deputy director General with the longest tenure shall be designated.

**፲፮. በጀት**

የባለሥልጣኑ በጀት በመንግሥት የሚመደብ ይሆናል፡፡

**፲፯. የሂሳብ መዛግብት**

፩/ የባለሥልጣኑ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብትን ይይዛል፡፡

፪/ የባለሥልጣኑ የሂሳብ መዛግብት እና ሌሎች ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም በዋናው ኦዲተር በሚሰየም ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ፡፡

**ምዕራፍ አራት**

**መሠረታዊ የመንግሥት የግዥ እና የንብረት አስተዳደር ድንጋጌዎች**

**፲፰. የግዥ እና የንብረት አስተዳደር ዕቅድ**

፩/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጡ መመሪያዎች ላይ የሚገለፁትን ዝርዝር ጉዳዮች ያካተተ ዓመታዊ የግዥ እና የንብረት አስተዳደር ዕቅድ ማዘጋጀት ይኖርባቸዋል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተዘጋጁት የግዥ እና ንብረት አስተዳደር ዕቅዶች በመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ ፀድቀው ለሚመለከታቸው የመሥሪያ ቤቱ የሥራ ክፍሎች እንዲሁም ዓመታዊ የግዥ ዕቅዱን በመመሪያው ላይ በሚወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ በኤሌክትሮኒክ ሥርዓት መሠረት ለባለሥልጣኑ መላክና ለሕዝብ ይፋ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

**፲፱. የግዥ እና የንብረት አስተዳደር ሰነዶች ስለመያዝ**

፩/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ከመንግሥት ግዥ እና የንብረት አስተዳደር ጋር የተያያዙ ሰነዶችን ግዥው ከተፈፀመበት፣ ወይም ንብረቱ

**16. Budget**

The budget of the Authority shall be allocated by the Government.

**17. Books of Accounts**

1/ The Authority shall keep complete and accurate books of accounts.

2/ The books of accounts and other financial documents of the Authority shall be audited annually by the Auditor General or by an auditor designated by him.

**CHAPTER FOUR**

**BASIC PROVISIONS OF PUBLIC PROCUREMENT AND PROPERTY ADMINISTRATION**

**18. Procurement and Property Administration Plan**

1/ Public Bodies shall prepare annual procurement and property administration plan containing such details as are stated in the Directives issued hereunder.

2/ The procurement and property administration plan to be prepared by a Public Body in accordance with Sub-Article (1) of this Article shall be approved by the head of the Public Body and communicated to the relevant units of the Public Body and sent to the Authority and disclose to the public using the electronic system within the timeframe to be specified in the procurement Directive.

**19. Records of Procurement and Property Administration**

1/ Public Bodies shall retain using the electronic system complete records pertaining to their procurement and

ከተወገደበት ቀን አንስቶ እስከ ፲ ዓመት በኤሌክትሮኒክ ሥርዓት ይዘው ማቆየት አለባቸው፡፡

፪/ ከላይ በንዑስ አንቀጽ ፩ ላይ በተደነገገው መሠረት መሥሪያ ቤቶች የግዥና ንብረት አስተዳደር ተግባራትን ኦዲት ለማድረግ፣ ወይም ሌሎች በሕግ ሥልጣን ለተሰጣቸው አካላት በሚያመች ሁኔታ ሰነዶችን በተሟላ መልኩ አደራጅተው መያዝ አለባቸው፡፡

፫/ ውል ከተፈረመ ወይም በማናቸውም ምክንያት ውሉ ከተቋረጠ የግዥ አፈፃፀሙንና የሚወገድ ንብረት ሽያጭ ዝርዝር አፈፃፀም የሚያሳየውን መረጃ ተጫራቾች ሲጠይቁ እንዲያውቁት መደረግ አለበት፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ አዋጅ፣ በአፈፃፀም መመሪያዎቹ ወይም አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች ሥልጣን በተሰጠው አካል ወይም በፍርድ ቤት ካልታዘዘ በስተቀር የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ የሚከተሉትን መረጃዎች መስጠት የለበትም፡-

ሀ) የመረጃው ይፋ መሆን በሕግ የማይፈቀድ፣ የሕግ አፈፃፀምን የሚያሰናክል፣ የሕዝብን ጥቅም የሚቃረን፣ የተዋዋዮችን ሕጋዊ የንግድ ጥቅም እንዲሁም ፍትሐዊ ውድድርን የሚጎዳ ከሆነ፣

ለ) ከተጫራቾች የቀረበውን የመወዳደሪያ ሀሳብ ከመመርመርና ከመገምገም ተግባር ጋር የተያያዙ እና ተጫራቾች ያቀረቧቸውን የመጫረቻ ሰነዶች ይዘት የሚገልፁ መረጃዎች፡፡

property administration for 10 years from the date of procurement or disposal of the property.

2/ The records mentioned in Sub Article 1 shall be kept in such an orderly manner as to be readily locatable for audit or any other lawful purpose by persons having legally authorized access to such records.

3/ The record concerning any proceeding of public procurement or sale of disposable property shall on request, and once the proceedings have resulted in a contract or the contract has otherwise been terminated, be made available to the bidders who participated in the proceedings. However, except when ordered to do so by a competent court or by other body authorized by this Proclamation, the Directives issued hereunder or any other law and subject to the conditions of such an order, the Public Body shall not disclose:

a) information if its disclosure would be contrary to law, would impede law enforcement, would not be in the public interest, would prejudice legitimate commercial interest of the parties or would inhibit fair competition,

b) information relating to the examination and evaluation of bid proposals or quotations submitted by bidders and the actual content of bid proposals or quotations.

**፳. አድልዎ ያለማድረግ**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፩ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በዜግነት፣ በዘር ወይም ከመወዳደሪያ መስፈርቶች ጋር ባልተያያዙ ሌሎች ምክንያቶች በመንግሥት ግዥ አፈፃፀም እና የሚወገድ ንብረት ሽያጭ ሂደት በማንኛውም ተወዳዳሪ ወይም ተጫራች ላይ አድልዎ ማድረግ አይቻልም፡፡

**፳፩. ልዩ አስተያየት**

፩/ ዝርዝር ሁኔታዎችና አፈፃፀሙ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው መመሪያ ላይ በሚወሰነው መሠረት በጨረታ ግምገማ ወቅት ለሚከተሉት ልዩ አስተያየት ይደረጋል፡-

ሀ) በኢትዮጵያ ለተመረቱ ዕቃዎች፣

ለ) ለኢትዮጵያውያን ከምክር ውጭ የሆነ አገልግሎት ሰጪዎች፣ አማካሪዎች እና ሥራ ተቋራጮች፣

ሐ) በውጭ ሀገር ድርጅቶችና በሀገር በቀል ድርጅቶች መካከል ለሚመሠረት ጥምረት ወይም የሽርክና ወይም የእሽሙር ማህበር፣ ወይም

መ) በማምረት ሥራ ላይ ለተሰማሩ ጥቃቅንና አነስተኛ ማህበራት፣ አካል ጉዳተኞች፣ እና የነጋዴ ሴቶች ማህበራት፣ እንዲሁም የቴክኖሎጂ ፈጠራ ውጤቶች፡፡

፪/ የስራ ዕድል ፈጠራ ተቋማት ብቻ የሚሳተፉበት ግዥ እና ዝርዝር አፈፃፀም በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው መመሪያ ይወስናል፡፡

**20. Non-Discrimination**

Without prejudice to Article 21 of this Proclamation, candidates or bidders shall not be discriminated against in any proceedings of public procurement and sale of disposable property on account of nationality, race or any other criterion not having to do with their qualifications.

**21. Preference**

1/ With the details to be prescribed in the Directive to be issued hereunder, a preference margin which shall be determined by the procurement Directive to be issued hereunder shall be granted to the following in the evaluation of bids:

a) goods produced in Ethiopia,

b) non-cosultancyservice providers, consultants and contractors of Ethiopian nationals,

c) consortium, partnerships or joint ventures formed between domestic and foreign enterprises, or

d) micro and small enterprises engaged in manufacturing, persons with disabilities, and women’s enterprises, as well as products of technological innovations.

2/ The conditions under which procurement may be open exclusively to manufacturing enterprises established for job creation shall be determined by the procurement Directive issued hereunder.

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የዕቃዎች፣ ከምክር ውጭ የሆኑ አገልግሎቶች፣ የምክር አገልግሎቶች ወይም የግንባታ ዘርፍ ሥራዎች ጥራትና ዋጋ ተመሳሳይ ሆኖ ተጫራቾች በግምገማ እኩል ነጥብ ሲያገኙ ለሀገር ውስጥ ምርቶች፣ ከምክር ውጭ የሆኑ አገልግሎቶች፣ የምክር አገልግሎቶች ወይም የግንባታ ዘርፍ ሥራዎች ቅድሚያ ይሰጣል፡፡

፬/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ሀ) አፈፃፀም ማናቸውም ዕቃ በኢትዮጵያ ውስጥ እንደተመረተ ለመቆጠር ማሟላት ያለበት የአገር ውስጥ የታከለ እሴት መጣኔ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

፭/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተፈቀደውን ልዩ አስተያየት በጨረታ ሰነድ ውስጥ በግልፅ ማመልከት አለበት፡፡

## ፳፪. የግንኙነት ስልት

፩/ በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች እና በተወዳዳሪዎች፣ ተጫራቾች ወይም አቅራቢዎች መካከል የሚደረጉ ግንኙነቶች በኤሌክትሮኒክ ሥርዓት መሠረት በመጠቀም መደረግ አለባቸው፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ የመረጃ ልውውጡን ትክክለኛነት እና በሚስጥር መጠበቁን ማረጋገጥ የሚያስችሉ ሥርዓቶች መዘርጋታቸውን እና በቴክኒክ ረገድ ተፈላጊ ሁኔታዎች መሟላታቸውን ሲያረጋግጥ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ግንኙነት ማድረግ የሚያስችል መመሪያ ያወጣል፡፡

3/ Without prejudice to the provision of Sub-Article 1 of this Article, preference shall be given to local goods, non-cosultancyservices, consultancy services or works where in the evaluation of bids for procurement of goods, services, consultancy services or works, equal percentage points are given for bidders offering similar price and quality.

4/ For the purpose of paragraph (a) of Sub-Article 1 of this Article, the minimum threshold of value addition required for goods to be treated as produced in Ethiopia shall be determined in the Directive to be issued hereunder.

5/ The Public Body executing the procurement shall expressly state in the bid document the preference to be granted pursuant to Sub-Article 1 of this Article.

## 22. Mode of Communication

1/ Communications between Public Bodies on one hand and candidates, bidders or suppliers on the other shall be done using the electronic system.

2/ Subject to a system for ensuring the necessary safeguards with regard to authenticity and confidentiality, and when technical conditions so permit, the Ministry shall issue a Directive to determine the extent by which communication by electronic means may be used.

፳፫. **ቋንቋ**

፩/ ለብሔራዊ ጨረታ የሚዘጋጀው የጨረታ ሰነድ እና ጨረታው የሚካሄድበት ቋንቋ አማርኛ ይሆናል፣ ሆኖም ለግዥው ወይም ለሚወገደው ንብረት ሽያጭ አካሄድ አመቺና ፍትሐዊ ውድድርን የማይገድብ መሆኑ ሲታመንበት የጨረታ ሰነዱ የተወሰኑ ክፍሎች እና የመጫረቻ ሰነድ በእንግሊዝኛ ቋንቋ እንዲዘጋጅ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

፪/ ለዓለም አቀፍ ግዥ ጨረታ ማስፈፀሚያ የሚዘጋጁት ማናቸውም ሰነዶች በእንግሊዝኛ ቋንቋ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

፳፬. **የተወዳዳሪዎች ቅድመ ብቃት**

፩/ በማንኛውም የመንግሥት ግዥ ለመሳተፍ ፍላጎት ያላቸው ተወዳዳሪዎች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን እና የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ከግዥው ልዩ ባህርይ በመነሳት የሚያወጧቸውን ሌሎች መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው፡-

ሀ) የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት የንግድ ግንኙነቶች ላለማድረግ ክልከላ ከጣለበት ሀገር የሚመጣ ዕቃና አገልግሎት አለመሆኑን፣

ለ) በተባበሩት መንግሥታት የፀጥታው ጥበቃ ምክር ቤት ውሳኔ መሠረት ክልከላ ከተደረገባቸው ሀገራት ያልመጡ ዕቃዎችና ተዛማጅ አገልግሎቶች መሆናቸው ወይም ክፍያ እንዲፈፀምለት በምክር ቤቱ ክልከላ ያልተደረገበት ሰው ወይም ድርጅት፣

23. **Language**

1/ For national bids, the bid document shall be prepared and the bid process shall be conducted in the Amharic language. However, if it is found to facilitate the process of procurement or sale of disposable property, the Public Body concerned may authorize the use of the English language in the preparation of some part of the bid document and bid proposals, provided that such an act is not prejudicial to fair competition.

2/ For procurements to be conducted by means of International Competitive Bidding, all documents shall be prepared in the English language.

24. **Pre-Qualification Requirements of Candidates**

1/ In order to participate in public procurement and sale of disposable property, candidates shall qualify by meeting the following criteria as appropriate, and such other criteria as the Public Body considers appropriate under the circumstances:

a) that the object of procurement does not originate in a country that the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has suspended trade relations with,

b) that the object of procurement does not originate in a country under trade sanction imposed by resolution of the Security Counsil of the United Nations, or that such sanction does not apply to the person or entity to whom payment would be effected,

ሐ) በዚህ አዋጅና በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው መመሪያ እንዲሁም ሌሎች የግዥ እና ንብረት አስተዳደር ሕግ ሰነዶች በተገለፀው መሠረት የጥቅም ግጭት የሌለው፣

መ) ውል ለመፈፀም የሚያስችል የሕግ ችሎታ ያለው፣

ሠ) በዕዳ ያልተያዘ፣ ያልከሰረ ወይም የሥራ እንቅስቃሴውን ያላቋረጠ፣ ወይም የንግድ ሥራ እንቅስቃሴው ያልታገደ ወይም በእነዚህ ምክንያቶች ተከሶ በክርክር ላይ ያልሆነ፣

ረ) በመንግሥት ግዥ ወይም በሚወገደው ንብረት ሽያጭ እንዳይሳተፍ ታግዶ የነበረ ከሆነ የታገደበትን ጊዜ ያጠናቀቀ፣

ሰ) ዝርዝሩ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ መመሪያ የሚወሰን ሆኖ ቀደም ሲል በግዥ ፈፃሚው ወይም ንብረት አስወጋጁ መሥሪያ ቤት ሥር ሠራተኛ የነበረ እና የመጫረቻ ሰነድ ባቀረበበት ቀን መሥሪያ ቤቱን ከለቀቀ ከአንድ ዓመት በላይ የሆነው ሰው፣

ሸ) የታደሰ የንግድ ሥራ ፈቃድ ያለው እና በኢትዮጵያ የግብርና የታክስ ሕጎች በተደነገገው መሠረት የግብርና የታክስ ግዴታውን የተወጣ፣ እንዲሁም በኢትዮጵያ ውስጥ የንግድ እንቅስቃሴ የሌለው የውጭ ሀገር ድርጅት ከሆነ በተቋቋመበት አገር የተሰጠ ሕጋዊ የንግድ ፈቃድ እና የታደሰ የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት ፈቃዱን ወይም የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀቱን በሰጠው ሀገር በሚገኝ የኢትዮጵያ ኤምባሲ በማረጋገጥ ያቀረበ፣ እና

c) that the candidate does not have conflict of interest as defined in this proclamation, the Directives issued hereunder and other legal documents pertaining to public procurement or property administration,

d) that the candidate has the capacity to enter into a contract,

e) that the candidate is not insolvent, in receivership, bankrupt or being wound up, or that his business activities have not been suspended or he is not the subject of legal proceedings for any of the foregoing,

f) that the period for which he was suspended from participating in public procurement or sale of disposable property must have been over,

g) with the details to be prescribed in the Directive issued hereunder, in the case of a candidate being an ex-employee of the Public Body executing the procurement or sale of the disposable property, that on the date he submits his proposal, at least one year mast have lapsed since he left the Public Body,

h) the candidate who has renewed trade license and fulfilled his obligation to pay taxes in accordance with the Ethiopian tax laws or a foreign company having no business operation in Ethiopia and with business license and certificate of registration authenticated by Embassy of Ethiopia in a country where the company has been licensed or registered, and

ቀ) በኢትዮጵያ ውስጥ የንግድ እንቅስቃሴ የሌለው የውጭ ሀገር ድርጅት ካልሆነ በስተቀር የባንክ ሂሳብ ያለው፡፡

፪/ በጨረታ ሰነዱ ላይ በተለየ ሁኔታ ካልተገለፀ በስተቀር ማናቸውም በመንግሥት ግዥ ጨረታ ለመሳተፍ ፍላጐት ያላቸው ተወዳዳሪዎች የውድድር አቅማቸውንና ብቃታቸውን ለማሳደግ ከሀገር ውስጥ ወይም ከውጭ አገር ድርጅት ጋር በእሽሙር፣ በሽርክና ወይም በጊዜያዊ ህብረት/ጥምረት ማህበር በመደራጀት ለውድድር ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው መመሪያ በልዩ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ተጠሪ በሆኑለት የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም ለመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ተጠሪ የሆነ ሌላ ግዥ ፈፃሚ መሥሪያ ቤት በሚፈፅመው ግዥ ላይ ያለውድድር መሳተፍ አይችልም፡፡

፬/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ተወዳዳሪዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተዘረዘሩት መስፈርቶች የሚያሟሉ መሆኑን ለማረጋገጥ አስፈላጊ የሆኑ የሰነድ ማስረጃዎችን እንዲያቀርቡ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በተወዳዳሪዎች እንዲሟሉ የሚጠበቁት መስፈርቶች በጨረታ ሰነድ ወይም የተጫራቾችን የመወዳደሪያ ሀሳብ ለመጠየቅ በሚዘጋጁ ሰነዶች ውስጥ መገለፅ አለባቸው፡፡

፮/ ዝርዝር አፈፃፀሙ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው መመሪያ የሚወሰን ሆኖ በመንግሥት የሚወገድ ንብረት ሽያጭ ላይ ለመሳተፍ የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በጨረታው መሳተፍ ይችላል፡፡

i) unless it is a foreign company that does not have business in Ethiopia, the candidate has a bank account.

2/ Unless expressly provided otherwise in the bid document, candidates desiring to participate in a bid for public procurement by forming joint venture, partnership, or consortium with domestic or foreign business entities may do so to boost their competitive ability.

3/ Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article, unless otherwise provided in the Directive issued hereunder, a public enterprise shall not participate with out competition in a procurement by a Public Body to which the enterprise is accountable, or in procurement by another procuring Public Body which is accountable to the same Public Body.

4/ The Public Body may require candidates to produce documentary evidence to prove that they fulfill the requirements listed in Sub-Article (1) of this Article.

5/ The requirements enumerated in Sub Article (1) of this Article shall be expressly stated in the bid document or in the request for proposal;

6/ With mode of application of this provision to be determined in the Directive issued hereunder, any person desiring to participate in a bid to buy disposable property may do so.

፯/የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ሀሰተኛ ማስረጃ ያቀረቡ ተጫራቾች ወይም ብቃታቸውን ለማረጋገጥ ሲሉ መሠረታዊ ስህተት ያለበት ወይም ያልተሟላ ማስረጃ ማቅረባቸው በማናቸውም ጊዜ የተረጋገጠባቸውን ተጫራቾች ከጨረታ ውድድር ውጪ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡

7/ Without prejudice to being criminally liable in accordance with Article 88 of this Proclamation, the Public Body shall disqualify a bidder who submits a document containing false information for purposes of qualification or if it finds at any time that the information submitted concerning the qualification of the bidder was materially inaccurate or incomplete.

**፳፭. <u>የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ</u>**

፩/ ስለግዥው ምንነት ትክክለኛና የተሟላ መግለጫ እንዲኖር እንዲሁም ተወዳዳሪዎች ፍትሐዊና ግልፅ በሆነ አሠራር መወዳደር የሚችሉበትን ሁኔታ ለማመቻቸት የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ የሚገዙትን ዕቃ፣ ከምክር ውጭ የሆነ አገልግሎት፣ የምክር አገልግሎት ወይም የግንባታ ዘርፍ ሥራ ባህርይ የሚያሳይ የቴክኒክ ፍላጐት መግለጫ እንደ ግዥው ውስብስብነት ከሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ጋር በመሆን ማዘጋጀት አለባቸው፡፡

፪/የቴክኒክ ፍላጐት መግለጫው የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ሊገዛ የሚፈልገውን ዕቃ ጥራት፣ ጠቀሜታ፣ እንደአስፈላጊነቱ መለኪያውን፣ መለያውን፣ መጠሪያውን፣ አስተሻሸጉን፣ ወይም የአመራረቱን ሂደትና ዘዴ እንዲሁም ተፈላጊ የሆኑ ሌሎች ሁኔታዎችን የሚያሟላ መሆኑ የሚረጋገጥበት ሥርዓት የሚገልፅ መሆን አለበት፡፡

፫/ በመንግሥት መሥሪያ ቤቱ የሚዘጋጀው የቴክኒክ ፍላጐት መግለጫ እስከተቻለ ድረስ፡-

ሀ) በዲዛይን ወይም ባህሪያትን በመዘርዘር ላይ ሳይሆን በጠቀሜታ ላይ፣

ለ) ሀገራዊ ደረጃ የወጣለት ሲሆን ደረጃውን ወይም ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያላቸውን ደረጃዎች ወይም የንግድ ቃላት ወይም

**25. <u>Technical Specification</u>**

1/ For the purpose of providing a correct and complete description of the object of procurement and facilitating fair and open competition between all candidates, Public Bodies shall, in collaboration with the appropriate Public Bodies depending on the complexity of the procurement, prepare, technical specifications and descriptions setting forth the characteristics of the goods, non-consultancy services, consultancy services or works to be procured.

2/ The technical specification shall clearly describe the Public Body's requirements with respect to quality, performance, safety and where necessary dimensions, terminology, packaging, marking and labeling or the processes and methods of production and requirements relating to conformity assessment procedures.

3/ The technical specification prepared by the Public Body shall as far as possible:

a) be in terms of performance rather than design or descriptive characteristics,

b) be based on national standards, where such exist, or otherwise on internationally recognized standards,

የግንባታ ኮዶች መሠረት አድርጎ መዘጋጀቱን፣

ሐ) ሰፊ ውድድርን የሚጋብዝ እና ውድድርን ሊገድቡ የሚችሉ መግለጫዎች ያልተካተቱበት መሆኑን፣

መ) ለሕይወት ዘመን ወጪ ትንተና የሚያስፈልጉ መመዘኛዎችን ያካተተ መሆኑን፣ እና

ሠ) የሚገዛው ዕቃ፣ ከምክር ውጭ የሆነ አገልግሎት ወይም የግንባታ ሥራ ከባቢያዊ ብክለትን የማያስከትል መሆኑን ማረጋገጥ የሚያስችሉ መመዘኛዎችን የያዘ መሆኑን፣

ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

፬/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱን ፍላጐት በትክክል ለመግለፅ አስቸጋሪ ካልሆነ ወይም ሌላ ዘዴ ከሌለ በስተቀር የቴክኒክ መግለጫው የተለየ የንግድ ምልክት ወይም ስም፣ ፓተንት፣ ዲዛይን ወይም የተወሰነን አምራች ወይም አገልግሎት ሰጪን የሚጠቅስ መሆን የለበትም፡፡ ሆኖም አስገዳጅ ሁኔታ በሚያጋጥምበት ጊዜ እንደ አስፈላጊነቱ ከላይ የተገለፁትን በማመልከት እና "ወይም ተመሳሳይ" የሚል ሐረግ በመጨመር የፍላጎት መግለጫውን ማዘጋጀት ይቻላል፡፡

## ፳፮. <u>ጨረታን በሙሉ ወይም በከፊል ውድቅ ስለማድረግ</u>

፩/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ከሚከተሉት በአንዱ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ምክንያቶች የግዥ ወይም የንብረት ሽያጭ ውል ከመፈረሙ በፊት ጨረታን ወይም የመጫረቻ ሰነድን በማናቸውም ጊዜ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ውድቅ ማድረግ ይችላሉ፡-

trade terms or building codes,

c) invite open competition and be devoid of any statement having the effect of restricting competition,

d) contain criteria necessary for life time cost analysis, and

e) contain criteria for ensuring that the goods, services or works to be procured by the Public Body are environmentally friendly.

4/ There shall be no requirement for reference in the technical specifications to a particular trademark or name, patent, design or type, specific original producer or service provider, unless there is no sufficiently precise or intelligible way of describing the procurement requirements of the Public Body, in which case words such as "or equivalent" may be included in the specifications.

## 26. <u>Rejection of Bids Wholly or Partly</u>

1/ Public Bodies may for one or more of the following reasons, reject bid or bid Proposal in whole or in part, at any time prior to the conclusion of contract for public procurement or sale of disposable Property:

ሀ) በግዥ አፈፃፀም እና ንብረት ሽያጭ ሂደት ላይ ውጤቱን ሊያዛባ የሚችል ስህተት መፈፀሙ ከተረጋገጠ፣

ለ) በሥራ ዕቅድ መቀየር ምክንያት ወይም የመሥሪያ ቤቱን ፍላጐት ለማሟላት ሌላ የተሻለ አማራጭ በመፈጠሩ ምክንያት ወይም ግዥውን ወይም የንብረት ሽያጩን ማካሄድ ለመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ኢኮኖሚያዊ ወይም ማህበራዊ ጥቅም የማያስገኝ መሆኑ ሲረጋገጥ፣

ሐ) የቀረቡት ተጫራቾች በጨረታ ሰነዱ ላይ የተቀመጠውን ዝቅተኛ መስፈርት የማያሟሉ ሲሆን፣

መ) በጨረታ የቀረበው ዋጋ ከኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት ከሚያሰራጨው ወቅታዊ የገበያ ዋጋ፣ ወይም ከኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት መረጃ ማግኘት የማይቻል ከሆነ እንደ ቅደምተከተሉ ከታወቀ አምራች ዋጋ ወይም ከመስሪያቤቶች በሚቀርብለት ጥያቄ መነሻ ባለሥልጣኑ በሚሰጠው ትዕዛዝ መሰረት በማዕከል በሚከናወን የገበያ ዋጋ ጥናት መሠረት ከሚገኘው ዋጋ አንፃር ከፍተኛ ልዩነት ያለው ሲሆን፣ ወይም የግንባታ ሥራ ግዥ ሲሆን የቀረበው ዋጋ እጅግ አነስተኛ ወይም የተጋነነ ዋጋ ሆኖ ሲገኝ፣

ሠ) በጨረታው አሸናፊ የሆነው ተጫራች የሰጠው ዋጋ የግዥ ፈፃሚ መሥሪያ ቤቱ ለግዥው ከያዘው በጀት በላይ ሲሆንና የበጀቱን ልዩነት ከሌላ ምንጭ ማሟላት የማይቻል ሲሆን ወይም ከሚሸጠው ንብረት የጨረታ መነሻ ዋጋ በታች ሲሆን፣

a) where there is proof of fundamental error in the proceeding of procurement or sale of disposable property which could affect the outcome of the bid,

b) where it is ascertained that the procurement or sale of disposable property is no longer necessary for the Public Body as a result of a change of work plan or another alternative representing a better option to meet the requirement of the Public Body,

c) where bidders fail to meet the minimum criteria set forth in the bid document,

d) where the price offered in the bid has considerable difference from the current market price published by the Central Statistics Service, or if such information cannot be obtained from the Central Statistics Service , from the price of a prominent manufacturer or from the price obtained through market survey conducted by the instruction of the Authority at the request of Public Bodies in order of their sequence, or in case of Procurement of works, the price offered is found to be abnormally high or low,

e) where the price offered by the successful bidder exceeds the budgetary allocation made for the procurement and the Public Body cannot make up for the deficiency from any other source or where the price offered for the property to be disposed of is below the estimated minimum,

ረ) ተጫራቾች የግዥ ወይም የንብረት ሽያጭ ሂደቱን ለማዛባት በመመሳጠራቸው ወይም ሌሎች ከሥነ-ምግባር ውጪ የሆኑ ድርጊቶች በመፈፀማቸው ምክንያት በቂ ውድድር አለመደረጉ ሲረጋገጥ፡፡

፪/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተመለከተው መሠረት ጨረታን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ሲሠርዙ ምክንያቱን የሚገልፅ ማስታወቂያ ለተወዳዳሪዎች ወይም ለተጫራቾች ወዲያውኑ ማሳወቅ አለባቸው፡፡

፫/ ጨረታውን ውድቅ የማድረግን ውሳኔ የተሰጠው ጨረታው ከመከፈቱ በፊት ከሆነ የመጫረቻ ሰነዶቹ በኤሌክትሮኒክ ሥርዓት መሠረት ሚስጥራዊነቱ ተጠብቆ የሚቀመጥ ይሆናል፡፡

፬/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ጨረታን ውድቅ በማድረጋቸው ምክንያት ተጠያቂ አይሆኑም፡፡

፳፯. **<u>ዘመናዊ የግዥ እና የንብረት አስተዳደር ሥርዓት ስለመዘርጋት</u>**

፩/ ሚኒስቴሩ የግዥ እና የንብረት አስተዳዳር ሥርዓትን ወጪ ቆጣቢ፣ ግልጽ እና ዘመናዊ ለማድረግ የሚያስችል ዘመናዊ የኤሌክትሮኒክ የመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ሥርዓት ይዘረጋል፣ መስሪያ ቤቶች እንዲተገብሩ ያደርጋል ሥርዓቱን በየጊዜው ያዘምናል፡፡

፪/ ባለሥልጣኑ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ዓላማ፡-

ሀ) በሚኒስቴሩ የተዘረጋውን ኤሌክትሮኒክ ዘዴ ለማዳበር እና ለማሻሻል የሚያስችሉ ጥናቶችን ያደርጋል፣

f) where it is proved that the bid for procurement or sale of disposable property is not sufficiently competitive as a result of connivance among bidders with an intent to distort the result of the bid or other unethical conduct observed in the bid process.

2/ Public bodies shall give notice to candidates or bidders forthwith disclosing the reasons for wholly or partially cancelling a bid pursuant to Sub-Article (1) of this Article.

3/ If the decision to reject bids is taken before the opening date and time, the bids received shall be kept confidentially using the electronic system.

4/ Public bodies shall incur no liability for rejection of bids pursuant to Sub-Article (1) of this Article.

27. **<u>Establishing a Modern Procurement and Property Administration System</u>**

1/ The Ministry shall establish electronic system to achieve economy, efficiency, transparency and modernization in the execution of public procurement and property administration, and it shall direct Public Bodies to implement electronic procurement and property administration and modernize it from time to time.

2/ For the purpose of the provision of Sub-Article (1) of this Article, the Authority shall:

a) conduct study for the advancement and improvement of the electronic system established by the Ministry,

ለ) በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች፣ በተወዳዳሪዎች፣ በተጫራቾች፣ በአቅራቢዎች እና በተቆጣጣሪ አካላት የአሠራር ሥርዓቱን ለመተግበር የሚያስችል አቅም መፈጠሩን ያረጋግጣል፣

ሐ) በሚኒስቴሩ የተዘረጋውን የኤሌክትሮኒክ አሰራር ሥርዓት ይቆጣጠራል፣ ያስተዳድራል፣

መ) በኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ አጠቃቀም ወቅት ሊከሰቱ የሚችሉ የሳይበር ጥቃቶችን ለመከላከል ይህንኑ እንዲያስተዳድር በሕግ ሥልጣን ከተሰጠው አካል ጋር በትብብር ይሠራል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚዘረጋው የኤሌክትሮኒክ ሥርዓት፡-

ሀ) የግዥ ዕቅድ ዝግጅትን፣

ለ) የጨረታ ማስታወቂያ አወጣጥን፣

ሐ) የማብራሪያ እና የማሻሻያ ጥያቄና ምላሽን፣

መ) የመጫረቻ ሰነድ አቀራረብና አከፋፈትን፣

ሠ) የመጫረቻ ሰነድ ግምገማን፣

ረ) የይግባኝ ማጣራት ሥነ ሥርዓትን፣

ሰ) የውል አስተዳደርን፣

ሸ) በግዥና ንብረት አስተዳደር ሂደት የሚደረጉ የመረጃ ልውውጦችን፣ እና

ቀ) እንደአስፈላጊነቱ ለዚህ ዓላማ በሚኒስቴሩ በሚወጣው መመሪያ የሚገለጹ ሌሎች የግዥና ንብረት አስተዳደር ተግባራትን ያካተተ ሊሆን ይገባዋል፡፡

b) ensure that Public Bodies, candidates, bidders, suppliers and supervising entities have the requisite capacity to implement the system,

c) regulate and administer the electronic system established by the Ministry,

d) work in collaboration with the concerned legal Authority to prevent cyber attacks on the application of the electronic system.

3/ The electronic system to be established pursuant to Sub-Article (1) of this Article shall support the following activities:

a) preparation of procurement plan,

b) issuance of invitation to bid,

c) request for and response to clarification or modification on bid documents,

d) submission and opening of bid proposals,

e) evaluation of bid proposals,

f) procedure of appeal,

g) contract administration,

h) exchange of information in the process of public procurement and property administration, and

i) other activities to be specified in the Directive to be issued by the Ministry for this purpose as necessary.

፬/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ዘመናዊ የኤሌክትሮኒክ የመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ሥርዓትን ተግባራዊ እንዲያደርጉ ሚኒስቴሩ ከወሰነበት ጊዜ ጀምሮ ተግባራዊ ማድረግ አለባቸው። ሆኖም የኤሌክትሮኒክ የግዥ እና ንብረት አስተዳደር ሥርዓትን ተግባራዊ ማድረግ የማይቻልበት ሁኔታ ሲፈጠር እና ሚኒስቴሩ ሲያምንበት የግዥና ንብረት አስተዳደር ተግባራትን ኤሌክትሮኒክ ባልሆነ የግዥና ንብረት አስተዳደር ሥርዓት ይከናወናል። ዝርዝሩ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

፭/ በዚህ አዋጅ እና ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተዘረጋውን ሥርዓት ተከትሎ የቀረበ ሰነድ ወይም የተደረገ ግንኙነት አስገዳጅነት ይኖረዋል፡፡

**፳፰. ዘላቂነት ያለው የግዥና ንብረት አስተዳደርን ተፈፃሚ ስለማድረግ**

፩/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች እንደ ግዥው ባህርይ ከአካባቢ ብክለት የፀዳ፣ መልሶ መጠቀምን፣ የህይወት ዘመን ወጪ ትንተናን እና የማህበረሰብ ተጠቃሚነትን ከግምት ያስገባ ዘላቂነት ያለው የግዥ አፈፃፀም አሰራርን በፍላጎት መግለጫ፣ በመገምገሚያ መስፈርት፣ በውል ቃላትና ሐረጎች ዝግጅት ወቅት፣ እንዲሁም በውል አፈፃፀም ቁጥጥር ወቅት ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡

፪/ ዘላቂነት ያለው የግዥ አፈፃፀም ሥርዓት ዝርዝር አተገባበር በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

4/ Public Bodies shall implement electronic public procurement and property administrations system when the Ministry decides to do so. However, when it becomes impossible to implement public procurement and property administrations system and the Ministry is convinced, they shall execute procurement and property administration functions in other alternative systems. The details shall be prescribed by a Directive to be issued by the Ministry.

5/ Unless prescribed to the otherwise in this Proclamation or in the Directive issued by the Ministry, documents submitted or communications made using the electronic system established pursuant to Sub-Article (1) of this Article has a binding legal effect.

**28. Applying Sustainable Procurement and Property Administration**

1/ Depending on the nature of the Procurement, Public Bodies may apply sustainable procurement considering green procurement, recycling, total life cycle cost analysis and the interest of the society when developing specification and evaluation criteria, defining terms and conditions of the contract, as well as monitoring of contract performance.

2/ Details pertaining to the application of sustainable procurement shall be prescribed in the procurement Directive to be issued hereunder.

**፳፱. <u>የመንግሥት ግዥ እና የንብረት አስተዳደር ሥነ-ምግባር</u>**

፩/ በግዥና ንብረት አስተዳደር ሥራ ላይ የተሰማሩ ኃላፊዎችና ሠራተኞች የሚከተሉትን የሥነ-ምግባር መርሆዎች ተከትለው ተግባራቸውን ያከናውናሉ፡፡

ሀ) የተፈጠረ ወይም ሊፈጠር የሚችል የጥቅም ግጭትን ማሳወቅ እና ራስን ከሂደቱ ማግለል፣

ለ) በተወዳዳሪዎች፣ በተጫራቾች እና በአቅራቢዎች መካከል አድልዎ አለማድረግ፣

ሐ) በሥራ አጋጣሚ ያወቃቸውን የመንግሥት መሥሪያ ቤቱን እና የተወዳዳሪዎችን፣ ተጫራቾችን ወይም የአቅራቢዎችን እንዲሁም የኤሌክትሮኒክ ሥርዓት ተጠቃሚዎችን መረጃ በሚስጥር መጠበቅ፣

መ) ስጦታ ወይም የሥራ ዕድል ወይም የገንዘብ ዋጋ ያለውን ነገር ወይም አገልግሎት አለመቀበል፣

ሠ) በሥራ ሂደት ያወቃቸውን ሊፈጠሩ የታሰቡ ወይም የተፈጠሩ የሙስና ተግባራትን ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የሕግ አስፈፃሚ አካላት ማሳወቅ እና ሙስናን እና ብልሹ አሠራርን ለመዋጋት የሚደረገውን ጥረት ማገዝ፣

ረ) ለመንግሥት ገንዘብ እና ንብረት ተቆርቋሪ መሆን፡፡

፪/ ማንኛውም ተወዳዳሪ፣ ተጫራች ወይም አቅራቢ የመንግሥት የግዥ አፈፃፀምን እና የሚወገድ ንብረት ሽያጭን ሊያዛቡ ከሚችሉ የሚከተሉት ተግባራት መቆጠብ አለበት፡-

**29. <u>Ethics of Public Procurement and Property Administration</u>**

1/ Personnel engaged in public procurement and property administration shall observe the following principles of ethics in the discharge of their duties:

a) the obligation to notify any actual or possible conflict of interest and isolate oneself from any process involving such conflict,

b) not to discriminate among candidates, bidders and suppliers,

c) keep in secret any confidential information concerning the Public Body, candidate, bidder or supplier and electronic system users which he came to know of on account of his duty,

d) to reject any gift or offer of an employment opportunity, or service or anything of monetary value;

e) to report to the law enforcement agencies any intended or committed action of corruption that came to his knowledge on account of his duties and contribute to the effort to fight corruption and malpractice;

f) demonstrate concern to public money and property.

2/ Any candidate, bidder or supplier shall refrain from the following acts affecting the process of public procurement and sale of disposable property:

ሀ) የመንግሥት መሥሪያ ቤቱን ኃላፊ ወይም ሠራተኛ ተግባር ወይም ውሳኔ ለማዛባት ወይም ከግዥው አፈፃፀም እና ከሚወገድ ንብረት ሽያጭ ጋር በተያያዘ መሥሪያ ቤቱ ሊከተለው የሚገባውን አሠራር ለማስለወጥ በመደለያ መልክ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ማናቸውንም ዓይነት ስጦታ ከመስጠት ወይም ስጦታ ለመስጠት ቃል ከመግባት ወይም የሥራ ዕድል ወይም ሌላ ማናቸውንም የገንዘብ ዋጋ ያለውን ነገር ወይም አገልግሎት ከመስጠት፣

ለ) የመንግሥት ግዥ አፈፃፀምን ወይም የሚወገድ ንብረት ሽያጭን ለማዛባት በማሰብ የሀሰት ማስረጃ ከማቅረብ ወይም መገለፅ የነበረበትን መረጃ ከመደበቅ፣

ሐ) ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ ከሌላ ተወዳዳሪ ጋር በመመሳጠር የሀሰት ውድድር ከማድረግ፣

መ) በመንግሥት ግዥ ወይም በሚወገድ ንብረት ሽያጭ ሂደት ያወቃቸውን ሊፈጠሩ የታሰቡ ወይም የተፈጠሩ የሙስና ተግባራትን ለሕግ አስፈፃሚ አካላት ካለማሳወቅ እና ሙስናን እና ብልሹ አሠራርን ለመዋጋት የሚደረገውን ጥረት ካለማገዝ፡፡

a) giving directly or indirectly gifts of any kind in the form of inducement, promising to give gifts, offering employment opportunity, service or anything of monetary value with an intention to influence the decision or action of the head or staff member of the Public Body or persuade the Public Body to change its established practice of procurement and sale of disposable property,

b) presenting a falsified document or withholding information he should have disclosed with an intention to mislead proceedings of public procurement or sale of disposable property,

c) conniving with another candidate in an act of false competition in order to get unfair advantage,

d) failing to report to the law enforcement agencies any intended or committed act of corruption which he came to know of during the proceedings of public procurement or sale of disposable property and failing to contribute to the effort to fight corruption and malpractice.

## ምዕራፍ አምስት
## የግዥ ዘዴዎችና ስልቶች

### ፴. የተፈቀዱ የግዥ ዘዴዎች

፩/ በማናቸውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ግዥ አፈፃፀም የሚከተሉት የግዥ ዘዴዎች ሥራ ላይ ይውላሉ፡-

ሀ) ግልፅ ጨረታ፣
ለ) በማጣሪያ የሚከናወን ጨረታ፣
ሐ) ውስን ጨረታ፣
መ) በቀጥታ የሚፈፀም ግዥ፡፡

፪/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከተዘረዘሩት ውስጥ ለእያንዳንዱ ግዥ ተገቢ የሆነውንና ለመንግሥት ገንዘብ ከፍተኛ ጥቅም ሊያስገኝ የሚችለውን የግዥ ዘዴ በመምረጥ ተግባራዊ ማድረግ አለባቸው፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች አግባብነት ያለውን የግዥ ዘዴ ሲጠቀሙ በሥራ ላይ እንዲውል የተመረጠው የግዥ ዘዴ ተፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎችን ያሟላ መሆኑን የሚያስረዳ ሰነድ መያዝ ይኖርባቸዋል፡፡

፬/ የሚፈፀመው ግዥ ከአንድ በላይ የሆኑ የግዥ ዓይነቶችን አጣምሮ የያዘ ሲሆን ግዥው ከአጠቃላይ የግምት ዋጋ ቢንስ ከ፶ (ሃምሳ) በመቶ በላይ የሆነውን የግዥ ዓይነት ሥርዓት ተከትሎ ይፈፀማል፡፡

## CHAPTER FIVE
## METHODS AND APPROACHES OF PROCUREMENT

### 30. Authorized Methods of Procurement

1/ With the details to be prescribed in the Directives issued hereunder, the following methods of procurement shall be used in the procurement of any Public Body:

a) open tendering ,
b) selective tender,
c) limited tendering,
d) direct procurement.

2/ Public Bodies shall select and apply the appropriate Procurement method that enables to secure better maximum value for public money from among those listed under Sub-Article (1) of this Article.

3/ In applying the appropriate procurement method as per Sub Article (2) of this Article, Public Bodies shall keep record evidencing the precondition for the selected procurement method are satisfied.

4/ Where a procurement comprises more than one type of procurement, it shall be conducted following the procedures for the procurement type representing at least more than 50 (fifty) present of the estimated total cost of the procurement.

፭/በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በዚህ አዋጅ የተዘረጋውን ሥርዓት ጠብቀው ግዥ መፈፀም የማይችሉበት ሁኔታ ሲያጋጥም ግዥውን በልዩ ሁኔታ መፈፀም የሚችሉበት የአሠራር ሥርዓት በተመለከተ ሚኒስቴሩ መመሪያ ያወጣል፡፡

**፴፩. <u>ግልፅ ጨረታ</u>**

፩/ ግልፅ ጨረታ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ፍላጎት ላላቸው ሁሉም ተጫራቾች እኩል ዕድል በሚሰጥ ጨረታ ግዥ የሚፈፅምበት ዘዴ ሲሆን፣ በግልፅ ጨረታ የሚፈፀም ግዥ በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውን መደበኛ የጨረታ ሰነድ እና በዚህ አዋጅ ምዕራፍ ሰባት እና በአዋጁ መሠረት በሚወጣው የግዥ አፈፃፀም መመሪያ የተመለከተውን የጨረታ ሥርዓት ተከትሎ መከናወን አለበት፡፡

፪/የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ማናቸውንም ግዥ በግልፅ ጨረታ የግዥ ዘዴ መፈፀም ያለባቸው ሲሆን ግልፅ ጨረታን ለማስቀረት በማሰብ በአንድነት ሊፈፀሙ የሚገባቸውን ግዥዎች መከፋፈል የለባቸውም፡፡

፫/የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ከግልፅ ጨረታ ውጭ ሌሎች የግዥ ዘዴዎችን ሲጠቀሙ ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም በሚወጣው መመሪያ የተገለፁትን አሠራሮች ግምት ውስጥ ያስገባ ሆኖ የግዥ ዘዴው በግዥ ዕቅድ ውስጥ መካተት አለበት፡፡

5/ Notwithstanding the provision of Sub-Article (1) of this Article, the Ministry shall issue a Directive regarding the conditions and procedures where by Public Bodies may execute special procurement when it is ascertained that they cannot procure by the procurement methods stipulated in this Proclamation.

**31. <u>Open Tendering</u>**

1/ Open tendering is a method of procurement whereby public bodies execute procurement in such a way that gives equal opportunity to all interested bidders, and shall be conducted in accordance with the standard bid documents prepared by the Authority, the bidding procedure laid down in chapter Seven of this Proclamation and the Directive issued hereunder.

2/ Public Bodies shall use open tendering as default method of Procurement, and shall not split procurement with the sole intent of avoiding open tendering.

3/ When Public bodies employ other methods of Procurement, they shall take in to consideration the procedures laid down in the Directive issued hereunder, and the method to be used shall be included in the procurement plan.

**፴፪. በማጣሪያ የሚከናወን ጨረታ**

፩/ በማጣሪያ የሚከናወን ጨረታ የግዥ ዘዴ በጨረታ መሳተፍ የሚፈልጉ ተጫራቾችን ከአንድ ደረጃ በላይ በሆነ ውድድር በማጣራት እና በመጀመሪያው ደረጃ ያለፉ ተጫራቾችን ለቀጣይ ዙር ውድድር በመጋበዝ ከተጫራቾች መካከል የጨረታው አሸናፊ የሚመረጥበት የግዥ ዘዴ ሲሆን፣ የሁለት ደረጃ ጨረታ፣ የቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ጨረታ ወይም የፍላጎት መጠየቂያ ጨረታን ያካትታል፡፡

፪/ የሁለት ደረጃ ጨረታ ግዥ ውስብስብ ለሆኑና ዝርዝር የፍላጎት መግለጫ ማዘጋጀት አስቸጋሪ በሚሆንበት ጊዜ መሥሪያ ቤቶች ሁለት ዙር ጨረታ በማውጣት ፍላጎታቸውን ሊያሟላ የሚችል የመጫረቻ ሰነድ ያቀረበን ተጫራች በአሸናፊነት የሚመርጡበት ሥርዓት ሲሆን ከሚከተሉት ሁኔታዎች አንዱ መሟላቱ መረጋገጥ አለበት፡-

ሀ) ለሚፈለገው ግዥ በመሥሪያ ቤቱ ደረጃ የተሟላ ዝርዝር የፍላጎት መግለጫ ማዘጋጀት የማይቻል ሆኖ ሲገኝ ወይም የግዥውን ባህሪ ለይቶ ለማሳየት የማይቻል በሚሆንበት ጊዜ እና የመሥሪያ ቤቱን የግዥ ፍላጎት በከፍተኛ ደረጃ ለማሟላት የሚያስችል መፍትሄ ሲፈለግ፣

ለ) ግዥው የሚካሄደው በገበያ ላይ ሊውሉ የሚችሉ ዕቃዎችን ለማምረት ወይም የምርምር እና የልማት ወጪዎችን ለመተካት ሳይሆን የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ የምርምር፣ የሙከራ፣ የጥናት እና የልማት ሥራዎችን ለማከናወን የሚያስችል ውል መፈፀም ሲፈልግ፣

**32. Selective Tendering**

1/ Selective method of procurement is a procurement method whereby interested bidders are selected through more than one stage of competition in such a way that only shortlisted bidders in the first stage are invited to the second stage of competition so that the successful bidder is selected from among the shortlisted bidders, and it involves two stage tendering, pre-qualification bid, and expression of interests selection methods.

2/ Two stage tendering is a procurement procedure by which a Public Body selects the winning bidder that has submitted a bid responsive to the requirements of the procurement through two stage bid, in respect of complex procurements and where drawing up detailed technical specification is difficult, provided that either of the following conditions are satisfied:

a) where the Public Body does not have the technical capability to draw up sufficiently detailed specification for the required object of procurement or to identify the characteristics of the procurement and in order to obtain the most satisfactory solution to its procurement needs,

b) where the Public Body seeks to enter into a contract for the purpose of research, experiment, study or development, except where the contract includes the production of goods in quantities sufficient to establish their commercial viability or to recover research and development costs,

ሐ) ጨረታ እንዲወጣ ተደርጎ በሚፈለገው ግዥ ባህርይ ወይም ተፈጥሮ ግልፅ አለመሆን ምክንያት ተወዳዳሪዎች በጨረታው ያልቀረቡ እንደሆነ ወይም የቀረቡት የመጫረቻ ሰነዶች ውድቅ ሲደረጉ እና ይህም የሆነው መሥሪያ ቤቱ የተሟላ የፍላጎት መግለጫ ዝርዝር ማዘጋጀት ባለመቻሉ መሆኑ ሲታመን፣

መ) የሚገዛውን ዕቃ፣ ከምክር ውጭ የሆነ አገልግሎት፣ የምክር አገልግሎት ወይም የግንባታ ሥራ ባህርይ ወይም ተፈጥሮ አስመልክቶ ከተወዳዳሪዎች ጋር ውይይት ማድረግ ሲያስፈልግ፡፡

፫/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ግዥው ከሚኖረው የተለየ ባህርይ አንፃር በቅድሚያ የተወዳዳሪዎችን ብቃት መሠረት በማድረግ ግምገማ ማድረግ አለብኝ ብሎ ሲያምኑ እንደግዥው ዓይነት ብሔራዊ ወይም ዓለም አቀፍ የቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ጨረታ በማውጣት ግዥ ሊፈፅሙ ይችላሉ፡፡

፬/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የምክር እና ሌሎች አዕምሯዊ የሙያ አገልግሎት ፍላጎታቸውን ለማሟላት እንደ ሁኔታው ተወዳዳሪዎች የፍላጎት መግለጫ ወይም የመወዳደሪያ ሀሳብ እንዲያቀርቡ በማድረግ የተሻለ ብቃት ያለውን አማካሪ ድርጅት በመምረጥ ግዥ የሚፈፅሙበት አሠራር በመመሪያ ይወሰናል፡፡

c) where bid proceedings are initiated but no bids are submitted as a result of the characteristics or nature of the object of procurement not being clearly described or where all bid proposals are rejected due to failure on the part of the Public Body concerned to draw up a clear and complete specification,

d) where it is necessary to discuss with the candidates on the technical character or nature of the object, good, or service of procurement.

3/ Where, in view of the particular nature of the procurement, the Public Body finds it necessary to prequalify bidders, it may execute procurement by inviting national or international prequalification bid as the case may be.

4/ The procedure whereby Public Bodies conduct procurement to satisfy their requirement for consultancy and other professional intellectual services through expression of interest or request for proposal by selecting a bidder on the basis of their qualification shall be prescribed in the Directive to be issued hereunder.

**፴፫. ውስን ጨረታ**

፩/ የውስን ጨረታ የግዥ ዘዴ የጨረታ ማስታወቂያ ማውጣት ሳያስፈልግ ቁጥራቸው ውስን ለሆኑ ተሳታፊዎች በኤሌክትሮኒክ ሥርዓት አድራሻቸው በሚላክ ግብዣ መሠረት የሚቀርቡ ተጫራቾችን በማወዳደር የጨረታው አሸናፊ የሚመረጥበት የግዥ ዘዴ ነው፡፡

፪/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) እና (፬) የተቀመጡ ሁኔታዎች ሲሟሉ ለተገደበ ጨረታ ወይም በዋጋ ማቅረቢያ ለሚፈፀም ግዥ የተመለከቱ አሠራሮችን በመከተል ግዥ ሊፈፅሙ ይችላሉ፡፡

፫/ የተገደበ ጨረታ በቁጥር በተገደቡ ተጫራቾች መካከል ውድድር በማካሄድ ከግልፅ ጨረታ ጋር ተመሳሳይ በሆነ ሥርዓት የሚፈፀም ግዥ ሲሆን የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በተገደበ ጨረታ ግዥ መፈፀም የሚችሉት ከሚከተሉት ሁኔታዎች ውስጥ አንዱ ሲሟላ ይሆናል፡-

ሀ) ለመግዛት የተፈለገው ዕቃ፣ ከምክር ውጭ የሆነ አገልግሎት፣ የምክር አገልግሎት፣ ወይም የግንባታ ሥራ ከተወሰኑ ድርጅቶች ብቻ የሚገኝ መሆኑ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ መመሪያ በሚቀመጥ ሥርዓት ሲረጋገጥ፣

ለ) የግዥው መጠን ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ለተገደበ ጨረታ ከተቀመጠው የገንዘብ መጠን ያልበለጠ ሲሆን፣ ወይም

ሐ) የተወዳዳሪዎችን ተሳትፎ በማይገድብ ሁኔታ የተዘጋጀ የጨረታ ሰነድ በመጠቀም ቢያንስ አንድ ጊዜ ግልፅ ጨረታ ወጥቶ ተወዳዳሪ ወይም የመሥሪያ ቤቱን ፍላጎት የሚያሟላ ተጫራች ያልተገኘ ሲሆን፣

**33. Limited Tendering**

1/ Limited tendering is a procurement method whereby the winning bidder is selected through a competition involving limited number of candidates by sending invitation to their address without advertising the bid.

2/ Public Bodies may conduct procurement following the procedures set for restricted tender or request for quotation provided that the conditions stated in Sub-Article (3) and (4) of this Article are satisfied.

3/ Restricted tender is a procurement procedure conducted through competition among limited number of bidders in a manner that is otherwise similar to open tendering. Public Bodies may use restricted tendering where one of the following conditions is satisfied:

a) where it is ascertained as per the requirements to be set in a Directive issued in accordance with this Proclamation that the required goods, non consultancy services, consultancy services or works are available only from limited candidates,

b) where the estimated value of the procurement does not exceed the threshold prescribed in respect of restricted tendering in the Directive issued by the Ministry, or

c) where an open tendering floated using a non-restrictive bid document advertised at least once fails to attract candidates or the Public Body cannot secure bid that is responsive to its requirements,

፬/ በዋጋ ማቅረቢያ የሚፈፀም ግዥ እስከተቻለ ድረስ ከሦስት ያላነሱ ተወዳዳሪዎችን በመጋበዝ ወይም በመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ውሳኔ ለሁሉም ተወዳዳሪዎች ክፍት በማድረግ በሚሰበሰብ የዋጋ ማቅረቢያ ውድድር አሸናፊው ተጫራች የሚመረጥበት ሥርዓት ሲሆን ከዚህ በታች ከንዑስ አንቀጽ (፭) እስከ (፲) የተቀመጡ ድንጋጌዎች ተከትሎ ይፈፀማል፡፡

፭/ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በዋጋ ማቅረቢያ ግዥ ለመፈፀም የሚችሉት ለዚህ የግዥ ዘዴ ከተፈቀደው የገንዘብ መጠን ያልበለጠ እና የሚገዙት ዕቃዎች ለገበያ ተብለው የተዘጋጁ፣ ወዲያውኑ ጥቅም ላይ የሚውሉ ወይም በጅምላ ሊገዙ ያልቻሉ ወይም የታወቀ ዋጋ ያላቸው ዕቃዎች፣ ከምክር ውጭ የሆኑ አገልግሎቶች፣ የምክር አገልግሎቶች ወይም የግንባታ ሥራዎች ሲሆኑ ነው፡፡

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) የተቀመጠው ቢኖርም በፌደራል መንግሥት ሥር ያሉ የትምህርት ተቋማት የምግብ ግብዓት አቅርቦቶችን እና ሸቀጣ ሸቀጦችን በማምረት ዘርፍ ከተሠማሩ ህብረት ስራ ማህበራት ወይም ከአምራቾች ወይም ከአስመጪዎች በዋጋ ማቅረቢያ ግዥ የሚፈፅሙበት የተለየ አሠራር በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

፯/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) ድንጋጌ ቢኖርም የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ባላቸው የተለየ የሥራ ባህሪ ምክንያት የኤሌክትሮኒክ የግዥ ሥርዓት ወይም ሌሎች ተመሳሳይ አማራጮችን በመጠቀም ለጥናት እና ምርምር፣ እንዲሁም ለሕክምና መሣሪያዎች አገልግሎት ሊውሉ

4/ Request for quotation is a mode of procurement where the successful bidder is selected on competitive basis by request of quotation as far as possible from at least three candidates or up on the decision of the Public Body by giving equal opportunity to all interested bidders to quote their price, and shall be conducted in compliance to the provisions of Sub-Article (5) up to (10) of this Article.

5/ Public Bodies shall use request for quotations to procure goods that are readily available, for immediate use or that cannot be procured in bulk or for procurement of goods, non consultancy services, consultancy services or works for which there is a standard price, provided that the estimated value of the procurement does not exceed the threshold fixed for such method in the procurement Directive issued by the Ministry.

6/ Notwithstanding Sub-Article (5) of this Article, special procedure where educational institutions of the Federal Government buy supplies of food items and commodities from unions engaged in manufacturing same, or from manufacturers or from importers by request for quotation shall be prescribed in the Directive to be issued hereunder.

7/ Notwithstanding Sub-Article (5) of this Article, Public Bodies, given the special nature of their function, may buy inputs for research and study as well as pharmaceutical equipment, items of short shelf life, or procurements of confidential

የሚችሉ ግብዓቶችን፣ የቆይታ ጊዜያቸው አጭር የሆኑ ዕቃዎችን ወይም ሚስጥራዊነታቸው ተጠብቆ ሊፈፀሙ የሚገባቸው ግዥዎችን በዋጋ ማቅረቢያ ሊፈፅሙ ይችላሉ፡፡

nature through electronic or other similar means using request for quotation.

፰/ በዋጋ ማቅረቢያ የሚፈፀም ግዥ በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ዓመታዊ የግዥ ዕቅድ ውስጥ መካተት አለበት፡፡

8/ Procurement to be executed by means of request for quotation shall be included in the annual procurement plan of Public Bodies.

፱/ አስገዳጅ ሁኔታ በማጋጠሙ ምክንያት ከዕቅድ ውጪ የሚፈፀም የዋጋ ማቅረቢያ ግዥ በመንግሥት መሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ መፈቀድ ይኖርበታል፡፡

9/ Procurement by means of request for quotation necessitated by unforeseen circumstances and which is not included in the annual procurement plan of the Public Body shall be executed only with the approval of the head of the Public Body.

፲/ በዋጋ ማቅረቢያ ለሚፈፀም ግዥ አማራጭ ተወዳዳሪዎች እስካሉ ድረስ በተደጋጋሚ የተወሰኑ ተወዳዳሪዎችን ብቻ በመጋበዝ ማወዳደር አይቻልም፡፡ በመሆኑም የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ እስከተቻለ ድረስ በዘርፉ ለተሠማሩ ሌሎች ተወዳዳሪዎች ተመጣጣኝ የመወዳደር ዕድል መሰጠቱን ማረጋገጥ አለበት፡፡

10/ When executing procurement by means of request for quotation, Public Bodies shall not repeatedly invite same candidates to submit their quotations as long as other candidates who can supply same object of procurement are available. They shall ensure that equal opportunity of participation in public procurement is given to all candidates engaged in the business as far as possible.

**፴፬. <u>በቀጥታ የሚፈፀም ግዥ</u>**

፩/ ዝርዝር አፈፃፀሙ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው መመሪያ የሚወሰን ሆኖ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ግዥን በቀጥታ መፈፀም የሚችሉት ከሚከተሉት ሁኔታዎች አንዱ ሲሟላ ሲሆን፣ ይህ የግዥ ዘዴ በአቅራቢዎች ወይም ተወዳዳሪዎች መካከል ውድድር እንዳይኖር ወይም አንድን ተጫራች ለመጥቀም ታስቦ ጥቅም ላይ ያልዋለ መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

**34. <u>Direct Procurement</u>**

1/ Provided that the detail implementation is to be prescribed in the Directive issued hereunder, Public Bodies may use direct procurement only where one of the following condition is satisfied, provided that Public Bodies have to ensure that they have not resorted to this method to circumvent competition or to favor a candidate.

ሀ) ዕቃው፣ ከምክር ውጭ የሆነ አገልግሎት፣ የምክር አገልግሎቱ ወይም የግንባታ ሥራው የሚገኘው ከአንድ ተወዳዳሪ ብቻ ሲሆን፣

ለ) ግዥው በጣም አስቸኳይ ከመሆኑ የተነሳ ወዲያውኑ ካልተፈፀመ በሰው ሕይወት እና ንብረት ላይ ከባድ ችግር የሚፈጥርና በመሥሪያ ቤቱ ሥራ አፈፃፀም ላይ ጉዳት የሚያስከትል መሆኑ ሲረጋገጥ፣

ሐ) መሥሪያ ቤቱ ባዘጋጀው የጨረታ ሰነድ ችግር ምክንያት ካልሆነ በስተቀር የሚፈለገው አቅርቦት በሌሎች የግዥ ዘዴዎች ማሳካት ያልተቻለ መሆኑ ሲረጋገጥ፣

መ) አስቀድሞ ለተገዙ ዕቃዎች ወይም ከምክር ውጭ የሆኑ አገልግሎቶች ተጓዳኝ ወይም መለዋወጫ ዕቃዎችን ወይም ተጨማሪ አገልግሎቶችን መግዛት ሲያስፈልግ እና እነዚህን ተጓዳኝ ወይም መለዋወጫ ዕቃዎችን ወይም ተጨማሪ አገልግሎቶችን ከሌላ ተወዳዳሪ መግዛት የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ከሚጠቀምበት ዕቃ ወይም አገልግሎት ጋር የማይጣጣም በመሆኑ ምክንያት ከመጀመሪያው አቅራቢ መግዛት የግድ ሲሆን፣

ሠ) በግዥ መመሪያ የሚደረገው ገደብ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ያልታሰቡ ሁኔታዎች በማጋጠማቸው ምክንያት በመጀመሪያ ውል ውስጥ ያልተካተቱ ተጨማሪ የግንባታ ሥራዎች ማሠራት አስፈላጊ ሲሆንና በቴክኒክ ወይም በኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ምክንያት እነዚህን ተጨማሪ የግንባታ ሥራዎች ከመጀመሪያው ውል ነጥሎ ማሠራት የማይቻል ሲሆን፣

a) where the good, non-cosultancy service, consultancy service or the works can be supplied or provided only by one candidate,

b) where the procurement is needed as a matter of urgency and it is ascertained that unless procured immediately would endanger human lives and property as well as seriously affects the performance of that Public Body,

c) where the Public Body cannot obtain the required object of procurement using other procurement methods provided that the failure to attract bidders is not due to problem in the bid document,

d) where there is a need for supply of spare parts, accessories, or delivery of services for goods or services already procured and where procuring such spare parts, accessories or services from another supplier would not meet the requirements of compatibility with goods or services of the Public Body and for this reason it becomes necessary to obtain the required spare parts, accessories or services from the original supplier,

e) subject to the limits set in the procurement Directive, where unforeseen circumstances give rise to the need for additional works which were not included in the initial contract and the separation of the additional works from the initial contract would not be feasible for technical or economic reasons,

ረ) በግዥ መመሪያ የሚደረገው ገደብ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አሸናፊው በውድድር ከተመረጠ በኋላ ከተፈረመ ውል ውጭ የመጀመሪያው ግዥ የተከናወነባቸው ከምክር ውጭ የሆነ አገልግሎት ወይም የምክር አገልግሎት ሥራዎች ወይም አቅርቦቶች ውል አጥጋቢ በሆነ ሁኔታ መጠናቀቁ እና ቁጠባንና ቅልጥፍናን የሚያስገኝ መሆኑ በመረጋገጡ ቀደም ሲል ውሉን ከፈረመው አቅራቢ እንዲሠራ ወይም እንዲቀርብ ማድረግ አስፈላጊ ሲሆን፣

ሰ) የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ለሚኖራቸው የተለየ የግዥ ፍላጎት ማሟያ ከገበያ በለቀማ ግዥ መፈፀም የሚያስገድዳቸው ሁኔታ ሲፈጠር፣ ወይም በግዥ መመሪያው ከሚወሰን የገንዘብ መጠን ያልበለጠ ጥቃቅን ግዥዎች ሲሆኑ፣

ሸ) ሽያጩ ለአጭር ጊዜ የሚቆይ፣ ለመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ልዩ ጥቅም በሚያስገኝ ሁኔታ የሚፈፀም እና በመደበኛ አቅራቢነት ከተሰማሩ ተወዳዳሪዎች ሊገኝ የማይችል ዕቃ ወይም አገልግሎት ግዥ ሲሆን፣

ቀ) የመንግሥት ባለበጀት መሥሪያ ቤቶች ለሚኖራቸው የዕቃና አገልግሎት ግዥ ፍላጎት ወጪን በመሸፈን ከመንግሥት ባለበጀት መሥሪያ ቤት ግዥ መፈፀም ሲያስፈልግ፣

በ) መሥሪያ ቤቶች ባላቸው የተለየ የሥራ ባህርይ ምክንያት በውድድር ሊገኙ የማይችሉ ለጥናት እና ምርምር፣ ለሕክምና መሣሪያዎች አገልግሎት የሚውሉ ግብዓቶችን እንዲሁም ሚስጥራዊነታቸው ተጠብቆ ሊፈፀሙ የሚገባቸው ግዥዎችን ሌላ የተለየ አማራጭ ባለመኖሩ ምክንያት

f) subject to the limits set in the procurement Directive, to obtain non-cosultancyservice or consultancy service of the same or similar kind to that previously procured by the Public Body under a contract awarded on competitive basis, where the previous contract has been satisfactorily performed and the provision of the non-cosultancyservice or consultancy service by the same supplier is likely to lead to gains in economy and efficiency,

g) where a situation arises in which piecemeal shopping becomes the feasible alternative to address the special procurement need of a Public Body; or to obtain goods of small value falling within the range to be fixed in the Directive issued hereunder,

h) for procurement of goods or service available for a short period of time, for goods or service that cannot be obtained from candidates who are regularly engaged in the provision of such goods or service,

i) where it is necessary for a Public Body to obtain goods or services from another Public Body at break-even price,

j) to obtain goods that are used for research and study, inputs for use of medical equipment or goods that have to be obtained confidentially, where such goods cannot be procured on competitive basis because of the special requirement of the Public Body arising from the character of

ከአንድ አቅራቢ በቀጥታ ግዥ መፈፀም አስፈላጊ መሆኑ በበላይ ኃላፊው ሲታመንበት፤

ተ) በሌላ ግዥ ፈፃሚ መሥሪያ ቤት ቀደም ሲል በግልፅ ጨረታ የግዥ ዘዴ ከተገዙ ዕቃዎች፣ ወይም ከምክር ውጭ ከሆኑ አገልግሎቶች ጋር በዓይነት እና በዋጋ አንድ ዓይነት የሆነ ግዥዎችን ቀደም ሲል አቅርቦቱን ከፈፀመው አቅራቢ ለአንድ ጊዜ ብቻ መፈፀም ከጊዜ፣ እንዲሁም ለመሥሪያ ቤቱ ከሚሰጠው ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ አንፃር አዋጭ መሆኑ በመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ ሲታመንበት፣

ቸ) ዋጋቸው በመንግሥት የሚወሰን ዕቃዎች እና ከምክር ውጭ የሆኑ አገልግሎቶች ሲሆኑ፣

ነ) ዕቃው፣ ከምክር ውጭ የሆነ አገልግሎቱ ወይም የምክር አገልግሎት በሚታወቁ እና ሚኒስቴሩ በየጊዜው በሚለየው የድርጅቶች ዝርዝር ውስጥ በተካተቱ ድርጅቶች በበይነ-መረብ ገበያ የሚገኝ፣ ዋጋው አስቀድሞ በበይነ መረብ ለሕዝብ ይፋ የተደረገ፣ ግዥው በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ብቻ የሚፈፀም እና የመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ በዚህ መልኩ ግዥው መፈፀሙ የመንግሥትን እና የመሥሪያ ቤቱን ጥቅም የሚያስጠብቅ መሆኑን ሲያምንበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ሰ) እና (ነ) መሠረት በቀጥታ ለሚፈፀሙ ግዥዎች የፅሑፍ ውል መዋዋል አያስፈልግም፡፡

፫/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች መሠረት የሚፈፅሚቸውን ግዥዎች በሌሎች ዘዴዎች መፈፀም የማይቻል መሆኑን የሚያረጋግጥ፣ እንዲሁም ግዥውን

its functions and the head of the Public Body approves the use of single source procurement on that ground,

k) to obtain from the same supplier and for the same price, goods or non- consultancy service of the same kind as those another Public Body has previously procured on open tendering, provided that execution of such procurement is allowed only for one time, and the head of the Public Body is satisfied that such procurement leads to gain in economy and efficiency,

l) where the price of the good or non-cosultancyservices to be procured is fixed by the Government,

m/ where the good, non -consultancy service or consultancy service is obtained on online market, its price is made public on online market by known campanies listed by the Ministry, where it can be electronically procured and the head of the Public Body is satisfied that such procurement brings gain and ensures institutional and governmnt interest.

2/ It shall not be necessary to conclude a contract in writing in respect of direct procurement effected in accordance with paragraph (g) and (m) of Sub-Article (1) of this Article.

3/ Public Bodies have to keep explanatory note supported by a documentary record evidencing that the procurements executed in accordance with the provisions of this

ከአንድ አቅራቢ ለመፈጸም ያስፈለገበትን አሳማኝ ምክንያት፣ ተፈላጊ ጥራት፣ ብዛት፣ የማቅረቢያ ጊዜና ሁኔታዎች የሚያስረዳ በሰነድ የተደገፈ መግለጫ መያዝ አለባቸው፡፡

፬/ ከአንድ አቅራቢ በቀጥታ በሚፈፀም ግዥ ድርድር የሚደረግባቸው ሁኔታዎች እና ዝርዝር ሂደት በመመሪያ ይወሰናል፡፡

**፴፭. <u>የገበያ አማራጮች</u>**

፩/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ከሚፈፅሙት ግዥ ዓይነት፣ ባህሪ እና የገንዘብ መጠን በመነሳት ብሔራዊ ወይም ዓለም ዓቀፍ የገበያ አማራጭን በመጠቀም ግዥ ሊፈፅሙ ይችላሉ፡፡

፪/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በብሔራዊ ግልፅ ጨረታ የገበያ አማራጭ ግዥ ለመፈፀም የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላታቸውን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡-

ሀ) የግዥው ግምታዊ ዋጋ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው የግዥ አፈፃፀም መመሪያ ለዓለም አቀፍ ግልፅ ጨረታ ከተፈቀደው የገንዘብ ጣሪያ በታች መሆኑን፣ ወይም

ለ) የግዥው ግምታዊ ዋጋ በግዥ አፈፃፀም መመሪያው ለብሔራዊ ግልፅ ጨረታ ከሚወሰነው የገንዘብ ጣሪያ በላይ ቢሆንም፣ የሚፈለገውን አቅርቦት ማግኘት የሚቻለው በሀገር ውስጥ ብቻ መሆኑን፡፡

፫/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በዓለም አቀፍ ግልፅ ጨረታ የገበያ አማራጭ ግዥ ለመፈፀም ከሚከተሉት ሁኔታዎች ውስጥ አንዱ መሟላቱን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡-

Article cannot be executed by other methods, and the reason justifying the use of direct procurement as well as the required quality, quantity, delivery period and other conditions thereof.

4/ The conditions and details of conducting negotiation in direct procurement shall be prescribed in the Directive to be issued hereunder.

**35. <u>Market Options</u>**

1/ Public Bodies may execute procurement using national or international market options as the case may be based on the type, nature and value of the procurement.

2/ Public Bodies shall ascertain that the following conditions are satisfied when executing procurement using open national tender market options:

a) that the estimated value of the procurement is below the threshold prescribed for international open tender in the procurement Directive issued hereunder, or

b) that the required object of procurement is available only locally notwithstanding that the estimated value of the procurement is above the threshold prescribed for national open tender in the Directive issued hereunder.

3/ Public bodies shall ascertain that the following conditions are satisfied when executing procurement using open international tender market options:

ሀ) የግዥው ግምታዊ ዋጋ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው መመሪያ ለብሔራዊ ግልፅ ጨረታ ከተመለከተው የገንዘብ ጣሪያ በላይ መሆኑን፣ ወይም

ለ) የግዥው ግምታዊ ዋጋ በግዥ አፈፃፀም መመሪያው ለዓለም አቀፍ ግልፅ ጨረታ ከሚወሰነው የገንዘብ ጣሪያ በታች ቢሆንም፣ የሚፈለገውን ግዥ በሀገር ውስጥ መፈፀም የማይቻል መሆኑን፡፡

፬/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ እና ፫ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የውጪ ኩባንያዎች እንዲሳተፉ ካልተደረገ በስተቀር ውጤታማ የሆነ ውድድር ሊኖር እንደማይቻል ሲታመንበት የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ከግልፅ ጨረታ ውጪ ሌሎች የተፈቀዱ የግዥ ዘዴዎችን በመጠቀም በብሔራዊ ወይም በዓለም አቀፍ የገበያ አማራጮች ግዥ መፈፀም ይችላሉ፡፡

፭/ በዚህ አዋጅና በአዋጁ መሠረት በሚወጣው መመሪያ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) በተገለፀው መሠረት ሌሎች የግዥ ዘዴዎችን በመጠቀም ከዓለም አቀፍ ገበያ ግዥ መፈፀም የሚቻለው በዚህ አዋጅ እና ይህን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣው መመሪያ ለየግዥ ዘዴዎች የተቀመጠውን አሠራር ተከትሎ መሆን አለበት፡፡

፮/ ባለሥልጣኑ ከሚኒስቴሩ እና ከሚመለከታቸው ሌሎች አካላት ጋር በመመካከር የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በዓለም አቀፍ ጨረታ ወቅት ሊጠቀሙ የሚገባቸውን ዓለም አቀፍ የንግድ ቃላትና ሁኔታዎች ይወስናል፡፡

a) that the estimated value of the procurement is above the threshold prescribed for national open tender by the procurement Directive issued hereunder, or

b) that the required object of procurement is not available locally notwithstanding that the estimated value of the procurement is below the threshold prescribed for international competitive bidding in the Directive issued hereunder.

4/ Without Prejudice to the provision of Sub-Article (2) and (3) of this Article, Public Bodies may execute procurement using international or national market options by means other than open tendering where the participation of foreign companies is believed to be necessary to carry out competitive and effective procurement;

5/ Unless otherwise provided in this Proclamation or the Directive issued hereunder, in carrying out Procurement using international market options by other methods of procurement pursuant to Sub-Article (4) of the this Article, the conditions prescribed for each method of procurement shall be complied with.

6/ The Authority shall, in consultation with the Ministry and other appropriate entities, determine the international commercial terms and conditions to be used by Public Bodies in international tendering.

## ፴፮. የግዥ ስልቶች

፩/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች እንደ ግዥው ባህሪ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ስልቶች በመጠቀም ግዥ መፈፀም ይችላሉ፡፡

ሀ) ስትራቴጂዊ ግዥ፣

ለ) በማዕቀፍ የሚፈፀም ግዥ፣

ሐ) የጋራ ግዥ፣

መ) በሊዝ ስምምነት የሚፈፀም ግዥ፣

ሠ) በራስ ኃይል የሚፈፀሙ ሥራዎች ግዥ፣

ረ) የተርንኪ ግዥ፣

ሰ) የኤሌክትሮኒክ ልውጥ ሐራጅ ጨረታ፡፡

፪/ ሀገራዊ ጠቀሜታ ያላቸው በመሆናቸው በማዕከል የሚፈፀሙ ስትራቴጂያዊ ግዥዎች በሚኒስቴሩ የሚወሰኑ ሲሆን ግዥው ለዚህ ዓላማ በደንብ ቁጥር ፩፻፹፬/፪ሺ፪ በተቋቋመው የመንግሥት መሥሪያ ቤት ይከናወናል፡፡

፫/ የማዕቀፍ ግዥ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ተከታታይነት ያላቸው የተናጠል ፍላጎቶቻቸውን ለማሟላት ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ መሥሪያ ቤቶች በተከታታይ የሚፈለጉ ተመሳሳይነት ያላቸው ዕቃዎችና ከምክር ውጭ የሆኑ አገልግሎቶች ግዥ በጥቅል በማዕከል የሚፈጸምበት የግዥ ስልት ሲሆን በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፱ እና አንቀጽ ፷ ላይ የተደነገገውን አሠራር ተከትሎ ይፈፀማል፡፡

፬/ የጋራ ግዥ ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ መሥሪያ ቤቶች ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፱ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት በሚያወጣው ዝርዝር ያልተካተቱና የጋራ ፍላጎታቸውን ለማሟላት በሚወጣ ጨረታ መሠረት አሸናፊ ከሚሆነው ተጫራች ጋር ውል በመያዝ የሚፈፀም የግዥ ስልት ነው፡፡

## 36. Procurement Approaches

1/ Public Bodies may execute procurement using the procurement approaches listed hereunder depending on the nature of the procurement.

a) strategic procurement,

b) framework procurement,

c) joint procurement,

d) lease procurement,

e) own force account procurement,

f) turnkey procurement,

g) electronic reverse auction.

2/ Strategic procurements which have national significant shall be carried out centrally by the Public Body established for this purpose by Regulation no. 184/2010, because of their national significance shall be determined by the Ministry.

3/ Framework procurement is a procurement approach whereby Public Bodies carryout procurements of goods and services to meet their recurrent needs, or procurement of similar items that may be recurrently required by more than one Public Body and procured in bulk centrally and it shall be carried out in accordance with the procedure prescribed under Article 59 and 60 of this Proclamation.

4/ Joint procurement is an approach where two or more Public Bodies execute procurement of items of common requirement not included in the list that is to be issued by the Authority pursuant to Sub-Article (3) of Article 59 of this Proclamation, by entering in to a contract with the winner of the bid.

፭/የዚህ ምዕራፍ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ለመንግሥት የሚያስገኘውን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ከግምት በማስገባት ባላቸው የስራ ባህርይ ምክንያት በሊዝ ስምምነት መሠረት ግዥ የሚፈፅሙበት ሁኔታ እና ዝርዝር አሠራር በዚህ አዋጅ መሠረት በሚኒስቴሩ በሚወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

፮/የመንግሥት መሥሪያ ቤት የራሱን የሰው ኃይልና መሣሪያ በመጠቀም ያለ ጨረታ ሂደት በራሱ ግንባታን ወይም ከምክር ውጭ የሆኑ አገልግሎት ሥራን የሚያከናውንበት የግዥ ስልት ዝርዝር አፈፃፀም በመመሪያ ይወሰናል፡፡

፯/የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ራሳቸውን ችለው በተለያየ ጨረታ ሊፈፀሙ የሚችሉ የአንድ ፕሮጀክት አካል የሆኑ ግዥዎችን በማቀናጀት በአንድ ጨረታ መፈፀሙ አዋጭና ጠቀሜታ እንደሚኖረው ሲያምኑ ግዥውን በተርንኪ ግዥ መፈፀም የሚችሉ ሲሆን ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

፰/የኤሌክትሮኒክ ልውጥ ሐራጅ ጨረታ የኤሌክትሮኒክ ዘዴ በመጠቀም ተጫራቾች በመሥሪያ ቤቶች ለሚፈለጉ ዕቃዎችና ከምክር ውጭ የሆኑ አገልግሎቶች ዋጋቸውን እየቀነሱ የሚወዳደሩበት ስልት ሲሆን ዝርዝር አሠራሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

5/ Without prejudice to the provisions of this chapter, the conditions and procedure whereby Public Bodies execute procurement on contract of lease, because of the character of their function and taking in to consideration the economic benefit that may be derived by the government shall be prescribed by the Directive to be issued by the Ministry.

6/ The procurement approach whereby Public Bodies carryout works and non-cosultancyservices without tendering, using its human resource and machineries shall be determined in the Directive to be issued hereunder.

7/ With the details to be prescribed in the Directive to be issued hereunder, where it is believed that conducting procurements of components in a projects under a single tender, which would otherwise be procured separately, is feasible and beneficial, public bodies may execute the procurement on turnkey basis.

8/ With the details to be prescribed in the Directive to be issued hereunder, Electronic Reverse Auction is an approach where bidders compete by quoting reduced price for the required goods and non-cosultancyservices using electronic means.

## ምዕራፍ ስድስት
## የመንግሥት ንብረት አያያዝ አጠቃቀምና አወጋገድ

**፴፯. አጠቃላይ መርህ**

እያንዳንዱ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ የመንግሥት ንብረት በአግባቡ የመያዝ እና የመጠቀም፣ የመከታተል እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም በወቅቱ የማስወገድ ተግባር መከናወኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

**፴፰. ንብረትን የመያዝ ዓላማ**

ማንኛውም የመንግሥት ንብረት በባለቤትነት የመያዝ ብቸኛ ዓላማ የፀደቁትን የመሥሪያ ቤቱን ግቦች ለማስፈጸም እና አገልግሎቱን በማፋጠን ውጤታማና ብቁ ለማድረግ መሆን አለበት፡፡

**፴፱. አጠቃቀም እና ጥገና**

፩/ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ በመሥሪያ ቤቱ ሥር ላሉ ተሽከርካሪዎች እና ሌሎች ማሽነሪዎች አገልግሎት የሚውሉ ነዳጅ፣ ዘይትና ቅባቶች፣ እንዲሁም ሌላ ማንኛውንም የመንግሥት ንብረት የመሥሪያ ቤቱን ኃላፊነት ውጤታማ በሚያደርግ መልኩ አገልግሎት ላይ ማዋሉን ማረጋገጥ አለበት፡፡

፪/ ዝርዝሩ በመመሪያ የሚወሰን ሆኖ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ የመንግሥት ንብረት ኢኮኖሚያዊና ውጤታማ በሆነ መንገድ አገልግሎት እንዲሰጥ ለተሽከርካሪዎች፣ ለማሽነሪዎች እና ሌሎች ቋሚ ንብረቶች ተገቢ የጥገና እና የእንክብካቤ ሥርዓት መዘርጋት አለበት፡፡

## CHAPTER SIX
## HANDLING, USE AND DISPOSAL OF PUBLIC PROPERTY

**37. General Responsibility**

The head of each Public Body shall ensure that property at the disposal of the Public Body is properly handled, used, accounted for and where necessary, disposed of in due time in accordance with the Directive issued hereunder.

**38. Purpose of Acquisition**

The acquisition of any public property shall be for the sole purpose of facilitating the implementation of the approved goals and effective and efficient delivery of services of the Public Body.

**39. Use and Maintenance**

1/ The head of a Public Body shall ensure that any property at the disposal of the Public Body including fuel, lubricant, and oil obtained for operational use of vehicles and machinery in the service of the Public Body are used as productively and economically as possible in discharging the duties and responsibilities of the Public Body.

2/ With the details to be prescribed in the Directive to be issued hereunder, the head of a Public Body shall establish a proper maintenance and handling system for vehicles, machinery and other fixed assets of the Public Body to ensure economic and effective use of such fixed assets.

፫/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ተሽከርካሪዎች፣ ማሽነሪዎች፣ ፕላንቶች እና በከፍተኛ ወጪ የሚገዙ ንብረቶች የመድህን ዋስትና ሽፋን እንዲያገኙ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡

፬/ ከባለሥልጣኑ ፈቃድ ካልተሰጠ በስተቀር የተሽከርካሪ፣ የማሽነሪ፣ እንዲሁም የኤሌክትሮኒክስ ንብረቶችን አካል ፈታትቶ ለሌላ ቋሚ ንብረት አካል አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው፡፡

## ፵. የመንግሥት ንብረት ስለማስተዳደር

፩/ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ፡-

ሀ) የመንግሥት ንብረት አስተዳደር የሕይወት ዘመን ሥርዓትን የተከተለ መሆኑን፣

ለ) በመሥሪያ ቤቱ ሥር ያለ የመንግሥት ንብረት ከተያዘበት፣ ከአገልግሎት ውጪ እስከሆነበት ቀን ድረስ ንብረቱ አገልግሎት ያቋረጠበትን ጊዜ፣ የንብረቱን ዓይነት፣ ብዛቱን እና ያስከተለውን ወጪ የሚያሳይ ዝርዝር ተመዝግቦ መያዙን፣

ሐ) ማናቸውንም ቋሚ ንብረት የመጠበቅ ኃላፊነት በመጀመሪያ ደረጃ ንብረቱን እንዲገለገሉበት ኃላፊነት ለተሰጣቸው ሠራተኞች መሰጠቱን እና በቋሚ ንብረት መዝገብ የጠባቂዎቹ ዝርዝር እና በእነርሱ ጥበቃ ሥር ያሉት ቋሚ ንብረቶች የሚገኙበት ቦታ መመዝገቡን፣

መ) ወዲያውኑ ጥቅም ላይ የማይውሉ አላቂ ንብረቶች በመሥሪያ ቤቱ የሚመለከተው የንብረት ሥራ ክፍል በንብረት ዝርዝር መዝገብ ውስጥ መካተታቸውንና ለጥበቃቸው ኃላፊ መመደቡን፣

3/ Public Bodies may contract insurance coverage for vehicles, machineries, plants and properties of high value.

4/ Public Bodies may not use parts of vehicles, machineries, as well as electronics products in the maintenance of another fixed asset in their possession without prior permission of the Authority in accordance with the Directive to be issued hereunder.

## 40. Administration of Public Property

1/ The head of a Public Body shall ensure that:

a) a life-time approach is used in the administration of public property,

b) record is properly maintained showing the description, quantity, date of decommissioning and cost associated with fixed assets, from acquisition of such fixed assets to the end of their life time,

c) the custodial responsibility for each fixed asset rests primarily on the staff using such fixed asset and that the name of the custodian is recorded in the register of fixed assets at the place where the property under custody is located,

d) custodial responsibility for supplies not acquired for immediate consumption are recorded in the supplies inventories and custodial responsibility is assigned for such inventories,

ሠ) ልዩ ቋሚ ንብረቶች በተጠቃሚዎች ካርድ ላይ ተመዝግበው የተለየ ቁጥጥር የሚደረግባቸው መሆኑን፣

ማረጋገጥ አለበት፡፡

፪/ ማንኛውም የመንግሥት ንብረት ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ መቆጠር አለበት፡፡

፫/ የመንግሥትን ንብረት ትክክለኛ ዋጋ ለመወሰን ሳይቻል ሲቀር ግምቱ በዚህ አዋጅ በሚወጣው መመሪያ መሠረት ይወሰናል፡፡

፬/በመንግሥት ቋሚ ንብረት ላይ የእርጅና ቅናሽ ይሰላል፡፡

፭/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በተፈጥሯዊ ባህርያቸው ምክንያት በትነት እና በፍሳሽ የሚፈጠሩ ብክነቶችን ለማካካስ ለዚህ ዓላማ ማስፈፀሚያ በዚህ አዋጅ በሚወጣው መመሪያ መሠረት ተፈፃሚ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

**፵፩. መጠበቅና መንከባከብ**

ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሠራተኛ ተረክቦ የሚገለገልባቸውን የመንግሥት ንብረቶች የመጠበቅና የመንከባከብ ኃላፊነት አለበት፡፡

**፵፪. የመንግሥት ንብረት ስለማስወገድ**

የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ ለመሥሪያ ቤቱ አገልግሎት የማይሰጡ የመንግሥት ንብረቶች በዚህ አዋጅ መሠረት በወቅቱ መወገዳቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

e) special fixed assets are captured by entry in the bin card assigned for each user.

2/ All inventories of public property shall be physically verified against records at least annually.

3/ Where the actual cost of public property cannot be determined, it shall be estimated in accordance with the Directive to be issued hereunder.

4/ Depreciation shall be calculated on fixed assets in accordance with the Directive to be issued hereunder.

5/ Public Bodies shall make provision for loss arising from evaporation or spillage in accordance with the Directive to be issued hereunder for this purpose.

**41. Protection and Preservation**

Any employee of a Public Body is responsible for the protection and preservation of public property in his custody.

**42. Disposal of Public Property**

The head of a Public Body shall ensure that public property at the disposal of the Public Body which are not useful to the Public Body are disposed of in due time in accordance with this Proclamation and the Directive to be issued hereunder.

**፵፫. ንብረትን ስለማስወገድ መሟላት የሚገባቸው ሁኔታዎች**

ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ንብረት ማስወገድ የሚችለው ከሚከተሉት ሁኔታዎች አንዱ ተሟልቶ ሲገኝ ብቻ ነው፡-

፩/ ንብረቱ ለመሥሪያ ቤቱ ዓላማዎች የማይፈለግ ሲሆን፤

፪/ ንብረቱን ይዞ መቀጠል የሚያስከትለው ወጪ ከፍተኛ በመሆኑ ንብረቱን ማስወገድ የተሻለ አማራጭ ሆኖ ሲገኝ፤

፫/ በልዩ ልዩ ምክንያት ንብረቱ የሚፈለግበትን አገልግሎት በብቃት መስጠት የማይችል ወይም ከአገልግሎት ውጪ ሲሆን፤ ወይም

፬/ መሥሪያ ቤቱ ከሚኖረው የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ የሥራ ዕቅድ ንብረቱ ትርፍ መሆኑ ሲታመን፡፡

**፵፬. የተፈቀዱ የንብረት ማስወገጃ ዘዴዎች**

የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ንብረት በሚያስወግዱበት ወቅት የሚከተሉትን አሠራሮች መከተል ይኖርባቸዋል፡-

፩/ በማናቸውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ይዞታ ሥር ያለን ንብረት ለማስወገድ እንደ ንብረቱ ባህርይ የሚከተሉት የንብረት ማስወገጃ ዘዴዎች ሥራ ላይ ይውላሉ፡-

ሀ) ለሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት በማዛወር ወይም በማስተላለፍ፣

ለ) ባሉበት ሁኔታ ወይም እንደ ሁኔታው ፈታቶ ለሕዝብ በኤሌክትሮኒክ ሥርዓት መሠረት በጨረታ ወይም በሐራጅ በመሸጥ፣

ሐ) ንብረቱን በስጦታ በማስተላለፍ፣

መ) ንብረቱን በመቅበር ወይም በማቃጠል፣

ሠ) ንብረቱን በማፈን፣ በማምከን ወይም በመቀየጥ፣

ማስወገድ፡፡

**43. Conditions to be Fulfilled to Dispose of Public Property**

Any Public Body may dispose of public property only where one of the following conditions is satisfied:

1/ Where the property is no longer needed for the objectives of the Public Body;

2/ Where the cost of retaining the property is so high that disposing of the property is economically a better option;

3/ Where the property does not function properly or becomes out of use for various reasons; or

4/ Where it is established that the property is surplus in view of the Public Body's long, medium and short term work plans.

**44. Authorized Methods of Property Disposal**

Public Bodies shall comply with the following procedures when disposing of property:

1/ In disposing of property in any Public Body, the following methods of disposal shall be applied based on the nature of the property:

a) by transferring the property to another Public Body,

b) by selling the property by bid or auction to the public using the electronic system in the condition in which it is or parts thereof,

c) by transferring the property as donation,

d) by burying or burning the property,

e) by suppressing, neutralizing or diluting.

፪/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ከላይ በተቀመጡ ማስወገጃ ዘዴዎች ንብረት ሲያስወግዱ ለመልሶ መጠቀም ቅድሚያ መስጠት አለባቸው፡፡

፫/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተቀመጡት የንብረት ማስወገጃ ዘዴዎች የተወገዱ ንብረቶችን ዝርዝር፣ እንዲሁም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፮ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሰረት ከማስወገድ የተገኘውን ገቢ የሚያሳይ ሪፖርት ለባለሥልጣኑ መላክ ይኖርባቸዋል፡፡

**፵፭. <u>ንብረትን በማስወገድ ሂደት ሊወሰዱ የሚገባቸው ጥንቃቄዎች</u>**

ዝርዝር አፈፃፀሙ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው የንብረት አስተዳደር መመሪያ የሚወሰን ሆኖ ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ንብረትን በማስወገድ ሂደት የሚከተሉትን ጥንቃቄዎች ማድረግ አለበት፡-

፩/ የንብረቱ ሕጋዊ ባለቤት ማን እንደሆነ መለየት፤ በይዞታው ሥር ለሚገኝ ንብረት የባለቤትነት ማስረጃ ማቅረብ የማይችል ከሆነ በገዥው ላይ ለሚቀርብ የይገባኛል ጥያቄ ዋቢ በመሆን ንብረቱን ማስወገድ፤

፪/ ሕንፃና ተመሳሳይ ግንባታዎች የባለቤትነት መብት የተሰጠው ለፌደራል መንግሥት በመሆኑ እነዚህን ንብረቶች ማስወገድ የሚፈልግ ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሚኒስቴሩን ማስፈቀድ፤

2/ In disposing of public property using the afore-stated methods, Public Bodies should give priority to recycling.

3/ Public Bodies shall report to the Authority the list of property disposed of by methods listed in Sub-Article (1) of this Article and the proceeds from sale of disposable property pursuant to Sub-Article (2) of Article 46 of this Proclamation.

**45. <u>Precautions to be Taken in the Process of Property Disposal</u>**

Provided the details to be prescribed in the Directive issued hereunder, Public Bodies shall observe the following precautionary measures when disposing of property:

1/ Identify the legal owner of the property to be disposed of; provided that, in default of documentary proof of ownership for the property under its possession, may transfer the property by warranting the buyer against possible dispossession by a third party;

2/ Secure authorization from the Ministry to dispose of public buildings and similar structures as ownership of such property lies with the Federal Government;

፫/ የሚወገዱት ንብረቶች በባህርያቸው ልዩ ጠቀሜታ ያላቸው ወይም በጤና ወይም በአካባቢ ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ ጊዜያቸው ያለፈባቸው ኬሚካሎች፣የኬሚካል ውጤቶች እና ከአገልግሎት ውጭ የሆኑ የኤሌክትሮኒክ ዕቃዎች፣ መድኃኒቶች፣ ጨረራ አመንጪ ወይም የመሳሰሉት ሲሆኑ በአወጋገዱ ላይ ከሚመለከተው አካል ጋር በመመካከር ወይም አስፈላጊውን እገዛ በመጠየቅ ማስወገድ፡፡

**፵፮. <u>ንብረትን በማስወገድ ስለሚገኘው ገቢ</u>**

፩/ በፋይናንስ አስተዳደር ሕጉ ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግሥት ንብረት በማስወገድ የተገኘው ገቢ ንብረቱን የሚያስወግደው የባለበጀት መንግሥት መሥሪያ ቤት ሲሆን ለማዕከላዊ ግምጃ ቤት፣ የመንግሥት የልማት ድርጅት ሲሆን ለድርጅቱ ገቢ መደረግ አለበት፡፡

፪/ ንብረቱን የሚያስወግደው በመንግሥት በጀት የሚተዳደር የመንግስት መሥሪያ ቤት ሲሆን የተወገደው የመንግሥት ንብረት መግለጫ እና ንብረቱን በማስወገድ የተገኘው ገንዘብ በዓመታዊ የመንግሥት ሒሳብ ሪፖርት ውስጥ መጠቃለል አለበት፡፡

**፵፯. <u>መሠረዝ</u>**

፩/ ማንኛውም የመንግሥት ንብረት፡-

ሀ) ለመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ወይም ለሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የማይጠቅምና ዋጋ የማያወጣ መሆኑ ሲረጋገጥ፣

ለ) ከጥቅም ውጪ ሲሆን ወይም ሲጎድል፣

3/ Consult with or seek the assistance of the appropriate entities in disposing of properties of special significance or that are harmful to health or the environment such as expired chemical substances or products, drugs or discarded radiation emitting or electronic equipment or substances.

**46. <u>Proceeds from Property Disposal</u>**

1/ Without prejudice the Financial Administration law, proceeds from the disposal of public property shall be deposited into the account of the central treasury where the disposing entity is a budgetary Public Body, and where the disposing entity is a public enterprise, to the account of the enterprise disposing of the property.

2/ The list of property disposed of and the proceeds from sale of disposable property in any fiscal year shall be included in the annual public accounts report where the disposing entity is budgetary Public Body.

**47. <u>Write Off</u>**

1/ Public property shall be written off for any of the following reasons፡

a) where it is considered to be of no use to the Public Body or to any other Public Body and has no scrap value,

b) where the property is destroyed or partially lost,

ሐ) ሲሠረቅ ወይም በማናቸውም ሌላ ተመሳሳይ ምክንያት ሲጠፋ ወይም ሲቃጠል እና በሚመለከተው የሕግ አካል ሲረጋገጥ፣

ከንብረት መዝገብ ይሠረዛል፡፡

፪/ ማናቸውም የመንግሥት ንብረት ሲሰረዝ መግለጫውና የንብረቱ መዝገብ ዋጋ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በዓመታዊ የመንግሥት ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ ተጠቃልሎ መታየት አለበት፡፡

**፵፰. <u>ማስተላለፍ እና ስጦታ</u>**

ሚኒስቴሩ ለፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች ለብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት፣ ለከተማ አስተዳደሮች በማስተላለፍ፣ እንዲሁም ለሌሎች የመንግሥትን ኃላፊነት የማገዝ ተግባር ለሚያከናውኑ አካላት በስጦታ የሚተላለፉበትን ሁኔታ በመመሪያ ይወስናል፡፡

## <u>ምዕራፍ ሰባት</u>

## <u>የጨረታ ሥነ-ሥርዓት</u>

**፵፱. <u>የጨረታ ማስታወቂያ</u>**

፩/ የጨረታ ማስታወቂያ የጨረታ ሰነዱ በተዘጋጀበት ቋንቋ በኤሌክትሮኒክ ሥርዓት ወይም እንደአግባብነቱ በሌሎች ዘዴዎች በመጠቀም ይፋ መሆን ይኖርበታል፡፡

፪/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ አፈፃፀም ጨረታው አየር ላይ የሚውልበት ጊዜ እስከሚጠናቀቅ ድረስ የጨረታ ማሻሻያ ሊኖር እንደሚችልና ተጫራቾችም ይህን ክትትል እንዲያደረጉ የሚገልፅ ማስታወቂያ በኤሌክትሮኒክ ሥርዓት መግለፅ ይኖርበታል፡፡

c) stolen or misses from inventory by any similar occurrence or burnt and this is verified by the appropriate legal entity.

2/ The list and book value of all public property written off in any fiscal year shall be included in the annual public accounts report in accordance with the Directive to be issued by the Ministry.

**48. <u>Transfer And Donation</u>**

The Ministry shall determine by Directive the manner in which any property which is not useful to the Public Bodies of the Federal Government may be transferred to Regional governments, City Administrations or donated to any other body carrying on activities complementing the responsibility of the Government.

## <u>CHAPTER SEVEN</u>

## <u>BID PROCEDURE</u>

**49. <u>Advertisement of Bid</u>**

1/ Invitation to bid shall be advertised at least once, by using the electronic system or by means of any other appropriate method of communication, in the language in which the bid document was prepared.

2/ For the purpose of Sub-Article (1) of this Article, the invitation to bid shall include a statement alerting candidates to the possibility of the bid document being modified within the floating period using the electronic system.

፫/ ለተወዳዳሪዎች ለመጫረቻ ሰነድ ማቅሪቢያ የሚሰጠው ጊዜ በግዥ አፈፃፀም እና ንብረት አስተዳደር መመሪያዎች ከሚወሰነው አነስተኛ የቀን ብዛት ያነሰ መሆን የለበትም፡፡

## ፶. የጨረታ ሰነድ

፩/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በተጫራቾች መካከል የሚደረገው ውድድር በተሟላና ወጥነት ባለው ሁኔታ እንዲካሄድ ለማድረግ የሚያዘጋጁት የጨረታ ሰነድ በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውን ወይም የፀደቀውን መደበኛ የጨረታ ሰነድ መሠረት ማድረግ ይኖርበታል፡፡

፪/ የጨረታ ሰነዱ የጨረታው ማስታወቂያ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ ጨረታው እስከሚዘጋበት ጊዜ ድረስ ባሉት ቀናት እና በጨረታ ማስታወቂያው በተገለፀው አኳኋን ለተወዳዳሪዎች በኤሌክትሮኒክ ሥርዓት ተደራሽ መደረግ አለበት፡፡

፫/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የጨረታ ሰነድ ለማዘጋጀት እና ሰነዱን ለተወዳዳሪዎች ለማቅረብ የሚያወጡትን ወጪ ለመተካት ክፍያ ሊጠይቁ ይችላሉ፡፡

## ፶፩. በጨረታ ሰነድ ላይ ስለሚደረግ ማሻሻያ

፩/ ማንኛውም ተወዳዳሪ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በሚያወጧቸው የጨረታ ማስታወቂያዎች እንዲሁም የጨረታ ሰነዶች ይዘት ላይ ማብራሪያ ሊጠይቅ ወይም ይግባኝ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

፪/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በራሳቸው ወይም ከተወዳዳሪዎች በሚቀርቡ ጥያቄዎች መነሻ የመጫረቻ ሰነድ ማቅረቢያ ጊዜ ገደብ ከመጠናቀቁ በፊት የጨረታ ሰነዶችን ይዘት ለማሻሻል ይችላሉ፡፡

3/ The time allowed for candidates to prepare bid proposal shall not be less than the minimum number of days prescribed in the Directives to be issued hereunder.

## 50. Bid Document

1/ Public bodies shall prepare bid document on the basis of the standard bid documents prepared or approved by the Authority to facilitate competition among bidders in a complete and uniform manner.

2/ The bid document shall be made available to candidates on all days using the electronic system between the date of publication of the invitation to bid and the closing date of the bid and in the manner specified in the invitation to bid.

3/ Public Bodies may charge fee to recover the cost they incur in preparing and making a bid document available to candidates.

## 51. Modification to Bid document

1/ Any candidate may seek clarification or submit appeal on the content of an invitation to bid or bid document issued by any Public Body within the time limit to be specified in the Directive issued hereunder.

2/ Public Bodies may, prior to the deadline for submission of bid proposal, modify bid documents on their own initiative or in response to a request by any candidate.

፫/ የተደረገው ማሻሻያ በኤሌክትሮኒክ ሥርዓት መውጣት ያለበት ሲሆን በተጨማሪም በጨረታ ሰነዱ ላይ ማሻሻያ ስለመደረጉ መገለፅ አለበት፡፡

፬/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ የጨረታ ሰነዱን ይዘት ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው እና በማሻሻያው የተመለከቱ ማስተካከያዎችን ለማድረግ በቂ ጊዜ የሌለ መሆኑን ሲረዳ ተወዳዳሪዎች የመጫረቻ ሰነዳቸውን አሻሽለው ለማዘጋጀት በቂ ጊዜ እንዲኖራቸው ለማድረግ የጨረታ ማቅረቢያ ጊዜውን ቢያንስ ለ ፭ (አምስት) ተጨማሪ የሥራ ቀናት ማራዘም አለበት፡፡

፭/ ዝርዝር አፈፃፀሙ በመመሪያ የሚወሰን ሆኖ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ በጨረታ ሰነዱ ላይ በተደረገ ማሻሻያ ወይም ለቀረቡ የማብራሪያ ጥያቄዎች በተሰጠ ምላሽ ላይ ተወዳዳሪዎች ቅሬታ ያላቸው እንደሆነ በአዋጁ አንቀጽ ፸፭ ንዑስ አንቀጽ ፪ እና ፫ ላይ በተደነገገው መሠረት ለቦርዱ ይግባኛቸውን ለማቅረብ እንዲያስችላቸው መሥሪያ ቤቱ ምላሽ ከሰጠበት ወይም ምላሽ ሊሰጥ ይገባው ከነበረበት ቀን አንስቶ ለ፭ (አምስት) የሥራ ቀናት ጨረታው ሳይዘጋ ማቆየት ወይም የጨረታ መዝጊያ ቀኑን ማራዘም አለበት፡፡

## ፶፪. የጨረታ ማስከበሪያ

፩/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በሚያዘጋጁት የጨረታ ሰነድ ላይ ተጫራቾች ከመጫረቻ ሰነዳቸው ጋር የጨረታ ማስከበሪያ ወይም እንደሁኔታው የጨረታ መተማመኛ ቅጽ ሞልተው የማቅረብ ግዴታ እንዳለባቸው መግለጽ ይኖርባቸዋል፡፡ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ዋስትናው እውነተኛ መሆኑን አስቀድመው ማረጋገጥ አለባቸው።

3/ Any such modification on the bid document shall be notified using the electronic system.

4/ Where a Public Body finds it necessary to modify the content of a bid document and determines that there is not enough time to incorporate the modification, it shall extend the closing date for submission of bid proposal for at least 5 (five) working days to give candidates adequate time to adjust their bid proposal in accordance with the modification to the initial bid document.

5/ With the detail to be prescribed in the Directive to be issued hereunder, Where candidates have inquiries on modifications or clarifications made on the bid document in response to candidates' inquiries, the Public Body shall keep the bid unclosed for 5 (five) working days starting from the date it responded or from the date it is supposed to respond to the inquiries, so as to enable candidates submit their appeal to the Board pursuant to Sub-Article (2) and (3) of Article 75 of this Proclamation.

## 52. Bid Security

1/ Public Bodies shall include statement in the bid documents that bid proposals shall be accompanied by bid security or otherwise fill out the bid security form. Public Bodies shall ensure the genuineness of the bid security.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ለሚቀርበው የጨረታ ማስከበሪያ የሚያስፈልገው የዋስትና መጠን እና ዓይነት በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

፫/ በማንኛውም ተጫራች የቀረበ የጨረታ ማስከበሪያ ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ሊወረስ ይችላል፡-

ሀ) ጨረታው ከተከፈተ በኋላ ጨረታው ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ ተጫራቹ ራሱን ከውድድሩ ካገለለ ወይም፣

ለ) ጨረታው ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ አሸናፊ ተጫራች መሆኑ በፅሑፍ ተገልጾለት፣ ውል ለመፈረም፣ የገዛውን ንብረት ለማንሳት ወይም የውል ማስከበሪያ ለማስያዝ ፈቃደኛ ካልሆነ፣

ሐ) በዚህ አዋጅና በመመሪያው ላይ በሚደነገገው መሠረት ተጫራቹ የሂሳብ እርማት ተደርጎ ለመቀበል ፈቃደኛ ካልሆነ፤

መ) ተጫራቹ የማጭበርበር ወይም የማታለል ወይም ከሌሎች ተጫራቾች ጋር የመመሳጠር ወይም መረጃ የመደበቅ ድርጊቶችን መፈፀሙ ሥልጣን ባለው አካል የተረጋገጠ ከሆነ፡፡

**፶፫. <u>የመጫረቻ ሰነድ ስለማቅረብና ስለመቀበል</u>**

፩/ የመጫረቻ ሰነድ በኤሌክትሮኒክ ሥርዓት ጨረታ ማስታወቂያው እና በጨረታ ሰነዱ ላይ የተመለከተው የጊዜ ገደብ ከማለፉ በፊት መቅረብ አለበት፡፡

፪/ የመጫረቻ ሰነድን ለማቅረቢያ ከተወሰነው ጊዜ በኋላ የሚቀርብ ሰነድ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

2/ The amount of bid security to be furnished pursuant to Sub-Article (1) of this Article shall be prescribed in the Directive to be issued hereunder.

3/ A bid security furnished by any bidder may be forfeited for one of the following reasons:

a) where the bidder withdraws his bid proposal after the bids were opened and within the validity period of the bid, or

b) where the successful bidder refuses to sign the contract or fails to take delivery of the disposable property or to furnish performance security after notification of award,

c) where the bidder refuses to accept arithmetic correction made in accordance with this Proclamation and the Directive issued hereunder,

d) where the bidder commits fraudulent or deceitful act, collides with other bidders or conceals information and where such act or omission is proved by a competent Authority.

**53. <u>Submission and Receipt of Bid Proposal</u>**

1/ Bid proposals shall be submitted by using the electronic system before the expiry of the deadline for submission of bids and at the place stated in the invitation to bid and in the bid document.

2/ A bid proposal presented after the deadline set for submission of proposals had expired shall be rejected.

፫/ ተጫራቾች በጨረታ ማስታወቂያ ላይ በተገለፀው የመጫረቻ ሰነድ ማቅረቢያ ጊዜ ውስጥ የማሻሻያ ሰነድ ማቅረብ ይችላሉ፡፡

**፶፬. ጨረታን ስለመክፈት**

፩/ በመንግሥት መሥሪያ ቤቱ በጨረታ ሰነዱ የተመለከተው የመጫረቻ ሰነድ ማቅረቢያ የተወሰነው የጊዜ ገደብ እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ የመጫረቻ ሰነድን በጨረታ መክፈቻ ቀንና ሰዓት ጠብቆ መክፈት አለበት፡፡

፪/ የተጫራቹ ስም እና በእያንዳንዱ የመጫረቻ ሰነድ የቀረበው የመጫረቻ ዋጋ፣ የተሰጠ ቅናሽ እና የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ እንደ ሻኘው ሁኔታ ተጫራቾች አንፃራዊ ደረጃቸውን ለማወቅ ይረዳቸዋል ብሎ የሚያምንባቸውን ሌሎች መረጃዎች እንዲመዘገብ እና ተጫራቾች የተመዘገበውን ዝርዝር እንዲያገኙ ማድረግ አለበት፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው ቢኖርም የቴክኒክና የፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳብ ተለይቶ የቀረበ በሚሆንበት ጊዜ ተጫራቾች ያቀረቡት ዋጋ የሚከፈተው የቴክኒክ ግምገማው ከተጠናቀቀና ወደሚቀጥለው የውድድር ምዕራፍ የተሸጋገሩት ተጫራቾች ከታወቁ በኋላ ይሆናል፡፡

3/ Bidders may submit amendments to their bid proposal within the time frame stated in the invitation to bid for submission of bid proposals.

**54. Opening of Bids**

1/ After the closing date for submission of bid proposals, the Public Body shall open all bid proposals received before the closing date, at the time and date stated in the bid document and in the invitation to bid for opening of bids.

2/ The name of the bidder and the total amount of each bid, discounts offered and any such information as the Public Body deems necessary to let the bidders know their relative rank shall be recorded and the record shall be made available to any bidder.

3/ Notwithstanding the provision of Sub-Article (2) of this Article, where technical and financial proposals are submitted separately, the price quoted by the bidders shall be opened after the bidders who have qualified for the second stage on the basis of the result of the evaluation of the technical proposals are identified.

**፶፭. የመጫረቻ ሰነዶችን ስለመመርመር እና ስለመገምገም**

፩/ ጨረታውን ለመመርመርና ግምገማውን ለማከናወን የሚረዳ ሆኖ ሲገኝ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ተጫራቾች ባቀረቡት የመጫረቻ ሰነድ ላይ ማብራሪያ እንዲሰጡ ሊጠይቅ ይችላል፡፡ ሆኖም የዋጋ ለውጥን ጨምሮ የመጫረቻ ሰነዱ ላይ መሠረታዊ ለውጥ የሚያስከትል ሀሳብ ማቅረብ ወይም መፍቀድ አይቻልም፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ቢኖርም የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ በጨረታ ግምገማ ወቅት የተገኙ የሂሳብ ስህተቶችን ማረምና የተደረገውን ማስተካከያ ለሚመለከተው ተጫራች በአፋጣኝ መግለፅ አለበት፡፡

፫/የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ የመጫረቻ ሰነዱ የተሟላ ነው ብሎ ሊቀጥል የሚችለው በጨረታው ሰነድ የተመለከቱትን ተፈላጊ ሁኔታዎች የሚያሟላ ሆኖ ሲያገኘው ነው፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በጨረታው ሰነድ ከተዘረዘሩት ባህሪያት፣ የውል ቃሎች፣ ሁኔታዎች እና ሌሎችም ተፈላጊ ነጥቦች ጋር በተወሰነ ደረጃ ልዩነት ቢኖረውም፣ መሠረታዊ የሆነ ለውጥ እና ልዩነት እስከሌለው ድረስ ወይም የጨረታው ቁምነገር ሳይለወጥ ሊታረም የሚችል ጥቃቅን ስህተት ወይም ግድፈት ቢኖረውም፣ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ጨረታውን እንደተሟላ አድርጎ ሊቀበል ይችላል፡፡

፭/ ማናቸውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ምክንያቶች በአንዱ ተጫራችን የጨረታው አሸናፊ አድርጎ መምረጥ የለበትም፡-

**55. Examination and Evaluation of Bid Proposals**

1/ The Public Body may ask bidders for clarification of their bid proposals in order to assist in the examination and evaluation of bid proposals, provided, however, that no change in the substance of the bid, including changes in price, shall be sought, offered or permitted.

2/ Notwithstanding the provision of Sub-Article (1) of this Article, the Public Body shall correct arithmetical errors that are discovered during the examination of bid proposals and give prompt notice of any such correction to the bidder concerned.

3/ The Public Body may regard a bid proposal as responsive if it conforms to the requirements stated in the bid document.

4/ Without prejudice to Sub-Article (3) of this Article, the Public Body may regard a bid proposal as responsive even if it contains minor deviations that do not materially alter or depart from the characteristics, terms, conditions and other requirement set forth in the bid document or it contains errors or oversights that can be corrected without touching on the substance of the bid.

5/ The Public Body shall not pronounce a bidder to be the successful bidder on any of the following grounds:

ሀ) ተጫራቹ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፳፬ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሱትን መስፈርቶች ማሟላት የማይችል ሆኖ ሲገኝ፣

ለ) ተጫራቹ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የተደረገውን የሂሳብ ማስተካከያ የማይቀበል ሆኖ ሲገኝ፣ ወይም የሂሳብ ስህተቱ በመመሪያው ወይም በጨረታ ሰነዱ ላይ ከሚቀመጠው ገደብ ውጭ ሆኖ ሲገኝ፣

ሐ) የቀረበው የመጫረቻ ሰነድ በጨረታ ሰነዱ የተመለከቱትን ሁኔታዎች የማያሟላ ሆኖ ሲገኝ፣

መ) አስቀድሞ በጨረታ ሰነዱ ላይ በተቀመጡ መመዘኛዎች መሠረት በሚደረግ ግምገማ ተጫራቹ የሚገባውን ውል ለመፈፀም የሚያስችል የሙያና የቴክኒክ ብቃት፣ የፋይናንስ አቅም፣ መሣሪያ፣ በቂ የአገልግሎት መስጫ ስፍራ፣ ግዥው በሚፈፀምበት ዘርፍ የሥራ አመራር ችሎታ እና ልምድ፣ መልካም ሥራ አፈፃፀም እና ብቃት ያለው የሰው ኃይል የሌለው ሆኖ ሲገኝ፣

ሠ) የተለየ አስተያየት ለማግኘት ወይም ጨረታውን ለማሸነፍ ለማናቸውም ኃላፊ ወይም ሠራተኛ መደለያ መስጠቱ ወይም የመደለያ ሀሳብ ማቅረቡ ሲረጋገጥ፣

ረ) የግዥ ሂደቱ ከተጀመረ በኋላ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፹፬ ንዑስ አንቀጽ (፪) ፊደል ተራ (ሀ) መሠረት ባለሥልጣኑ በሚሰጠው ውሳኔ መሠረት በማንኛውም የመንግሥት ግዥ ጨረታ እንዳይሳተፍ ዕገዳ የተጣለበት ድርጅት፣

a) the bidder fails to satisfy the requirements stated in Sub-Article (1) of Article 24 of this Proclamation,

b) the bidder does not accept a correction of any arithmetical error made pursuant to Sub-Article (2) of this Article or the margin of error is beyond the limit prescribed in the Directive to be issued hereunder or the bid document,

c) the bid proposal is not responsive to the requirements of the bid document,

d) based on evaluation conducted on the basis of the criteria set out in the bid document, the bidder does not possess the necessary professional and technical qualifications and competence, financial resources, equipment and other physical facilities, managerial capability and experience in the object of procurement, good track record, and qualified personnel to perform the contract,

e) where it is ascertained that the bidder has given or offered inducement to any employee or authority of the Public Body who is involved in the evaluation of or endorsement of the bid with a view to win special favor or the award;

f) if the bidder was suspended from participating in public procurement by the Authority in accordance with Sub-Article (2) paragraph (a) of Article 84 of this Proclamation after the procurement process had begun,

ሰ) ተወዳዳሪው በጨረታው ሰነድ ላይ የማጭበርበር ተግባር መፈፀሙ፣ ወይም ከሌላ ተወዳዳሪ ጋር መመሳጠሩ ሲረጋገጥ ወይም በጨረታ ሰነዱ ወይም መመሪያው ላይ በሚገለፀው መሠረት የጥቅም ግጭት ያለበት ሆኖ ከተገኘ ወይም ሌሎች ከሥነ-ምግባር ውጪ የሆኑ ድርጊቶች ፈፅሞ ሲገኝ፡፡

፮/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፰) በተደነገገው መሠረት አሸናፊውን ተጫራች ለመምረጥ በጨረታ ሰነዱ በተመለከተው የግምገማ መስፈርት መሠረት ተፈላጊውን ያሟሉ የመጫረቻ ሰነዶችን መገምገምና ማወዳደር አለበት፡፡ በጨረታ ሰነድ ያልተመለከተ የማወዳደሪያ መስፈርት በጥቅም ላይ ሊውል አይችልም፡፡

፯/ በዚህ አዋጅ በግልፅ ካልተመለከተ በስተቀር ማናቸውም ተጫራች በመጫረቻ ሰነዱ ከተመለከተው ውጪ በጨረታው አሸናፊ ለመሆን ያቀረበውን የመጫረቻ ዋጋ እንዲለውጥ ወይም ያቀረበውን የመወዳደሪያ ሀሳብ እንዲያሻሽል ወይም ይህንን ለመፈፀም ግዴታ እንዲገባ ሊጠየቅ ወይም ሊገደድ አይችልም፡፡

፰/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በጨረታ ውድድሩ ከቀረቡ ተጫራች መካከል አሸናፊ የሚሆነውን ተጫራች ለመለየት፡-

ሀ) በጨረታ ሰነድ ላይ የተመለከቱትን ዝቅተኛ የቴክኒክ መመዘኛ መስፈርቶች ማሟላቱ በቅድሚያ ከተረጋገጠ በኋላ እንደ ግዥው ባህሪ አነስተኛ ዋጋ ያቀረበን ተጫራች፣ ወይም በነጥብ አሰጣጥ

g) where it is ascertained that the bidder has committed an act of fraud in connection with the bid document or has connived with another bidder in price quotation or it is established that the bidder has conflict of interest as defined in the Directive to be issued hereunder or in the bid document or is involved in any unethical act which is prejudicial to the procurement.

6/ In the process of selecting the successful bidder, the Public Body shall only consider substantially responsive bids as defined in Sub-Article (8) of this Article, in accordance with the criteria specified in the bid document. No criterion that has not been set forth in the bid document shall be used to evaluate bid proposals and select the successful bidder.

7/ Unless expressly provided otherwise in this Proclamation, no bidder may be required to change the price quoted in his bid proposal to win award or otherwise modify his proposal or to assume obligation to do so except as set forth in the bid document.

8/ In order to identify the successful bidder from among bidders competing in the bid, the Public Body shall:

a) where the bidder having fulfilled the minimum technical requirements set forth in the bid document, offers the lowest evaluated price or where the bidder scores the highest point in the

የግምገማ ዘዴ በቴክኒክና በዋጋ ጠቅላላ ድምር ውጤት ከፍተኛውን ነጥብ ያገኘን ተጫራች አሸናፊ አድርገው ሊመርጡ ይችላሉ፣

ለ) የዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች እንደ ግዥው ባህሪ እና ዓይነት የህይወት ዘመን ወጪ ትንትና ሥርዓትን መጠቀም አለባቸው፡፡

፱/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፰) መሠረት በአሸናፊነት የተመረጠ ተጫራች በቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ጨረታ ተገምግሞ ያለፈ ካልሆነ በስተቀር እንደአስፈላጊነቱ ሕጋዊነቱ እንዲሁም የፋይናንስ እና የቴክኒክ አቅሙ በመጫረቻ ሰነዱ ላይ በቀረበው ማስረጃ መሠረት መሆኑ በድህረ-ግምገማ መረጋገጥ አለበት፡፡

፲/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ የግምገማውን ሂደትና ውጤት የሚገልፅ የግምገማ ሪፖርት ማዘጋጀት አለበት፡፡

**፶፮. <u>የጨረታን ሂደት በሚስጥር ስለመጠበቅ</u>**

ጨረታው ከተከፈተበት ጊዜ አንስቶ ከጨረታ ምርመራ፣ ከማብራሪያ ከግምገማ እና አሸናፊውን ተጫራች በሚመለከት ከቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ጋር የተያያዙ መረጃዎች በሚስጥርነት መጠበቅ ያለባቸው ሲሆን፣ አሸናፊው ተጫራች እስከሚገለፅ ድረስ ለተጫራቾች ወይም ከሥራው ሂደት ጋር ግንኙነት ለሌላቸው ሰዎች መገለፅ የለባቸውም፡፡

**፶፯. <u>ከአሸናፊ ተጫራች ጋር ድርድር ስለሚደረግባቸው ጉዳዮች</u>**

፩/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ከአሸናፊው ተጫራች ጋር መሠረታዊ ባልሆኑ የውል አፈፃፀም ጉዳዮች ላይ ድርድር ሊያደርግ ይችላል፡፡

total sum of the technical and financial evaluation by merit point, or

b) without prejudice to paragraph (a) of this Sub-Article, Public Bodies shall use total life cycle cost analysis depending on the nature and type of the procurement.

9/ Unless the bidder selected as the successful bidder pursuant to Sub-Article (8) of this Article is sourced through prequalification bid, it shall be ascertained, as necessary, by post evaluation that the legal, financial and technical standing of the successful bidder conforms to the evidence presented with the bid proposal.

10/ The Public Body shall prepare an evaluation report showing the conduct and result of the evaluation of bids.

**56. <u>Confidentiality of Bid Proceeding</u>**

After the opening of bids, information relating to the examination, clarification, and evaluation of bids and recommendations for award shall not be disclosed to bidders or to other persons who are not concerned with the proceeding until the award of the contract is announced.

**57. <u>Matters subject to negotiation with the Successful Bidder</u>**

1/ The Public Body may negotiate with the successful bidder on non-essential matters of contract performance.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ የተመለከተው ቢኖርም በመንግሥት መሥሪያ ቤቱ እና በአሸናፊው ተጫራች መካከል በሚደረገው ድርድር መሠረት የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ የሚስማማባቸው የውል ቃላት እና ቅድመ ሁኔታዎች ለተጫራቹ የተለየ ጥቅም የማይሰጡ እና መሥሪያ ቤቱንም የማይጎዱ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

፫/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፬ ላይ በተጠቀሰው መሠረት ከአንድ አቅራቢ በቀጥታ ለሚፈፀም ግዥ ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው መመሪያ በተለይ ካልተፈቀደ በስተቀር የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ አሸናፊ ተጫራቾች ባቀረቡት ዋጋ እና ዋጋን በተመለከቱ ሌሎች ጉዳዮች ላይ ድርድር ማድረግ አይችልም፡፡

## ፶፰. <u>የጨረታ ውጤትና አሸናፊነትን ስለመግለፅ</u>

፩/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ከተጫራቾች የቀረበው የመጫረቻ ሰነድ ፀንቶ የሚቆይበት የጊዜ ገደብ ከማለፉ በፊት የጨረታውን ዝርዝር ውጤት በኤሌክትሮኒክ ሥርዓት መሠረት በጨረታው ለተሳተፉ በሙሉና ለሕዝብ በተመሳሳይ ጊዜ ይፋ ማድረግ አለባቸው፡፡

፪/ ተጫራቾች በጨረታው ውጤት የማይስማሙ ከሆነ በዚህ አዋጅ ላይ የተገለፀውን የአቀራረብ ሥርዓት በተከተለ መንገድ አቤቱታ ማቅረብ የሚችሉ መሆኑን የሚገልፅ መሆን ይኖርበታል፡፡

2/ Notwithstanding the provision of Sub-Article (1) of this Article, the Public Body shall make sure that the terms and conditions of the contract to which it agrees by negotiation with the successful bidder does not give special advantage to the successful bidder or is not prejudicial to the interest of the Public Body.

3/ Except in the case of direct procurement provided for in Article 34 of this Proclamation or unless expressly provided in the Directive to be issued hereunder, the Public Body cannot negotiate on the price quoted by the successful bidder and on other matters related to price.

## 58. <u>Notification of Bid Evaluation Results And Award of Contract</u>

1/ The Public Body shall disclose by using the electronic system to all bidders and the public at the same time, the result of the bid evaluation in detail prior to the expiry of the validity period of the bid proposals submitted by the bidders.

2/ The notification of the result of the bid evaluation shall clearly state that any bidder not satisfied with the result of the bid evaluation has the right to lodge complaint in accordance with the procedure laid down in this Proclamation.

፫/ በዚህ አዋጅ ለአቤቱታ ማቅረቢያ የተቀመጠው የጊዜ ገደብ ካበቃ በኋላ ወይም አቤቱታ ቀርቦ የመጨረሻ እልባት ካገኘ በኋላ ወዲያውኑ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ በአሸናፊነት ለተመረጠው ተጫራች የአሸናፊነት ማስታወቂያ መላክ አለበት፡፡

፬/ የአሸናፊነት ማስታወቂያ ውሉ የሚፈረምበትን ቀን፣ ተጫራቹ ማስያዝ ያለበትን የውል ማስከበሪያ ዓይነት እና መጠን እንዲሁም እንደአስፈላጊነቱ በአሸናፊው ተጫራች ሊሟሉ የሚገባቸውን ሌሎች ቅድመ-ሁኔታዎች የሚገልፅ መሆን ይኖርበታል፡፡

፭/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ለተጫራቾች የጨረታውን ውጤት ከማሳወቁ በፊት እና በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፸፬ እና ፸፭ የተመለከተው የአቤቱታ ወይም የይግባኝ ማቅረቢያ የጊዜ ገደብ ከማለፉ በፊት ውል መፈረም የለበትም፡፡

**ምዕራፍ ስምንት**

**የማዕቀፍ እና ስትራቴጂያዊ ግዥዎች**

**፶፱. የማዕቀፍ እና ስትራቴጂያዊ ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት**

፩/ በማዕከል የሚፈፀሙ የማዕቀፍ እና ስትራቴጂያዊ ግዥዎች የሚከናወኑት፣ እንዲሁም በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች እንዲወገዱ ውሳኔ የተሰጠባቸው የመንግሥት ንብረቶች በሽያጭ የሚወገዱት ለዚህ ዓላማ በደንብ ቁጥር ፩፻፹፬/፪ሺ፪ በተቋቋመው የመንግሥት ግዥ አገልግሎት መሥሪያ ቤት ይሆናል፡፡

3/ Notification of award shall be sent to the successful bidder immediately after the expiration of the time limit for lodging complaint stipulated in this Proclamation or after any complaint lodged has been disposed of.

4/ The notification of award shall specify the date on which the contract shall be signed, the type and amount of the contract security to be furnished by the successful bidder and such other requirements as the successful bidder should satisfy.

5/ The Public Body may not sign any contract prior to giving notification of the result of the bid evaluation to all bidders and before the expiration of the period specified under Article 74 and 75 of this Proclamation for lodging complaint or appeal.

**CHAPTER EIGHT**

**FRAMEWORK AND STRATEGIC PROCUREMENTS**

**59. Framework, and Strategic Procurements and Property Disposal**

1/ The functions of executing framework and strategic procurements as well as getting rid of public property that Public Bodies desire to dispose of by sale centrally shall be performed by public Procurement Service established for this purpose by Regulation no. 184/2010.

፪/ ሚኒስቴሩ ሀገራዊ ጠቀሜታ ያላቸው በመሆናቸው ምክንያት በመንግሥት ግዥ አገልግሎት መሥሪያ ቤት የሚፈፀሙ ስትራቴጂያዊ ግዥዎችን ይወስናል፡፡ ሚኒስቴሩ ግዥው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችን ፍላጎትና የሥራ ባህሪ ያገናዘበና በሌላ የግዥ አማራጭ ሊፈፀም የማይችል መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

፫/ ባለሥልጣኑ በመንግሥት ግዥ አገልግሎት መሥሪያ ቤቱ ግዥ ያቸው በማዕከል የሚፈፀሙ የማዕቀፍ ዕቃዎችንና ከምክር ውጭ የሆኑ አገልግሎቶችን፣ እንዲሁም በማዕከል የሚወገዱ ንብረቶችን ዝርዝር በየጊዜው ይወስናል፡፡

## ፷. <u>የማዕቀፍ ስምምነት አፈፃፀም</u>

፩/ ዝርዝር አፈፃፀሙ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው መመሪያ የሚወሰን ሆኖ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ለሚኖራቸው ተመሳሳይ የግዥ ፍላጎት ወይም አንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት በተወሰነ ጊዜ ውስጥ በተደጋጋሚ ለሚኖረው ፍላጎት ግዥውን በማዕቀፍ ስምምነት መፈፀም ይችላል፡፡

፪/ ዝርዝር አፈፃፀሙ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው መመሪያ የሚወሰን ሆኖ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በሥራቸው ባህሪ ምክንያት የሚጠቀሙባቸው በየጊዜው ከጥቅም ውጭ የሚሆኑ ተመሳሳይ ንብረቶችን ወይም ተረፈ ምርቶችን ሽያጭ በማዕቀፍ ስምምነት ማስወገድ ይችላሉ፡፡

2/ The Ministry shall determine strategic procurements on the basis of their national significance that are to be carried out by the Public Procurement Service. The Ministry shall ensure this procurement is made in consideration of peculiar characteristics and interests of Public Bodies and cannot otherwis be obtained in other procurement methods.

3/ The Authority shall determine from time to time the list of goods and non-consulting services that are procured under framework procurement and the properties that are disposed of centrally by the Public Procurement Service.

## 60. <u>Application of Framework Agreement</u>

1/ With the mode of application of this provision to be prescribed in the Directive issued hereunder, framework agreement may be used to fulfill similar procurement requirements of Public Bodies or recurrent procurement requirements of a Public Body within certain time frame.

2/ With the mode of application of the provision of this Sub-Article to be prescribed in the Directive issued hereunder, similar properties that Public Bodies use because of the character of their function and become out of service from time to time or byproducts may be disposed of by sale under framework agreement.

፫/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፱ ንዑስ አንቀጽ (፫) በሚያወጣው ዝርዝር ውስጥ ለተካተቱት ዕቃዎችና ከምክር ውጭ የሆኑ አገልግሎቶች የሚኖራቸውን የፍላጎት ትንበያ፣ እንዲሁም በማዕቀፍ ሊወገዱ የሚገባቸውን ንብረቶች ዝርዝር አዘጋጅተው በመላክ ለመንግሥት ግዥ አገልግሎት መሥሪያ ቤት ያሳውቃሉ፡፡

፬/ የመንግሥት ግዥ አገልግሎት መሥሪያ ቤት በዚህ አዋጅ በተመለከተው እና በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው መመሪያ ላይ በሚገለፀው ዝርዝር መሠረት በማዕከል የሚፈፀም ግዥ የማዕቀፍ ስምምነት ይፈፅማል፣ ያስተዳድራል፡፡

፭/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት የሚፈረመውን የማዕቀፍ ስምምነት መሠረት በማድረግ ከማዕቀፍ አቅራቢዎች ጋር ዝርዝር ውል ይፈፅማሉ፣ የፈፀሙትን ውልም ያስተዳድራሉ፡፡

፮/ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው መመሪያ በተመለከተው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር በማዕቀፍ ስምምነቱ የነጠላ ዋጋ ወይም መሠረታዊ በሆኑ ሌሎች የስምምነቱ የውል ሁኔታዎች ላይ ለውጥ ማድረግ አይፈቀድም፤ ሆኖም በማዕቀፍ ስምምነቱ ያልተካተቱ እና በማዕቀፍ ስምምነቱ ላይ መሠረታዊ ለውጥ የማያስከትሉ ጉዳዮች የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ እና የማዕቀፍ ስምምነቱ አቅራቢ በሚገቡት ዝርዝር ውል ሊወሰኑ ይችላሉ፡፡

3/ Public Bodies shall prepare forecast of their requirements for goods and non-consulting services that are included in the list that the Authority issues pursuant to Sub-Article (3) of Article 59 of this Proclamation and list of properties that may be disposed of under a framework agreement and communicate same using the electronic system to the Public Procurement Service.

4/ The Public Procurement Service shall conclude and administer central framework agreements in the manner prescribed in this Proclamation and the Directive issued hereunder.

5/ Public Bodies shall on the basis of the framework agreement to be signed pursuant to Sub-Article (4) of this Article conclude call of contract with the frame work suppliers and administer the contract.

6/ Except in cases provided for in this Proclamation or the Directive issued hereunder no variation shall be allowed to unit price and such other fundamental terms of the framework agreement when concluding call of contract with the suppliers; however, the Public Body and the supplier may agree on terms that have not been dealt with in the framework agreement or that do not materially affect the framework agreement.

፯/ በዚህ አዋጅ ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው የግዥ አፈፃፀም መመሪያ ካልተፈቀደ በስተቀር የማዕቀፍ ስምምነት የሚፈፀመው በግልፅ ጨረታ የግዥ ዘዴ ከተመረጡ ተጫራቾች ጋር ይሆናል፡፡

፰/ የግዥ እንዲሁም የሚወገዱ ንብረቶች ሽያጭ የማዕቀፍ ስምምነት ዝርዝር አፈፃፀም በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

## ምዕራፍ ዘጠኝ
## የግዥ እና የሚወገድ ንብረት ሽያጭ ውል

### ፷፩. ጠቅላላ ድንጋጌዎች

፩/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የግዥ ውል ከመፈረማቸው አስቀድመው ለግዥው አገልግሎት የሚውል በቂ በጀት ያላቸው መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

፪/ በዚህ አዋጅ እና በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው መመሪያ በሌላ ሁኔታ ካልተወሰነ በስተቀር በመንግሥት መሥሪያ ቤት የሚፈፀም ማንኛውም የግዥ ወይም የሚወገድ ንብረት ሽያጭ ውል ወይም የውል ማሻሻያ በጽሑፍ መሆን አለበት፡፡

፫/ ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት እንደሁኔታው ከአቅራቢው ወይም ከሚወገድ ንብረት ገዥ ጋር ውል ከመዋዋሉ በፊት ወይም ከተዋዋለ በኋላ በውሉ መሠረት መፈፀም እንዲቻል ለውሉ አፈፃፀም አስፈላጊ የሆኑ ቅድመ ሁኔታዎች መሟላታቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

7/ Unless otherwise expressly provided for in this proclamation and the Directive issued hereunder, framework agreement shall be awarded to bidders selected through open bidding procedure.

8/ Details pertaining to the application of framework agreement for procurement and property disposal shall be determined in the Directive issued hereunder.

## CHAPTER NINE
## CONTRACT OF PROCUREMENT AND SALE OF DISPOSABLE PROPERTY

### 61. General Provisions

1/ Public Bodies shall make sure that they have adequate budget of expenditure for any procurement that they intend to execute before entering into contract for the procurement.

2/ Unless expressly provided otherwise in this Proclamation or the Directives to be issued hereunder, any contract of procurement or sale of disposable property or the amendment thereto shall be made in writing.

3/ Public Bodies shall ensure that all preconditions necessary for the performance of a contract are fulfilled before or after entering into a contract with a supplier or the buyer of a disposable property, as the case maybe.

፷፪. ውል ስለመፈራረም

፩/ ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት የመደበኛ ጨረታ ሰነዶች አንድ ክፍል የሆነውን አጠቃላይ የውል ሁኔታዎች የውሉ አካል በማድረግ እና ስምምነት ላይ የተደረሰባቸውን ልዩ የውል ሁኔታዎች የያዘውን የውል ሰነድ ከአቅራቢው ጋር መፈረም አለበት፡፡

፪/ በመንግሥት መሥሪያ ቤቱ እና በአሸናፊው ተጫራች መካከል ውል ካልተፈረመ በስተቀር የጨረታው አሸናፊ በመገለፁ ብቻ ውል እንደተፈፀመ አይቆጠርም፡፡

፫/ በመንግሥት መሥሪያ ቤት እና በአቅራቢው መካከል ውል ተመስርቷል የሚባለው ሁለቱም ተዋዋይ ወገኖች ስምምነት የተደረሰባቸውን ጉዳዮች የያዘ ውል ሰነድ ሲፈርሙ ሲሆን፣ የአሸናፊነት ማስታወቂያ ለተጫራቹ ከተገለፀበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር ፲፭ (አስራ አምስት) የሥራ ቀናት ውስጥ ሁለቱም ተዋዋይ ወገኖች ውሉን መፈረም አለባቸው፡፡

፬/ በመንግሥት መሥሪያ ቤቱ እና በአሸናፊው ተጫራች መከከል የሚደረገው ውል የሁለቱን ወገኖች መብትና ግዴታ በግልፅ ማመልከት አለበት፡፡

፷፫. ውልን ይፋ ስለማድረግ

ከብሔራዊ ደህንነት ወይም ከሀገር መከላከያ ጋር ከተያያዙ ሚስጥራዊ ግዥዎች በስተቀር ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት የግዥው ወይም የሚወገድ ንብረት ሽያጭ ውሉ ከተፈረመ በኋላ በኤሌክትሮኒክ ሥርዓት መሠረት ዋና ዋና መረጃዎችን ለሕዝብ ይፋ ማድረግ አለበት፡፡

62. Signing of Contract

1/ Any Public Body has to sign with the supplier a contract document containing the general conditions of contract forming an integral part of the standard bid documents and the special conditions of contract reflecting the mutually agreed terms and conditions of the contract.

2/ Mere notification of award does not give rise to the existence of a contract unless a contract is signed between the Public Body and the successful bidder.

3/ A contract is said to exist between the Public Body and the supplier where the parties sign a contract document containing all the agreements reached between the parties, with the parties being required to sign the contract within 15 (Fifteen ) days of notification of award.

4/ The contract to be concluded between the Public Body and the successful bidder shall expressly state the rights and obligations of the parties.

63. Disclosure of Contract

With the exception of confidential procurements pertaining to national security or national defense, a Public Body entering into a contract of procurement or sale of disposable property shall disclose to the public the important features of the contract using the electronic system after the signing of the contract.

**፷፬. የውል ማስከበሪያ**

፩/ አቅራቢው ወይም የሚወገድ ንብረት ገዥው ለውሉ ማስከበሪያ የሚሆን ዋስትና ለግዥ ፈፃሚው መሥሪያ ቤት ወይም የሚወገድ ንብረት ሻጭ ለሆነው መሥሪያ ቤት ማስያዝ አለበት፡፡ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ዋስትናው ትክክለኛ መሆኑን አስቀድመው ማረጋገጥ አለባቸው።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የውል የማስከበሪያ የሚጠየቅባቸው የግዥ እና የሚወገድ ንብረት ሽያጭ ዓይነቶች፣ የውል ማስከበሪያው ዓይነትና መጠን በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

**፷፭. የውል አስተዳደር**

ዝርዝሩ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ መመሪያ የሚወሰን ሆኖ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሚከተሉትን ዋና ዋና የውል አስተዳደር ተግባራት ማከናወን አለባቸው፡-

፩/ የቅድመ ክፍያ

ሀ) በመንግሥት ግዥ አፈጻጸም ለአቅራቢው የሚሰጠው የቅድመ ክፍያ መጠን እና ዝርዝር አፈፃፀሙ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው መመሪያ ይወሰናል፣

ለ) በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው መመሪያ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር፣ የቅድመ ክፍያ ሊፈፀም የሚችለው አቅራቢው በቅድመ ክፍያ መልክ ከሚወስደው ገንዘብ መጠን ጋር እኩል የሆነ የቅድመ ክፍያ ዋስትና ሲያቀርብ ይሆናል፡፡

**64. Contract Security**

1/ A supplier or buyer of a disposable property shall provide the Public Body with a contract security. Public Bodies shall ensure the genuineness of the contract security

2/ The type of procurement or sale of disposable property in respect of which contract security is required pursuant to Sub-Article (1) of this Article, and the type and amount of such contract security shall be determined by the Directive to be issued hereunder.

**65. Administration of Contract**

With the details to be specified in the Directive to be issued hereunder, Public Bodies shall carry out the following main tasks of contract administration:

1/ Advance payment

a) the amount of advance payment that may be allowed to suppliers in public procurement and the manner in which it is effected shall be determined by the Directive to be issued hereunder,

b) unless otherwise expressly provided by the Directive to be issued hereunder, advance payment may be effected against advance payment guarantee of equal amount to be furnished by the supplier.

፪/ ውልን ስለማስፈፀም

ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት፡-

ሀ) የውልን አፈፃፀም የሚከለክል ወይም የሚያስተጓጉል የተለየ ሁኔታ ካላጋጠመው በስተቀር ከአቅራቢዎች ወይም ከሚወገድ ንብረት ገዢዎች ጋር የተደረጉ ውሎች በፍጥነት ተፈፃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፣

ለ) በአቅራቢው ወይም የሚወገድ ንብረት ገዢው ሊከናወኑ የሚገባቸውን ተግባራት በመለየት አቅራቢው ወይም የሚወገድ ንብረት ገዢው በውሉ መሠረት ተግባራቱን በወቅቱ መፈፀሙን ተከታትሎ ማረጋገጥ፣

ሐ) የውሉ ቅድመ ሁኔታዎች ተሟልተው ውሉ ተፈፃሚ መሆን የጀመረበትን ቀን መዝግቦ መያዝ እና እንደአስፈላጊነቱ አቅራቢው ወይም የሚወገድ ንብረት ገዢው እንዲያውቀው ማድረግ አለበት፡፡

፫/ የውል አፈፃፀምን መከታተል

ሀ) የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የውል አፈጻጸምን የሚከታተል የሥራ ክፍል መለየት ወይም የውል ክትትል በተለያዩ የሥራ ክፍሎች በቅንጅት የሚፈፀም በሚሆንበት ወቅት የሥራ ክፍሎቹ ተግባራቸውን በግልጽ እንዲያውቁት ማድረግ ይኖርባቸዋል፣

2/ Enforcement of Contract

Any Public Body shall:

a) expedite the implementation of any contract concluded with suppliers or buyers of disposable property unless circumstances preventing or disrupting the performance of the contract arise,

b) identify the activities to be performed by the supplier or the buyer of disposable property under the contract and ensure that the supplier or the buyer of the disposable property performs such activities in due time as per the contract,

c) record the date on which the actual performance of the contract began upon fulfillment of the precondition set forth in the contract for the actual performance of the contract and, if necessary, notify this to the supplier or the buyer of the disposable property.

3/ Follow up of Enforcement of Contract

a) Public Bodies shall identify the unit responsible for following up the performance of a contract or where the task is carried out through the coordination of more than one unit, make sure that the units involved in the following up of the performance of the contract are aware of their duties,

ለ) የውል አፈፃፀምን የሚከታተለው የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ የሥራ ክፍል አቅራቢው ወይም የሚወገድ ንብረት ገዢው በውሉ መሠረት የሚያከናውናቸው ዋና ዋና ተግባራት በውሉ ላይ በተገለጸው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት እየተከናወኑ የሚገኙ መሆኑን መከታተል እና የውል አስተዳደር መረጃውን በኤሌክትሮኒክ ሥርዓት መሠረት መዝግቦ መያዝ ይኖርበታል፣

ሐ) አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ በውል አፈፃፀም ወቅት የውል ማሻሻያ ማድረግ የሚቻል ሲሆን የሚደረገው የውል ማሻሻያ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱን ጥቅም የሚጎዳ እና በጨረታው ከተወዳደሩ ሌሎች ተወዳዳሪዎች አንፃር ለአቅራቢው የተለየ ጥቅም የሚሰጥ መሆን የለበትም፣

መ) የመንግሥት መሥሪያ ቤት በውል አፈፃፀም ወቅት ከሦስተኛ ወገን የሚገኙ አገልግሎቶችን መለየት እና አገልግሎቶቹ የውል አፈፃፀሙን በሚያግዝ መልኩ መስጠታቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

፬/ የዋጋ ማስተካከያ ስለማድረግ

የዋጋ ማስተካከያ የሚደረግባቸው ሁኔታዎች በዚህ አዋጅ መሠረት ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

b) the unit within a Public Body responsible for monitoring performance of a contract shall make sure that the supplier or buyer of disposable property delivers the principal tasks under the contract in accordance with the agreed schedule and using the electronic system maintain track records of contract administration,

c) where it is called for, a contract may be amended in the course of its performance in accordance with the Directive to be issued hereunder, it being understood that such amendment shall not be detrimental to the interest of the Public Body and is not motivated by a desire to favor a supplier to the prejudice of the other bidders,

d) a Public Body shall identify services to be rendered by a third party in connection with the performance of a contract and ensure that such services are rendered in a manner that facilitates the performance of the contract.

4/ Price Adjustment

Conditions for price adjustment shall be prescribed in a Directive to be issued by the Ministry in accordance with this Proclamation.

፭/ ውልን ማጠናቀቅ

ሀ) ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ከአቅራቢዎች ወይም የሚወገድ ንብረት ገዥዎች ጋር የተፈረሙ ውሎችና ተያያዥ ጉዳዮች በውሎቹ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት መጠናቀቃቸውን ማረጋገጥ አለበት፣

ለ) የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ከአቅራቢው ወይም የሚወገድ ንብረት ገዢው እና ከሦስተኛ ወገን ጋር ያሉ ተግባራትን በማጠናቀቅ የውል አፈፃፀም ግምገማ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

፮/ ውልን ስለማቋረጥ

ውል በግዥ ፈፃሚው አካልና በአቅራቢው መካከል በተገባው የውል ቃላትና ሁኔታዎች መሠረት ሊቋረጥ ይችላል፡፡

፯/ የፍትሐብሔር ሕግ

በዚህ ንዑስ ክፍል የፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎች እንደአግባብነቱ ተፈፃሚ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

**፷፮. <u>የውል አለመግባባቶችን ስለመፍታት</u>**

፩/ ከግዥ ወይም የሚወገድ ንብረት ሽያጭ ውል አፈፃፀም ጋር በተያያዘ በመንግሥት መሥሪያ ቤቱ እና በአቅራቢው ወይም የሚወገድ ንብረት ገዥው መካከል የሚፈጠር ማንኛውም አለመግባባት አግባብነት ባላቸው ሕጎች፣ በዚህ አዋጅ፣ ይህን አዋጅ መሰረት በማድረግ በሚወጣው መመሪያ እና በውሉ መሠረት መፈታት አለበት፡፡

5/ Completion of Contract

a) public Bodies shall ensure that the performance of a contract for procurement or sale of disposable property and other transactions incidental to such contract are completed in accordance with the terms and conditions of the contract,

b) the Public Body shall settle pending activities with the supplier or buyer of disposable property and third parties involved in the performance of the contract and evaluate the performance of the contract.

6/ Termination of Contract

Contract may be terminated in accordance with the terms and conditions of a contract signed between the Public Body and the supplier.

**7/** Civil Code

The provisions of the civil code shall apply as the case may be on this sub-section.

**66. <u>Contract Dispute Settlement</u>**

1/ Any dispute arising between a Public Body and a supplier or a buyer of disposable property in connection with the performance of a contract of procurement or sale of disposable property shall be settled in accordance with other relevant laws, this Proclamation, the Directive issued hereunder and the contract.

፪/ በዚህ አዋጅ መሠረት ለሚፈፀሙ የግዥና ንብረት ማስወገድ ተግባራት የመንግሥት ተቋማት በሚገቧቸው ውሎች የሚፈጠርን አለመግባባት ለመፍታት አማራጭ የግጭት መፍቻ ዘዴዎችን ሊጠቀሙ ይችላሉ፡፡ ዝርዝሩ ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚያወጣ መመሪያ ይወሰናል።

**ምዕራፍ አሥር**

**ይግባኝ አጣሪና ውሳኔ ሰጪ ቦርድ ስለማቋቋም**

፷፯. **ስለቦርዱ መቋቋም**

፩/ በመንግሥት ግዥ አፈፃፀም እና የንብረት አወጋገድ ላይ የሚቀርቡ ይግባኞችን አጣርቶ ውሳኔ የሚሰጥ ከፊል የዳኝነት ሥልጣን ያለውና ገለልተኛ የሆነ የይግባኝ አጣሪ እና ውሳኔ ሰጪ ቦርድ (ከዚህ በኋላ "ቦርድ" እየተባለ የሚጠራ) በዚህ አዋጅ እንደገና ተቋቁሟል፡፡

፪/ ቦርዱ ለሚኒስትሩ ተጠሪ ይሆናል፡፡

፫/ ቦርዱ እንደ አስፈላጊነቱ ንዑስ ኮሚቴዎች ይኖሩታል፡፡

፬/ ቦርዱ የሥራ ክንውኑን የሚያሳይ ዓመታዊ ሪፖርት ለሚኒስትሩ ያቀርባል፡፡

፷፰. **የቦርዱ አባላት አሰያየም እና የሥራ ዘመን**

፩/ የቦርዱ ሰብሳቢና አባላት በሚኒስትሩ የሚሰየሙ ይሆናል፡፡

፪/ የቦርዱ አባላት ብዛት ከ፭ የማያንስ ከ፯ የማይበልጥ ሆኖ ከፍትህ ሚኒስቴር፣ ከንግዱ ማኅበረሰብ፣ ከሲቪል ማህበረሰብ፣ ከሙያ ማህበራት እና አግባብነት ካላቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የተውጣጡ ይሆናል፡፡

2/ Public Bodies may use alternative dispute resolution mechanisms to resolve disputes arising in connection with procurement or disposable property contracts made in accordance with this Proclamation. Details shall be determined by a Directive to be issued by the Ministry in accordance with this Proclamation.

**CHAPTER TEN**

**ESTABLISHMENT OF BOARD OF APPEAL**

67. **Establishment of the Board**

1/ There is here by re-established aBoard (hereinafter referred to as the "Board") as a quasi-judicial and impartial body which investigates and decides on appeals lodged in regard to the conduct of public procurement and property disposal.

2/ The Board shall be accountable to the Minister.

3/ The Board may have sub-committees as necessary.

4/ The Board shall submit annual performance report to the Minister.

68. **Appointment and Term of Service of Members of the Board**

1/ The chairperson and members of the Board shall be appointed by the Minister.

2/ With their number being not less than 5 and not more than 7, members of the Board shall be drawn from the Ministry of Justice, the business sector, professional associations, civic associations and the relevant public bodies.

፫/ ባለስልጣኑ የቦርዱ ጸሐፊ በመሆን ያገለግላል፡፡

፬/ የቦርድ አባላት አሰያየም በብቃት ላይ የተመሠረተ ሆኖ በግዥ፣ በምህንድስና፣ በጤና፣ በግብርና፣ በፋይናንስ ወይም በሕግ ሙያ የትምህርት ዝግጅት፣ በመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር በቂ ዕውቀትና ልምድ ያካበቱ እና መልካም ሥነ-ምግባር ያላቸው መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

፭/ ማንኛውም የቦርዱ አባል በዚህ ምዕራፍ መሠረት ግዴታውን በአግባቡ ለመወጣት በፈፀመው ድርጊት ወይም አለማድረግ ምክንያት ምንም ዓይነት ክስ ሊቀርብበት አይችልም፡፡

፮/ ከዚህ በላይ ባሉት ንዑሳን አንቀጾች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የቦርዱ አባላት አሰያየም በተቻለ መጠን የፆታ ተዋፅዖን ከግምት ያስገባ መሆን አለበት፡፡

፯/ የቦርዱ አባላት የሥራ ዘመን ሦስት ዓመት ሲሆን፣ እንደአስፈላጊነቱ ለተጨማሪ አንድ የሥራ ዘመን ሊራዘም ይችላል፡፡

፰/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፯ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ሚኒስትሩ የመጀመሪያው የሥራ ዘመን ተጠናቆ የቦርዱ አባላት በሌሎች እስኪተኩ ድረስ የቦርዱን ሰብሳቢ ጨምሮ የአባላቱን የሥራ ዘመን ለተጨማሪ ስድስት ወራት ሊያራዝም ይችላል፡፡

፱/ ሚኒስትሩ ለቦርዱ አባላት የሚከፈለውን አበል መጠን እና የክፍያ አፈፃፀም ይወስናል፡፡

3/ The Authority shall serve as a secretariat to the Board.

4/ Appointment to membership of the Board shall be based on competency and persons to be appointed as members of the Board shall be required to have adequate knowledge and work experience in the fields of procurement, engineering, agriculture, health, finance or law and to have good character and ethical standing.

5/ No member of the Board shall be liable to any suit for any act or omission done in the proper execution of his duties.

6/ Without prejudice to the provisions of the foregoing Sub-Article of this Article, the appointment of members of the Board shall as far as possible take into account gender composition.

7/ The term of service of members of the Board shall be three years with the possibility of extension for one more term if the need arises.

8/ Without prejudice to the provision of Sub-Article (7) of this Article, upon completion of the term of service of the incumbent members of the Board, the Minister may extend the term for not more than six months until they are replaced by new members.

9/ The Minister shall determine the amount of allowance paid to members of the Board and the mode of payment.

## ፷፱. የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ ይግባኝ አቅራቢው እና መሥሪያ ቤቱ ጉዳያቸውን በስምምነት ካልፈቱ በስተቀር ከተወዳዳሪዎች ወይም ከተጫራቾች የሚቀርቡ ይግባኞችን መርምሮ ውሳኔ የመስጠት፤

፪/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ዓላማ ሰነዶች፣ መዛግብት፣ ሪፖርቶች እና ማናቸውም ሌሎች ማስረጃዎች ከመንግሥት መሥሪያ ቤቶች፣ ከተወዳዳሪዎች ወይም ከተጫራቾች እና ከሌላ ማንኛውም ሰው እንዲቀርቡለት የማዘዝ፣

፫/ ምስክሮችን በመጥራት፣ ምስክሮችና ግዥው ወይም የሚወገደው ንብረት ሽያጭ የሚመለከታቸው ወገኖች ቃላቸውን በመሐላ እንዲሰጡ የማድረግ፤

፬/ ጉዳዩን መርምሮ በይግባኙ ላይ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ የጽሁፍ ማስታወቂያ በመስጠት የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ክርክር ከተነሳበት የግዥ ወይም የንብረት ማስወገድ ሂደት ጋር በተያያዘ ቀጣይ እንቅስቃሴ እንዳያደርግ የማገድ፤

፭/ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም መሥሪያ ቤት ወይም ድርጅት ቢሮ በአካል በመገኘት ምርመራ የማድረግ፤

፮/ የቀረበለትን ይግባኝ በማጣራት እና ውሳኔ በመስጠት ሂደት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ከሚመለከተው ሰው ሙያዊ እገዛ የመጠየቅ እና የማግኘት፤

፯/ እንደአስፈላጊነቱ የሰነድ ምርመራ ወይም የችሎት ስሚ በማድረግ ይግባኝ የቀረበበት የግዥ አፈፃፀም ወይም የሚወገድ ንብረት ሽያጭ ሂደት እንዲስተካከል ወይም ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲቋረጥ የመወሰን፤

## 69. Powers and Duties of the Board

The Board shall have the following powers and duties:

1/ Unless the Public Body and the appellant agree to settle their dispute amicably, investigate and decide on appeal from any candidate or bidder;

2/ For the purpose of Article (1) of this Article, require documents, record, reports and any other evidence from Public Bodies, candidates, bidders, or from any other person;

3/ Summon witnesses and the parties concerned with the procurement or sale of disposable property, and cause them to give testimony under oath;

4/ Suspend by a written notice, further action of the Public Body in connection with the proceedings of procurement or sale of disposable property in dispute until it investigates the matter and gives decision on the appeal;

5/ Conduct investigation in person at the office of a Public Body or an organization where necessary;

6/ Seek professional assistance from any appropriate person where it finds such assistance necessary in disposing of any appeal submitted to it;

7/ Decide that a proceeding of procurement or sale of disposable property in respect of which appeal was lodged be rectified or be fully or partially terminated by examination of documents or by hearing as necessary;

፰/ ተገቢ ሆኖ ካላገኘው የተወዳዳሪውን ወይም የተጫራቹን ይግባኝ ውድቅ የማድረግ፡፡

8/ Dismiss any appeal of a candidate or bidder which in its view is untenable.

## ፸. የቦርዱ የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት

፩/ የቦርድ አባላት ሥራቸውን ለማከናወን ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባሉ፤ ሆኖም እንደአስፈላጊነቱ ቦርዱ ከዚህ ባነሰ ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል፡፡

፪/ በማናቸውም ስብሰባ ከአባላቱ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ከተገኙ ምልዓተ-ጉባኤ ይሆናል፡፡

፫/ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ሰብሳቢው በስብሰባው ላይ የማይገኝ ሲሆን፣ ስብሰባውን በጊዜያዊነት የሚመራለት ሰብሳቢ ከአባላቱ መካከል ሊወክል ይችላል፡፡

፬/ የቦርዱ አባላት በተቻለ መጠን በስምምነት ውሳኔዎችን ያሳልፋሉ፣ ሆኖም በስምምነት ውሳኔ ማሳለፍ ካልተቻለ በድምፅ ብልጫ ይወስናሉ፣ ድምፅ እኩል በሚሆንበት ጊዜ የቦርዱ ሰብሳቢ ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል፡፡

፭/ ማንኛውም የተለየ የውሳኔ ሀሳብ ያለው አባል ሀሳቡ በልዩነት እንዲያዝለት ከጠየቀ የልዩነት ሀሳቡ በውሳኔው ቃለ-ጉባኤ እንዲካተት ይደረጋል፡፡

## 70. Meeting Procedure of the Board

1/ Members of the Board shall meet to discharge their duty once a Month, provided; however, that they may convene within a shorter period if the need arises.

2/ There shall be a quorum where more than half of the members of the Board are present in any meeting.

3/ The chairperson may represent a member to act on his behalf where he cannot attend a meeting of the Board for good reason.

4/ Members of the Board shall, as far as possible, pass decisions by consensus; however, if consensus cannot be reached, decisions shall be passed by a majority vote, provided that the chairperson shall have a casting vote in case of a tie.

5/ Any member of the Board holding dissenting opinion from the majority may require that statement of his opinion be recorded in the minutes of the decision.

## ፸፩. ከቦርድ አባልነት ስለመሰናበት

፩/ ሰብሳቢውን ጨምሮ ማንኛውም የቦርዱ አባል በማንኛውም ጊዜ ከቦርድ አባልነት የመልቀቂያ ማመልከቻ ለሚኒስትሩ በማቅረብ ሲፈቅደለት መልቀቅ ይችላል፡፡

፪/ ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ የቦርድ ሰብሳቢ ወይም አባል ከአባልነት ሊሰናበት ይችላል፡-

ሀ) በአዕምሮ ወይም ከልካይ የአካል ጉዳት ምክንያት ኃላፊነቱን መውጣት ካልቻለ፣

## 71. Removal From Membership of the Board

1/ Any member of the Board including the chairperson may at any time terminate his membership of the Board by submitting a request of resignation to the Minister and where such request is accepted.

2/ The Chairperson or any member of the Board may be removed for one of the following reasons:

a) where he cannot continue to discharge his duty by reason of mental or preventive physical disability,

ለ) በወንጀል ተከሶ ጥፋተኛነቱ በፍርድ ቤት ከተረጋገጠ፣

ሐ) የሥነ-ምግባር ወይም የዲሲፕሊን ጉድለት ከተገኘበት፣

መ) የተሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ ካልተወጣ ወይም ያለ በቂ ምክንያት በተደጋጋሚ የቦርዱ ስብሰባዎች ላይ ካልተገኘ፡፡

## ፸፪. የጥቅም ግጭትን የማሳወቅ ግዴታ

፩/ የቦርዱ ሰብሳቢ ወይም ማንኛውም የቦርዱ አባል ከይግባኝ አቅራቢው ወይም ይግባኝ ከቀረበበት ግዥ አፈጻጸም ወይም የሚወገድ ንብረት ሽያጭ ጋር በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ዝምድና ወይም የጥቅም ግንኙነት ካለው ይህንኑ እንደሁኔታው ለቦርዱ ሰብሳቢ ወይም ለቦርዱ አባላት በማሳወቅ ከቦርዱ ስብሰባ ራሱን ማግለል አለበት፡፡

፪/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እንዲሁም ለአንቀጽ ፸፩ ንዑስ አንቀጽ (፪) ፊደል ተራ (ለ)፣ (ሐ) እና (መ) አፈፃፀም ሚኒስትሩ የቦርዱ አባላት የሚተዳደሩበትን የሥነ-ምግባር ደንብ ያወጣል፡፡

## ምዕራፍ አሥራ አንድ
## የአቤቱታ እና ይግባኝ አቀራረብና አወሳሰን ሥርዓት

## ፸፫. ጠቅላላ ድንጋጌዎች

፩/ ከመንግሥት ግዥ ወይም የሚወገድ ንብረት ሽያጭ ጋር በተያያዘ ግዥውን በሚፈፅመው ወይም ንብረቱን በሽያጭ በሚያስወግደው የመንግሥት መሥሪያ ቤት የተከናወነው ወይም ሳይከናወን የቀረው ተግባር ይህንን አዋጅ፣ የመንግሥትና የግል አጋርነት አዋጅና ተያያዥ ድንጋጌዎች፣ የአፈፃፀም መመሪያዎቹንና

b) where he is convicted of crime by a competent court,

c) where he is found to be involved in ethical or disciplinary misconduct,

d) where he fails to properly discharge his responsibility or to attend meetings of the Board frequently.

## 72. Obligation to Disclose And Conflict of Interest

1/ The chairperson or any member of the Board having direct or indirect interest with proceedings of procurement or sale of disposable property in respect of which an appeal is lodged or related to the appellant shall disclose this fact to the chairperson or the members of the Board, as the case may be, and withdraw from the proceeding of the Board in which the complaint is considered.

2/ For the purpose of Sub-Article (1) of this Article and paragraphs (b), (c) and (d) of Sub-Article (2) of Article 71, the Minister shall issue a code of ethics governing the conduct of members of the Board.

## CHAPTER ELEVEN
## PROCEDURE FOR LODGING AND DISPOSING OF COMPLAINTS AND APPEALS

## 73. General

1/ Any candidate or bidder is entitled to submit a complaint or an appeal within the time limit stipulated herein, to the head of the Public Body or to the Board, as the case may be, against an act or an omission of the Public Body in regard to the conduct of public procurement or sale of

በጨረታ ሰነዱ ላይ የተመለከቱትን ሁኔታዎች ይጥሳል ብሎ የሚያምን እና በመሥሪያ ቤቱ አሠራር ምክንያት የደረሰበትን ወይም ሊደርስበት የሚችልን ጉዳት ማሳየት የሚችል ተወዳዳሪ ወይም ተጫራች በሕጉ በተፈቀደለት ጊዜ ውስጥ ለመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ አቤቱታ ወይም በደረጃ ለቦርዱ ይግባኝ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚቀርብ አቤቱታ ወይም ይግባኝ ሊታይ የሚችለው ግዥ ፈፃሚው ወይም ንብረት አስወጋጅ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ በአሸናፊነት ከተመረጠው ተጫራች ጋር ውል ከመግባቱ በፊት የቀረበ ከሆነ ብቻ ነው፡፡

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ ቢኖርም ከሚከተሉት ሁኔታዎች በአንዱ ምክንያት ውል ከተፈረመ በኋላ የሚቀርብ አቤቱታ ወይም ይግባኝ ሊታይ ይችላል፡-

ሀ) ውሉ የተፈረመው በዚህ አዋጅ መሠረት የተቀመጠው የአቤቱታ ወይም የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ከመጠናቀቁ በፊት ከሆነ፣

ለ) ውሉ የተፈረመው የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ለቀረበበት አቤቱታ ምላሽ ከሰጠ በኋላ ሆኖ በዚህ አዋጅ እና በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው መመሪያ ውል ለመፈረም የተቀመጠው ጊዜ ከመጠናቀቁ በፊት ከሆነ፣

ሐ) በዚህ አዋጅና በአፈፃፀም መመሪያው መሠረት የጨረታው ውጤት ለተጫራቾች ሳይገለፅ ውል የተፈረመ ከሆነ፣

disposable property where he believes that such an act or an omission violates this Proclamation, the Public and Private Partnership Proclamation, the Directives issued hereunder or the conditions stated in the bid document and can show that he has sustained or is likely to sustain damage as a result of such action or inaction of the Public Body.

2/ Complaint or appeal lodged pursuant to Sub-Article (1) of this Article will be heard if it is lodged before the contract had been signed with the successful bidder.

3/ Notwithstanding the provision of Sub-Article (2) of this Article, a complaint or an appeal lodged after a contract had been signed may be admitted under any of the following conditions:

a) where the contract is signed before the expiration of the time limit for lodging complaint set in this Proclamation,

b) where the contract was signed after the Public Body had responded to the complaint lodged against it but before the expiration of the time limit set in this Proclamation or the Directive issued hereunder for signing contract,

c) where the contract is signed without the result of the bid evaluation being notified to all bidders in accordance with this Proclamation and the Directive to be issued hereunder.

፬/ በመንግሥት የግዥ አፈፃፀምና የሚወገድ ንብረት ሽያጭ ላይ የሚቀርብ አቤቱታና ይግባኝ የሚጣራበት ዝርዝር የአሠራር ሥርዓት በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

**፸፬. <u>ለመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ ስለሚቀርብ አቤቱታ</u>**

፩/ በመንግሥት መሥሪያ ቤቱ በተከናወነ ወይም ሳይከናወን በቀረ ተግባር ምክንያት የሚቀርብ አቤቱታ በመጀመሪያ ደረጃ ለመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ መቅረብ አለበት፡፡

፪/ ተጫራቹ አቤቱታውን ሊያቀርብ የሚችለው ለአቤቱታው መሠረት የሆነውን ምክንያት ወይም ውሳኔ ካወቀበት ወይም ማወቅ ይገባው ከነበረበት ቀን ቀጥሎ ካለው ቀን ጀምሮ በሚቆጠር በ፭ (አምስት) የሥራ ቀናት ውስጥ ይሆናል፡፡

፫/ አቤቱታው በሁለቱ ወገኖች መካከል በሚደረግ ስምምነት ካልተፈታ በስተቀር የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ የግዥውን ወይም የንብረት ማስወገዱን ሂደት በማገድ አቤቱታው ከቀረበበት ቀን ቀጥሎ ካለው ቀን ጀምሮ በሚቆጠር ፯ (ሰባት) የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት እና የሰጠውን ውሳኔ ፍሬ ነገር በኤሌክትሮኒክ ሥርዓት መሠረት ይፋ ማድረግ አለበት፡፡

፬/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ የቀረበውን አቤቱታ ለመቀበል ወይም ውድቅ ለማድረግ ሊወስን ይችላል፡፡

4/ Details pertaining to the procedure of complaint and appeal shall be set forth in the Directive issued hereunder.

**74. <u>Complaint Lodged to the Head of a Public Body</u>**

1/ Any complaint against an act or an omission by a Public Body in regard to a conduct of public procurement or sale of disposable property shall, in the first instance, be submitted to the head of the Public Body.

2/ Any candidate or bidder shall submit his complaint within 5 (five) working days next following the date on which he knew or should have known of the circumstance or decision giving rise to the complaint.

3/ Unless the complaint is resolved by mutual agreement, the head of the Public Body shall suspend the procurement or property disposal proceedings and shall, within 7 (seven) working days after the submission of the complaint, issue a written decision on the complaint and cause the summary of the decision to be disclosed using the electronic system.

4/ The head of the Public Body may decide to uphold or dismiss the complaint.

፭/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ አቤቱታውን ለመቀበል ከወሰነ በቀረበው አቤቱታ ላይ ሊደረግ የሚገባውን ማስተካከያ፣ አቤቱታውን ውድቅ ካደረገ ደግሞ ምክንያቱን በውሳኔው መግለፅ አለበት፡፡

፸፭. <u>ለቦርዱ ይግባኝ ስለሚቀርብበት ሥነ-ሥርዓት</u>

፩/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፸፬ ንዑስ አንቀጽ (፫) በተገለፀው ጊዜ ውስጥ በቀረበው አቤቱታ ላይ ውሳኔ ካልሰጠ ወይም አቤቱታ አቅራቢው በተሰጠው ውሳኔ ያልረካ ከሆነ፣ ውሳኔው ከተገለጸለት ወይም ሊገለጽለት ይገባ ከነበረበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር ፭ (አምስት) የሥራ ቀናት ውስጥ ለቦርዱ ይግባኝ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፸፬ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም ጨረታ ከመከፈቱ አስቀድሞ በጨረታ ሰነዱ ይዘት ላይ ከግዥ ፈፃሚው መሥሪያ ቤት በሚሰጥ የማሻሻያ ወይም የማብራሪያ ምላሾች ላይ ቅሬታ ያለው ተወዳዳሪ የማሻሻያው ወይም የማብራሪያው ምላሽ ከደረሰው ወይም ምላሽ ሊሰጠው ይገባው ከነበረበት ቀን አንስቶ በ፭ (አምስት) የሥራ ቀናት ውስጥ ለቦርዱ ይግባኝ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

፫/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፩ ድንጋጌዎች መሠረት በጨረታ ሰነዱ ይዘት ላይ ማሻሻያ ሲያደርግ ወይም ለቀረበ የማብራሪያ ጥያቄ ምላሽ ሲሠጥ ተወዳዳሪዎች ቅሬታ ያላቸው እንደሆነ

5/ If the head of the Public Body decides to uphold the complaint, the decision shall indicate the corrective measure that has to be taken to address the complaint or if the complaint is dismissed, the reason for dismissing the complaint shall be stated in the decision.

**75. <u>Procedure of Appeal to the Board</u>**

1/ If the head of the Public Body does not give decision on the complaint within the time limit stated in Sub-Article (3) of Article 74, or if the complainant is not satisfied with the decision of the head of the Public Body, the complainant is entitled to lodge appeal to the Board within 5 (five) working days next following the date on which the decision was or should have been communicated to the complainant by the Public Body.

2/ Notwithstanding the provision of Sub-Article (1) of Article 74 of this Proclamation, any candidate not satisfied with the response of the Public Body to inquiries of candidates concerning any modification on the content of the bid document made by the Public Body or clarification thereon before the opening of the bid may lodge appeal directly to the Board within 5 (five) days from the date on which he received or should have received such response.

3/ When modifying the content of the bid document pursuant to Article 51 of this Proclamation or responding to inquiries of candidates, the Public Body shall defer or extend the closing date for submission of bids by 5 (five) working days from the

ጨረታው ሳይከፈት ይግባኙን በቀጥታ ለቦርዱ ለማቅረብ እንዲያስችላቸው ምላሽ ከሰጠበት ወይም ምላሽ ሊሰጥ ከሚገባው ቀን አንስቶ ለ፭ (አምስት) የሥራ ቀናት ጨረታው ሳይዘጋ እንዲቆይ ማድረግ ወይም የጨረታ መዝጊያ ቀኑን ማራዘም አለበት፡፡

፬/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፯ ንዑስ አንቀጽ (፭) መሠረት በፀደቀ ግዥ ላይ የሚቀርብ ይግባኝ ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ቀጥሎ ካለው ቀን ጀምሮ በሚቆጠር ፭ (አምስት) የሥራ ቀናት ውስጥ በቀጥታ ለቦርዱ ሊቀርብ ይችላል፡፡

**፸፮. <u>ቦርዱ በቀረበለት ይግባኝ ላይ ስለሚወስዳቸው እርምጃዎች</u>**

፩/ ቦርዱ ይግባኝ ሲቀርብለት ወዲያውኑ ለሚመለከተው የመንግሥት መሥሪያ ቤት ይግባኝ የቀረበበት መሆኑን የሚገልፅ ማስታወቂያ ይልካል፡፡

፪/ ቦርዱ ከሚቀርብለት ይግባኝ ጭብጥ እና ይዘት በመነሳት ለመንግሥት መሥሪያ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በሚልከው ማስታወቂያ እንደሁኔታው የጨረታ ሂደቱ ወይም የመሥሪያ ቤቱ ውሳኔ እንዲታገድ ወይም ሳይታገድ እንዲጣራ ሊያደርግ ይችላል፡፡

፫/ ቦርዱ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ የጨረታው ሂደት እንዲታገድ ለመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ካሳወቀ ይግባኝ የቀረበበት የመንግሥት መሥሪያ ቤት ይህ ማስታወቂያው ሲደርሰው ማናቸውም ቀጣይ እንቅስቃሴ ወዲያውኑ ማቆምና የይግባኙ ማስታወቂያ ከደረሰው ቀን ጀምሮ በሚቆጠር ፭(አምስት) የሥራ ቀናት ውስጥ መልሱን ከደጋፊ የሰነድ

date of its response or from the date it is supposed to respond, to give time for candidates to lodge appeal directly to the Board.

4/ Notwithstanding the provision of Sub-Article (1) of this Article, appeal on the conduct of procurement endorsed in accordance with Sub-Article (5) of Article 7 may be submitted directly to the Board within 5 (five) working days next following the date of the decision.

**76. <u>Measures to be Taken by the Board on the Appeal</u>**

1/ Upon receipt of any appeal, the Board shall promptly give notice of the appeal to the Public Body concerned.

2/ Based on the content and substance of the appeal, the Board may, by the notice it sends to the Public Body pursuant to Sub Article (1) of this Article, cause the investigation of the bid proceedings or the decision of the Public Body as the case may be, by suspending or without suspending the bid proceedings or the decision.

3/ Where the Board notifies the Public Body to suspend the bidding Process until it issues decision on the matter, the Public Body against which the appeal was lodged shall, upon receipt of notification of the appeal, immediately suspend any further action and submit its statement of response on the appeal to the Board

ማስረጃ ጋር በጽሑፍ ለቦርዱ ማቅረብ አለበት፡፡

together with documentary evidence supporting the statement within 5 (five) working days from the date on which it received the notification.

፬/ ቦርዱ በይግባኙ ላይ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት በውሳኔው ጥቅማቸው ሊነካ ከሚችሉ አካላት የሚቀርቡ ጥያቄዎችን በመመርመር በክርክሩ እንዲሳተፉ ሊፈቅድ ይችላል፣ ከእነዚህ አካላት የቀረበ መረጃ እና መከራከሪያ ሀሣብ ካለ መስማትና መመርመር አለበት፡፡

4/ Before taking decision on any appeal, the Board may examine requests and allow any party whose interest may be affected by the decision of the Board to participate in the proceeding, and investigate the evidence presented to it and hear the arguments of the intervening parties.

፭/ ቦርዱ ይግባኝ የቀረበበት የመንግሥት መሥሪያ ቤት የሰጠው ምላሽ ከደረሰው ወይም ሊደርሰው ይገባ ከነበረበት የመጨረሻ ቀን ቀጥሎ ባሉት ፲፭ (አስራ አምስት) የሥራ ቀናት ለውሳኔው መሠረት የሆኑትን ምክንያቶች እና የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች ካሉ በመጥቀስ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

5/ The Board shall give decision on the appeal within 15 (fifteen) working days following the date on which it received or from the last day on which it should have received the statement of response of the Public Body against which an appeal was lodged, stating the reasons for its decision and the remedies granted, if any.

፮/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) ድንጋጌ ቢኖርም እንደ ጉዳዩ ውስብስብነት እና ፍትሐዊ ውሳኔ ለመስጠት አስፈላጊ ነው ብሎ ሲያምን ቦርዱ ለተከራካሪ ወገኖች በሚላክ የጽሑፍ ማስታወቂያ የውሳኔ መስጫ ጊዜውን ከ፲ (አስር) የሥራ ቀናት ላልበለጠ ጊዜ ሊያራዝም ይችላል፡፡

6/ Notwithstanding the provision of Sub-Article (5) of this Article, the Board may, by notice in writing to the parties to an appeal, extend the period for deciding the appeal for a period not exceeding 10 (ten) working days having regard to the complexity of the issues in the case and the interests of justice.

፯/ ቦርዱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) ወይም (፮) የተመለከተውን የጊዜ ገደብ ሳይጠብቅ መቅረቱ ቦርዱ የሰጠውን ውሳኔ ተቀባይነት ሊያሳጣው አይችልም፡፡

7/ Failure by the Board to comply with the time framework stipulated in Sub-Article (5) or (6) of this Article shall not affect the validity of the decision of the Board on the appeal.

፰/ የተከራካሪዎችን የመደመጥ መብት ሳያጣብብ ቦርዱ የፍትሐብሔር ክርክሮችን ለመዳኘት በመደበኛ ፍርድ ቤቶች በሚሰራባቸው የሥነ ሥርዓት እና የመረጃ አቀራረብ ደንቦች ሳይወሰን በሌላ ቀለል ባለ ሥነ-ሥርዓት መጠቀም ይችላል፡፡

፸፯. **ቦርዱ የሚሰጣቸው ውሳኔዎች**

፩/ ቦርዱ በቀረበለት ይግባኝ ላይ ምርመራ ካደረገ በኋላ፡-

ሀ) ተገቢ ሆኖ ካላገኘዉ የተወዳዳሪውን ወይም የተጫራቹን ይግባኝ ውድቅ የማድረግ፣

ለ) የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ሕጉን ያልጠበቀ ተግባር እንዳያከናውን እና ውሳኔ እንዳይሰጥ የማገድ፣

ሐ) አሸናፊውን ተጫራች የመምረጥ ወይም ውል የመፈረም ውሳኔዎችን ከመስጠት በስተቀር የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ሕጉን ተከትሎ ሥራውን እንዲያከናውን፣ወይም

መ) የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ከሕግ ውጪ ያከናወነው ተግባር ወይም የሰጠው ውሳኔ በሙሉ ወይም በከፊል ቀሪ እንዲሆን፣ ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል፡፡

፪/ ይግባኝ የቀረበበት የመንግሥት መሥሪያ ቤት የቦርዱን ውሳኔ ተግባራዊ ስለማድረጉ ውሳኔው ከደረሰው ቀን ጀምሮ በሚቆጠር ፲ (አሥር) የሥራ ቀናት ውስጥ ግብረ መልስ መስጠት አለበት፡፡

፫/ ቦርዱ ይግባኙን በማጣራት ሂደት ከቀረበለት የይግባኝ ጭብጥ ውጪ የሚያገኛቸውን ግድፈቶች በአቤቱታው ላይ ለሚሰጠው ውሳኔ ሊጠቀምባቸው አይችልም፡፡

8/ Without prejudice to due process of law, in disposing of any appeal submitted to it, the Board may use flexible procedure without being bound by the rules of procedure followed by the regular courts of law in adjudicating civil disputes.

77. **Decision of the Board**

1/ Upon due consideration of the appeal brought to it by the candidate or the bidder, the Board may:

a) dismiss the appeal if it determines that it is not tenable,

b) prohibit the Public Body from acting unlawfully or giving illegal decision,

c) order the Public Body to proceed in conformity with the law other than giving decision of award or conclusion of contract,

d) annul in whole or in part, the unlawful act or decision of the Public Body.

2/ The Public Body against which an appeal was lodged shall report to the Board on the execution of the Board's decision within 10 (ten) working days of receipt of the decision.

3/ The Board shall not bring to bear on its decision any unrelated fact that came to its knowledge in the course of reviewing any complaint.

**፸፰. የቦርዱን ውሳኔ ለሕዝብ ተደራሽ ማድረግ**

ቦርዱ በቀረበለት ይግባኝ ላይ የሚያስተላልፋቸውን ውሳኔዎች ፍሬ ነገር እንዲሁም እንደሁኔታው የምርመራ ሂደቱ ያለበትን ደረጃ የሚያሳዩ መረጃዎችን በኤሌክትሮኒክ ሥርዓት መሠረት ለሕዝብ ይፋ ያደርጋል፡፡

**፸፱. ውሳኔን በድጋሚ ስለማየትና ስለማረም**

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፸፯ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ቦርዱ ከተከራካሪ ወገኖች በቀረበለት ማመልከቻ ወይም በራሱ በማንኛውም ይግባኝ ላይ የሰጠው ውሳኔ በቀረበለት ሐሰተኛ ማስረጃ ላይ የተመሠረተ መሆኑን ሲረዳ ወይም በሰጠው ውሳኔ ላይ መሠረታዊ ለውጥ ሊያስከትል የሚችል አዲስ ማስረጃ ሲቀርብለት ቦርዱ ውሳኔ የሰጠበትን ይግባኝ በድጋሚ ሊያይ ይችላል፡፡

፪/ ቦርዱ የሰጠው ውሳኔ ወይም ውሳኔው የተመሠረተበት የምክንያት መግለጫ ይዘት ስህተት እንዳለበት የተረዳ እንደሆነ፣ የውሳኔውን ወይም ውሳኔው የተመሰረተበትን የምክንያት መግለጫ ይዘት ሊያሻሽል ይችላል፡፡

፫/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) አፈፃፀም የውሳኔ ወይም ውሳኔ የተመሠረተበት የምክንያት መግለጫ ይዘት ስህተት፦

ሀ) የሕትመት ወይም የአፃፃፍ ስህተትን፤ ወይም

ለ) በውሳኔ እና ውሳኔው በተመሠረተበት የምክንያት መግለጫ መካከል የሚታይ ማንኛውንም አለመጣጣም ይጨምራል፡፡

**78. Accessibility of Decisions of the Board**

The Board using the electronic system shall make accessible to the public information pertaining to the content of its decisions on appeals submitted to it and the status of appeals under its consideration.

**79. Review And Correction of Decision By the Board**

1/ Without prejudice to Sub-Article (2) of Article 77 this Proclamation, where upon application by either party or on its own accord, the Board understands that the decision it has given on any appeal was based on false evidence presented to it or where new evidence is brought to the attention of the Board that is likely to prompt material change in its decision, the Board may reconsider its decision on the appeal.

2/ Where the Board understands that the decision it has given on any case brought to it or the reasoning on which the decision was based is erroneous, it may amend the decision or the statement of reason forming the basis of the decision.

3/ For the purpose of Sub-Article (2) of this Article, error of decision or statement of reason for a decision includes:

a) printing or editorial error,

b) incompatibility of the Board's decision with the statement of reason for the decision.

**፹. ይግባኝ ማቅረብ የማይቻልባቸው ጉዳዮች**

፩/ የዚህ ምዕራፍ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም ተወዳዳሪ ወይም ተጫራች በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ለቦርዱ ይግባኝ ማቅረብ አይችልም፦

ሀ) በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት ግዥ ፈጻሚው ወይም ንብረት አስወጋጁ የመንግሥት መሥሪያ ቤት በሚያከናውነው የግዥ ወይም የንብረት ማስወገድ ዘዴዎች ምርጫ፣

ለ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፮ መሠረት ውድቅ በተደረገ ጨረታ፣

ሐ) በመመሪያው የሚገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ በተገደበ ጨረታና በዋጋ ማቅረቢያ ለሚፈፀም ግዥ በተከናወነ የተወዳዳሪዎች አመራረጥ፣

መ) በጨረታ ሰነዱ አስቀድሞ በሰፈረ የተጫራቾች ማወዳደሪያ መስፈርት ላይ ጨረታ ከተከፈተ በኋላ የሚቀርብ ይግባኝ፤

ሠ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፸፫ ንዑስ አንቀጽ (፫) ከተገለፁት ሁኔታዎች በስተቀር በይግባኝ አቅራቢው እና በግዥ ፈፃሚው ወይም የሚወገድ ንብረት ሻጩ የመንግሥት መሥሪያ ቤት መካከል ለይግባኙ መንስዔ የሆነው አለመግባባት የተፈጠረው በዚህ አዋጅ የተቀመጠውን አሠራር ተከትሎ ውል ከተፈረመ በኋላ ከሆነ፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ይግባኙ በዚህ አዋጅ የተደነገጉ የይግባኝ አቀራረብ ሥነ ሥርዓቶችን ሳይከተል የቀረበ ከሆነ በቦርዱ ሊታይ አይችልም፡፡

**80. Matters In Respect of which Appeal may not be Lodged**

1/ Without prejudice to the provisions of this Chapter, any candidate or bidder may not lodge appeal to the Board in respect of the following matters:

a) on the selection of method by the Public Body for procurement or property disposal in accordance with this Proclamation,

b) on the rejection of bid in accordance with Article 26 of this Proclamation,

c) on the selection of candidates for procurement to be executed by means of restricted tendering or request for quotation, subject to the qualification set forth in the Directive to issued hereunder,

d) on the criteria for selection of bidders set forth in the bid document, after the opening of bid,

e) where the dispute between the complainant and the Public Body giving rise to the complaint arose after a contract had been signed following the procedures stipulated in this Proclamation, except under the circumstances specified in Sub-Article 3 of Article 73 of this Proclamation.

2/ Without prejudice to the provision of Sub-Article (1) of this Article, no appeal may be admitted by the Board unless it is lodged in accordance with the procedure stipulated in this Proclamation.

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም በመንግሥት መሥሪያ ቤቱ የግዥ ወይም የንብረት ማስወገድ ሽያጭ አፈፃፀም ተገቢ ያልሆነ አሰራር መኖሩን የሚያምን ማንኛውም ተወዳዳሪ፣ ተጫራች፣ አቅራቢ ወይም የሚወገድ ንብረት ገዥ ጉዳዩን ለመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ወይም ለባለስልጣኑ ወይም እንደሁኔታው ለሌሎች በሕግ ሥልጣን ለተሰጣቸው አካላት በጥቆማ መልክ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

፬/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ለመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ ለሚቀርብ አቤቱታ ጭምር ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ፹፩. ለመደበኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብት

፩/ ቦርዱ በሕግ ትርጉም ረገድ በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ተከራካሪ ወገን ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ቀጥሎ ባሉት ፲፭ (አስራ አምስት) የሥራ ቀናት ውስጥ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በመንግሥት ግዥና ንብረት አወጋገድ ሂደት ቅሬታ ያለው ማንኛውም ወገን በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት የመጨረሻውን አስተዳደራዊ እና ከፊል የዳኝነት መፍትሔ አሟጦ ሳይጠቀም ጉዳዩን ለመደበኛ ፍርድ ቤት ሊያቀርብ አይችልም፡፡

፫/ ይግባኝ የቀረበለት ፍርድ ቤት በይግባኙ ላይ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ የቦርዱ ውሳኔ እንዳይፈፀም ካላዘዘ በስተቀር ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

፬/ የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በሕግ ትርጉም ረገድ ቦርዱ የሰጠውን ውሳኔ ውድቅ የሚያደርግ ከሆነ ፍርድ ቤቱ በሰጠው የሕግ

3/ Notwithstanding the provision of Sub-Article (1) of this Article, any candidate, bidder or supplier alleging improper practice in regard to the execution of public procurement or sale of disposable property in a Public Body, may report such practice to the head of the Public Body, the Authority or any other competent body.

4/ The provision of Sub-Article (1) of this Article shall also apply to complaints lodged to the head of a Public Body at first instance.

## 81. Right to Appeal to a Court of Law

1/ An appeal may be lodged to the Federal High Court on questions of law by any party aggrieved by the decision of the Board within 15 (fifteen) working days next following the date of the decision.

2/ Without Prejudice to the provision of Sub-Article (1) of this Article, any party dissatisfied with the process of Public Procurement and Property disposal, shall not bring his case to adjudication by regular court of law without first exhausting the administrative and quasi-judicial remedies available to it under this Proclamation.

3/ The decision of the Board shall be effective during the course of the appeal unless the court of appeal orders a stay of execution pending decision on the appeal.

4/ If the court of appeal reverses the decision of the Board on a question of law, it shall remand the case to the Board for

ትርጉም መሠረት ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ ለቦርዱ ይመልሳል፡፡ ቦርዱ በፍርድ ቤቱ የተሰጠውን የሕግ ትርጉም መሠረት በማድረግ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

## ምዕራፍ አሥራ ሁለት
## የጥፋተኝነት ሪፖርት የሚቀርብበት እና የሚጣራበት ሥርዓት

**፹፪. ለባለሥልጣኑ ስለሚቀርብ የጥፋተኝነት ሪፖርት**

በመንግሥት ግዥ አፈፃፀም እና ንብረት አወጋገድ ሂደት የመንግሥት መሥሪያ ቤት በተጫራቾች፣ በአቅራቢዎች ወይም በሚወገድ ንብረት ግዥዎች ሕገ ወጥ የሆነ ወይም ሕጋዊ ጥቅሚን የሚጎዳ ድርጊት ተፈፅሞብኛል ብሎ ሲያምን በጨረታ ሰነዱ ወይም በውል ስምምነቱ መሠረት የሚወስዳቸው እርምጃዎች እንደተጠበቁ ሆነው የጥፋተኝነት ሪፖርት ለባለሥልጣኑ በኤሌክትሮኒክ ሥርዓት መሠረት ማቅረብ አለበት፡፡

**፹፫. ባለሥልጣኑ በቀረበለት የጥፋተኝነት ሪፖርት ላይ ስለሚወስዳቸው እርምጃዎች**

፩/ ባለሥልጣኑ ከመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የጥፋተኝነት ሪፖርት ሲቀርብለት የጥፋተኝነት ሪፖርት የቀረበ መሆኑን እና የጥፋተኝነት ሪፖርቱን ፍሬ ሀሳብ የሚገልፅ የጽሑፍ ማስታወቂያ የጥፋተኝነት ሪፖርት ለቀረበበት ተጫራች፣ አቅራቢ ወይም የሚወገድ ንብረት ገዥ ይልካል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ከባለሥልጣኑ የጥፋተኝነት ሪፖርት እንደቀረበበት የሚገልጽ ማስታወቂያ የደረሰው ተጫራች፣ አቅራቢ ወይም የሚወገድ ንብረት ገዥ የጥፋተኝነት ሪፖርት ማስታወቂያ ከደረሰው ቀን ጀምሮ በሚቆጠር ፯ (ሰባት) የሥራ ቀናት ውስጥ መልሱን ከደጋፊ የሰነድ ማስረጃ ጋር

reconsideration of the case in light of its interpretation. The Board shall pass a final decision in conformity with the legal interpretation given by the court of appeal.

## CHAPTER TWELVE
## PROCEDURE FOR SUBMISSION AND DISPOSING OF REPORT OF DEFUALT

**82. Report of Default to be Submitted to the Authority**

Where a Public Body believes that an unlawful act or an act prejudicial to its legitimate interest has been committed by bidders, supplier or buyers of disposable property, it shall without prejudice to the measures it is entitled to take against such persons in accordance with the bid document or the contract, submit using the electronic system a report of default to the Authority.

**83. Measures to be Taken by the Authority on Receipt of Report of Default**

1/ Upon receipt of a report of default from a Public Body, the Authority shall send a written notice of the report and the content of the report to the bidder, the supplier or the buyer of disposable property against whom the report of default was filed.

2/ A bidder, supplier or buyer of disposable property receiving notification from the Authority that a report of default is pending against him pursuant to Sub-Article (1) of this Article, shall present using the electronic system to the Authority its statement of response

በኤሌክትሮኒክ ሥርዓት መሠረት ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡

፫/ ባለሥልጣኑ የጥፋተኝነት ሪፖርቱን ለመመርመር እና ውሳኔ ለመስጠት ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው የሰውና የሰነድ መረጃዎችን እንዲሁም ከማናቸውም አካል የሙያ ድጋፍ መጠየቅ እና ማግኘት ይችላል፡፡

**፹፬. <u>ባለሥልጣኑ የሚሰጣቸው ውሳኔዎች</u>**

፩/ ባለሥልጣኑ የጥፋተኝነት ሪፖርት የቀረበበት ተጫራች ወይም አቅራቢ ምላሽ ከደረሰው ቀን ቀጥሎ ወይም ምላሽ መስጠት ይገባው ከነበረበት የመጨረሻ ቀን ቀጥሎ ካለው ቀን ጀምሮ በሚቆጠር ፲፭ (አሥራ አምስት) የሥራ ቀናት ውስጥ የጥፋተኝነት ሪፖርቱን አጣርቶ ውሳኔ መስጠት ይኖርበታል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ባለሥልጣኑ የሚሰጠው ውሳኔ ከሚከተሉት አንዱ ሊሆን ይችላል፡-

ሀ) በሚያደርገው ምርመራ ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘውን ተጫራች ወይም አቅራቢ ወይም የሚወገድ ንብረት ገዥ በማንኛውም የመንግሥት ግዥ እና የንብረት ሽያጭ ሂደት ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ እንዳይሳተፍ የማገድ፣

ለ) ጥፋተኛ ሆኖ ለተገኘውን ተጫራች ወይም አቅራቢ ወይም የሚወገድ ንብረት ገዥ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ የመስጠት፣ ወይም

ሐ) የቀረበውን የጥፋተኝነት ሪፖርት ውድቅ የማድረግ፣

together with documentary evidence supporting the statement within seven (7) working days following receipt of the notification.

3/ Where the Authority finds it appropriate to the investigation and resolution of the report of default, it may summon witnesses to appear in person and give oral testimony, order the production of documentary evidence or seek professional assistance from any appropriate body.

**84. <u>Decision of the Authority</u>**

1/ The Authority shall look into and give decision on the report of default within 15 (fifteen) working days following the date on which the Authority received or the last day on which the Authority should have received the statement of response from the bidder, supplier or buyer of disposable property against whom the report of default was filed.

2/ The Authority may give one of the following decisions pursuant to Sub-Article (1) of this Article:

a) based on the investigation conducted by it, suspend the bidder, supplier or buyer of disposable property who is found to be in default from participating in any proceedings of public procurement or sale of disposable property,

b) give a written warning to the bidder, supplier or buyer of the disposable property found to be in default, or

c) dismiss the report of default.

፫/ ባለሥልጣኑ ከመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ጋር በተያያዘ የወንጀል ክስ የቀረበበትና ጉዳዩ በመደበኛ ፍርድ ቤት ወይም ሌላ ሥልጣን ባለው አካል ታይቶ ጥፋተኛ በመሆኑ የቅጣት ውሳኔ የተሰጠውን ሰው በማንኛውም የመንግሥት ግዥ እና የንብረት ሽያጭ ሂደት እንዳይሳተፍ ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ ያግዳል፡፡

፬/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) አፈፃፀም የፌደራል ፍትህ ሚኒስቴር ጥፋት የፈፀሙ እና ውሳኔ የተሰጠባቸውን ድርጅቶች መረጃ ለባለሥልጣኑ ያቀርባል፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው ቢኖርም ተከራካሪ ወገኖች ጉዳያቸውን በስምምነት እልባት የሚሰጡበት፣ የጥፋተኝነት ሪፖርት የቀረበበት ድርጅት ጥፋቱን ተቀብሎ ግዴታውን ሲወጣ ወይም ጥፋቱን ሲያርም ባለሥልጣኑ ውሳኔ የሚሰጥበት አግባብ በመመሪያው ይወሰናል፡፡

፮/ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የቀረበለትን የጥፋተኝነት ሪፖርት መርምሮ ውሳኔ በመስጠት ሂደት በወንጀል የሚያስጠይቅ ድርጊት የተፈፀመ መሆኑን ሲያረጋግጥ ጉዳዩን ለመመርመር እና እርምጃ ለመውሰድ በሕግ ሥልጣን ለተሰጠው የሕግ አስፈፃሚ አካል ያሳውቃል፡፡

፯/ ባለሥልጣኑ ከመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሚቀርቡለትን የጥፋተኝነት ሪፖርቶች የሚመረምርበትን እና ውሳኔ የሚሰጥበትን ዝርዝር አሠራር በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

3/ The Authority shall suspend, for a definite or indefinite period of time from participating in any proceedings of public procurement or sale of disposable property, any person who is accused of a criminal offense in connection with public procurement or property administration and sentenced up on conviction for such offense by a court or any other competent body.

4/ For the purpose of Sub-Article (3) of this Article, the Federal Ministry of Justice shall supply data to the Authority concerning persons who are convicted and sentenced for such offense.

5/ Notwithstanding the provision of Sub-Article (2) of this Article, the conditions in which the Authority may decide otherwise where the parties agree to resolve their dispute amicably or the person against whom the report of default is filed admits its fault and agrees to correct the default shall be determined in the Directive issued hereunder.

6/ In disposing of a report of default submitted to it pursuant to Sub-Article (1) of this Article, the Authority shall report the case to the entity that is competent to conduct investigation and take any appropriate measure where it determines that the case constitutes a criminal offense.

7/ Details pertaining to the procedure for investigation and resolution of reports of default submitted to the Authority by public bodies shall be provided in the Directive issued hereunder.

**፹፭. <u>በባለሥልጣኑ ውሳኔ ላይ ስለሚቀርብ ይግባኝ</u>**

ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፹፬ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ተከራካሪ ወገን ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ቀጥሎ ባሉት ፳፩ (ሃያ አንድ) የሥራ ቀናት ውስጥ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

## ምዕራፍ አሥራ ሦስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፹፮. <u>አስተዳደራዊ ቅጣቶች</u>**

፩/ በማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት የተሾመ ወይም የተመደበ ሰው በዚህ አዋጅ እና በአዋጁ መሠረት በሚወጡት መመሪያዎች መሠረት እንደሁኔታው የግዥ ዕቅድ፣ የግዥ አፈጻጸምና ንብረት አስተዳደር ሪፖርት ያላቀረበ ወይም መቅረቡን ያላረጋገጠ፣ ወይም በባለሥልጣኑ የግዥና ንብረት ኦዲት ግኝት መሠረት ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ ያልወሰደ ወይም እርምጃ መወሰዱን ያላረጋገጠ፣ ወይም የቦርዱን ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ ያልፈፀመ፣ ወይም በዚህ አዋጅ እና በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጡ መመሪያዎች መሠረት ለሕዝብ ይፋ መደረግ ያለባቸውን መረጃዎች ይፋ ያላደረገ ወይም መደረጋቸውን ያላረጋገጠ፣ ወይም የግዥና የንብረት አስተዳደር ሰነዶችን አደራጅቶ ያልያዘ፣ ወይም ንብረት በወቅቱ ያላስወገደ፣ ኃላፊነቱን በአግባቡ ባለመወጣቱ ከብር ፭ሺህ እስከ ብር ፲ሺህ በሚደርስ አስተዳደራዊ መቅጮ ይቀጣል::

**85. <u>Appeal On the Decision of the Authority</u>**

Any party aggrieved by the decision of the Authority pursuant to Sub-Article (2) of Article 84 of this Proclamation may appeal to Federal High Court for adjudication within 21 (twenty one) working days next following the date of the decision by the Authority.

## CHAPTER THERTEEN
## MISCELANEOUS PROVISIONS

**86. <u>Administrative Penalties</u>**

1/ Any person appointed to or employed by a Public Body, who, as the case maybe, should have but failed to submit or to ensure the submission of public procurement or property administration plan or public procurement and property administration report in accordance with this Proclamation or the Directives to be issued hereunder, or to take corrective measures based on procurement and property audit findings or to ensure that such measures are taken, or fails to comply with the decision or order of the Board, or to make accessible to the public information that the public should know of pursuant to this Proclamation or the Directive to be issued hereunder or to ensure that such information is made accessible to the public, or fails to maintain public procurement and property administration documents in an organized manner, or fails to dispose of property in due time, shall be liable for breach of duty to administrative penalty of Birr 5,000 to 10,000.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚጣል አስተዳደራዊ ቅጣት በእያንዳንዱ ጥፋት ልክ የሚጣል ሲሆን፣ በሕግ የተጣለበትን ግዴታ ባለመወጣት ከሦስት ጊዜ በላይ አስተዳደራዊ ቅጣት የተጣለበት ሰው ላይ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ከባለሥልጣኑ በሚቀርብለት ሪፖርት መሠረት ሚኒስትሩ እንደአግባብነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ወይም ለሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ያቀርባል፡፡

፫/ ሚኒስትሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) መሠረት የሚጣሉ አስተዳደራዊ ቅጣቶችን ያስፈጽማል፣ ይህንን ለማስፈፀም የሚያስችል ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፡፡

፬/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አፈፃፀም "የተመደበ ሰው" ማለት የመንግሥት መሥሪያ ቤት የግዥ እና/ወይም የንብረት አስተዳደር ተግባራትን የሚያከናውን የሥራ ክፍልን እንዲመራ የተመደበ የሥራ ኃላፊ ነው፡፡

**፹፯. <u>ደንብ እና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>**

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈፀም ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ ይህን አዋጅ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚወጣ ደንብን ለማስፈፀም የሚረዱ መመሪያዎችን ያወጣል፡፡

፫/ ሚኒስቴሩ በብሔራዊ ደህንነት፣ በሀገር መከላከያ ምክንያት፣ በፌደራል መንግሥት ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶችን፣ በማዕከል የሚፈፀሙ የመድሐኒት አቅርቦቶች እና የህክምና

2/ The administrative penalty to be imposed pursuant to Sub-Article (1) of this Article shall be for each instance of breach of duty and if a person has been penalized for failing to discharge his obligations for more than three times, the Minister, upon report from the Authority, shall communicate the matter to the Prime Minister's Office or the Civil Service Commission, as the case maybe, to take the appropriate action on such person.

3/ The Minister shall cause the enforcement of the administrative penalties to be imposed as per Sub-Article (1) and (2) of this Article and issue a Directive for its proper implementation.

4/ For the purpose of Sub-Article (1) of this Article, person employed by a Public Body means a person entrusted with the responsibility of directing the procurement and/or property administration units of a Public Body.

**87. <u>Power to Issue Regulation And Directive</u>**

1/ The Council of Ministers may issue Regulations for the implementation of this Proclamation.

2/ The Ministry shall issue Directives for the implementation of this Proclamation and Regulations that may be issued in accordance with Sub-Article (1) of this Article.

3/ Subject to the fundamental Principles laid down in Article 4 of this Proclamation and by taking into consideration their peculiar characteristics, the Ministry shall issue procurement and property administration

መሣሪያ ግዥዎችን እና የተወሰኑ ዕቃዎችን ወይም ከምክር ውጭ የሆኑ አገልግሎቶችን በተመለከተ ልዩ ባህሪያቸውን ከግምት በማስገባት እና በዚሁ አዋጅ አንቀፅ ፬ የተጠቀሱ መርሆዎችን በመከተል ልዩ የግዥ አፈፃፀም ወይም ንብረት አስተዳደር መመሪያ ያወጣል፡፡

**፹፰. <u>የተሻሩና ተፈፃሚ የማይሆኑ ሕጎች</u>**

፩/ የኢትዮጵያ የፌደራል መንግሥት የግዥ እና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፮፻፵፱/፪ሺ፩ ተሽሮ በዚህ አዋጅ ተተክቷል፡፡

፪/ ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም በተሻረው አዋጅ መሠረት የወጣው ደንብ እና መመሪያዎች ከዚህ አዋጅ ጋር እስካልተቃረኑ እና እንደቅደም ተከተላቸው በአዲስ ደንብ ወይም መመሪያዎች እስኪተኩ ድረስ ተፈፃሚነታቸው ይቀጥላል፡፡

፬/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም በፌደራል መንግሥት ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶች የወጡ የግዥ እና የንብረት አስተዳደር መመሪያዎች በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፹፯ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት ሚኒስቴሩ በሚያወጣቸው ልዩ መመሪያዎች እስኪተኩ ድረስ ተፈፃሚነታቸው ይቀጥላል፡፡

Directives for National Defense, National Security, Federal Government Owned Enterprises, centrally procured medical supplies and medical equipments and certain goods or services.

**88. <u>Repealed and Non-Applicable laws</u>**

1/ The Ethiopian Federal Government Public Procurement and Property Administration Proclamation No. 649/2009 is hereby repealed and replaced by this Proclamation.

2/ No Proclamation, Regulation, Directive or practice which is inconsistent with this Proclamation shall have effect in respect of matters provided for in this Proclamation.

3/ Notwithstanding the provision of Sub-Article (1) of this Article, any Regulation and Directives issued in accordance with the repealed Proclamation shall continue to apply to the extent that they are not inconsistent with this Proclamation and until they are replaced by new Directives.

4/ Notwithstanding the provision of Sub-Article (1) of this Article, procurement and property administration Directives issued by Federal Government Owned Enterprises shall continue to apply until such Directives are replaced by the special Directives the Ministry issues in accordance with Sub-Article (3) of Article 87 of this Proclamation.

**፹፱. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>**

ይህ አዋጅ ከመፅናቱ በፊት ተጀምረው አዋጁ በፀደቀበት ዕለት ያልተጠናቀቁ የመንግሥት የግዥ እና የንብረት አስተዳደር ሥራዎች ወይም ክርክሮች በመንግሥት የግዥና የንብረት አስተዳደር ፮፻፵፱/፪ሺ፩ እና በአዋጁ መሠረት በወጡ መመሪያዎች መሠረት ፍፃሜ ያገኛሉ፡፡

**፺. <u>የመብትና ግዴታዎች መተላለፍ</u>**

በመንግሥት የግዥና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፮፻፵፱/፪ሺ፩ ተቋቋሞ የነበረው የመንግሥት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፱ ለተቋቋመው ባለሥልጣን ተላልፈዋል፡፡

**፺፩. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጳጉሜ ፬ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም**

**ሣህለ ወርቅ ዘውዴ**
**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ**
**ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**89. <u>Transitory Provision</u>**

Any proceedings of procurement or sale of disposable property beginning or disputes arising in respect of such proceedings before the entry into force of this Proclamation and pending on the effective date of this Proclamation shall be completed in accordance with the Public Procurement and Property Administration Proclamation No. 649/2009 and the Directives issued there under.

**90. <u>Transfer of Rights and Obligations</u>**

The rights and duties of Public Procurement and Property Administration Agency established under Article 12 of Public Procurement and Property Administration Proclamation No. 649/2009 are hereby transferred to the Authority established under Article 9 of this Proclamation.

**91. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, On this 9th Day of September, 2024.**

**SAHLE WORK ZEWDE**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**